አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

# አዲስ ልሳን

ቅጽ 32 ቁጥር 3553 | ቅዳሜ ታህሳስ 18 ቀን 2018 ዓ.ም | ዋጋው 10.00 ብር




# ሌላኛው የዲፕሎማሲ እርካብ

- ኮፕ-32 ኢትዮጵያ በዓለም መድረክ ላይ ያላትን ተሰሚነት እንደሚያሳድግ ተጠቁሟል

5



ፎቶ- ከገፀ ድር

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በኮፕ 32 ጉባኤ ዝግጅት ዙሪያ ከአፍሪካ ህብረት ኮሚሽን ሊቀ መንበር ማህሙድ አሊ የሱፍ ጋር በተወያዩበት ወቅት

## ለጋራ ትርክት መሠረት የሚጥሉ አሻራዎች

8



ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

በአራዳ ፓርክ ከሚገኙት የጥበብ ስራዎች መካከል ለዓድዋ ድል መገኘት አስተዋፅዖ የነበራቸውን ኢትዮጵያውያን የሚዘክሩት ተጠቃሾች ናቸው

## አዲሱ የህይወት ምዕራፍ

4



ፎቶ ከፋይል

በ'ለነገዋ' የሴቶች ተሃድሶና ክህሎት ማበልጸጊያ ማዕከል ሰልጥነው ስራ ከተፈጠረላቸው ሴቶች መካከል ጥቂቶቹ

## የሰባ ደረጃ ፍካት

11



ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

በኮሪደር ልማቱ ውበት የተጎናጸፈው ሰባ ደረጃ

# የጤና ቱሪዝም ጠቦች

- በአዲስ አበባ እየተገነቡ ያሉ አዳዲስ እና የነባር ሆስፒታሎች እድሳት የጤና ቱሪዝምን ለማስፋፋት የተያዘውን ውጥን እንደሚያግዙ ተጠቁሟል

በሳህሉ ብርሃኑ

በዓለም ላይ የጤና ቱሪዝም ዘርፍ በፍጥነት እያደገ ያለ ኢንዱስትሪ ሲሆን፣ በየጊዜው አዳዲስ ፈጠራዎችን እያሳየ የሚገኝ ዘርፍም ነው። እንደ የቴሌ መድኃኒት፣ ሰው ሰራሽ አስተውሎት እና ሮቦቲክስ ያሉ ቴክኖሎጂዎች ደግሞ ዘርፉ እያደገ ስለመሆኑ ማሳያ ተደርገው ከሚጠቀሱ ጉዳዮች ዋነኞቹ ናቸው፡፡ የርቀት ህክምና አገልግሎትም እየተስፋፋ በመምጣቱ ታካሚዎች ወደ ሌላ ሀገር ከመጓዛቸው በፊት ከውጭ ሀኪሞች ጋር በቪዲዮ መገናኘት፣ የምክር አገልግሎት ማግኘት እና ለቀዶ

ወደ ገጽ 3 ዞሯል



ፎቶ- ከገፀ ድር

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በዘውዲቱ መታሰቢያ ሆስፒታል ውስጥ የተገነባውን የላቀ የሕክምና ማዕከል መርቀው ስራ ባስጀመሩበት ወቅት

# አገልግሎትን በቴክኖሎጂ የማስደገፍ ጥረት ምን ለውጥ እያመጣ ነው?

- በአዲስ አበባ 347 አገልግሎቶች በቴክኖሎጂ በመታገዝ እየተሰጡ ይገኛሉ

በስንታየሁ ምትኩ

“ከዚህ ቀደም የይዞታ ማረጋገጫ ለማውጣት ብዙ ጊዜ ተመላልሻለሁ፡፡ ተስፋ ቆርጬ ነበር፤ በብዙ ልፋት ነው ካርታውን ያወጣሁት፡፡ በአሁኑ ወቅት አገልግሎቱ በቴክኖሎጂ ታግዞ የሚሰጥ በመሆኑ ቀልጣፋ ሆኗል፡፡ በሲስተም አማካኝነት ስልኬ ላይ በሚደርሰኝ መልእክት መሰረት ወደሚመለከተው ክፍል በመሄድ አገልግሎት አግኝቻለሁ፡፡ ጊዜዬንም

ወደ ገጽ 6 ዞሯል




አድራሻ +251 111 112 218 +251 111 267 266 www.amn.gov.et 5 kilo infront of St. Mary Church Addis Ababa Ethiopia

# ርዕሰ አንቀፅ




## የጤናው ዘርፍ ልማት ለቱሪዝም በር የሚከፍት ነው!

የቱሪዝም ጸጋችንና የተጠቀምንበት መንገድ ለየቅል ሆኖ ቆይቷል፡፡ ሀብቱ እያለን፣ ማልማትም እየቻልን “ጆሮ ዳባ” በማለታችን “ጭስ አልባ ኢንዱስትሪ” ከሚባልለት ከዚህ ዘርፍ ስናገኝ የቆየነው ገቢ በሚፈለገው ልክ ሳይሆን ቆይቷል፡፡ አሁን ላይ ይህን ሊያካክስ በሚችል መልኩ የዘርፉን የእይታ መስክ ከማስፋት ጀምሮ ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶት የተለያዩ ስራዎች እየተከወኑ መሆናቸው የጤና ቱሪዝም ሁነኛ ማሳያ ነው፡፡

አዲስ አበባ የኢትዮጵያውያንና አፍሪካውያን መዲና፣ የዲፕሎማቲክ ማህበረሰቡም መቀመጫ ናት፡፡ የጤናው ዘርፍ ይህን ማህበረሰብ በሚመጥን፣ የስማርት ሲቲነት ጉዞዋን በሚያሳልጥ መልኩ መጎልበት ይጠበቅበታል፡፡ ለዚህ የሚሆን መሰረት እየተጣለ ለመሆኑ እየተከናወኑ ያሉ ስራዎች የተግባር አስረጂዎች ናቸው፡፡ በሁሉም ክፍለ ከተሞች ያሉ ጤና ጣቢያዎች የሰው ሃይላቸውን በማብቃት እና ዘመናዊ የህክምና መሳሪያዎችን በማስታጠቅ ከመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል አገልግሎት ጋር እኩል ደረጃ እንዲኖራቸው ማድረግ ላይ አበረታች ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ በአቃቂ ቃሊቲ፣ በንፋስ ስልክ ላፍቶ እና በኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተሞች አዳዲስ ሆስፒታሎች እየተገነቡ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በሚኒልክ፣ በራስ ደስታ እና በዘውዲቱ ሆስፒታሎች አቅማቸውን በብዙ የሚያሳድግ የማስፋፊያ ስራ ተሰርቷል። እነዚህ ተግባራት የዘርፉን አገልግሎት ለማዘመን የሚደረገውን ጥረት የሚያሳይ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በጤና ቱሪዝሙ በኩል ያለውን እምቅ አቅም አሟጦ ለመጠቀም እየተሄደበት ያለውን ርቀት በግልፅ የሚያመላክት ነው፡፡

በአዲስ አበባ የአፍሪካ ህብረት ስብሰባን ጨምሮ በርካታ አህጉር እና ዓለም አቀፍ ጉባኤዎች ሲካሄዱ ቆይተዋል። በቀጣይም ኮፕ 32 ጉባኤን ጨምሮ ዘርፈ ብዙ ፋይዳ ያላቸው ሁነቶችን ታስተናግዳለች፡፡ የተሳታፊዎቹ ቁጥር ደግሞ ከዕለት ዕለት እየጨመረ መምጣቱን መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በዚህ ልክ ድርብርብ ኃላፊነትን እየተወጣች፣ ተምሳሌትነቷም እየፈካ ያለች ከተማ በሁለንተናዊ መልኩ አርዓያ ሆና መቀጠሏ ውዴታ ሳይሆን ግዴታ ነው፡፡ የጤና ቱሪዝሙም በዚህ ልክ ሊታይ ይገባዋል፡፡ በጤና ቱሪዝም ተደራሽ ከሆኑ ከተሞች መካከል ባንኮክ፣ ኢስታንቡል፣ ሴኡል፣ ሲንጋፖር እና ደልሒ ከግንባር ቀደም ተጠቃሾች መካከል ናቸው፡፡ ከእነዚህ ሀገራት ልምድና ተሞክሮ በመውሰድ ዘርፉን የበለጠ ማስፋትና ማሳደግ ያስፈልጋል፡፡

እንደ ከተማ ብሎም ሀገር ዘርፉ ላይ የሚከናወን ተግባር ጤናው የተጠበቀ ትውልድ እንዲኖር ማስቻል ብቻ ተደርጎ መታየት የለበትም፡፡ የቱሪዝሙ አንድ አካል ሆኖ ኢኮኖሚውን መደገፍ የሚችል ገንዘብ የሚያስገኝ ጭምር ነው፡፡ ለዚህ ግን የመንግስት አካላት ብቻም ሳይሆኑ የግል ባለሃብቶችም ጭምር ዘርፉ ላይ በትኩረት መስራት ይጠበቅባቸኋል፡፡ መንግስትም እነዚህን አካላት የሚደግፍበትንና የሚያበረታታበትን አሰራር አጠናክሮ ማስቀጠል ግድ ይለዋል፡፡ ይህ ሲሆን በዚህ ዘርፍ ያለውን የቱሪዝም እድል አሁን ካለውም በላይ ማስፋት እንደሚቻል በመገንዘብ ርብርብ ማድረግ ይጠበቃል፡፡

# የእኔ እይታ

ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን በነፃነት የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም።

## ትኩረት የሚሻው የችግኝ እንክብካቤ ተግባር

**ኤግል ከ6 ኪሎ**

ከለውጡ ወዲህ አበረታች ውጤት ተገኝቶባቸዋል ብዬ በልበ ሙሉነት ከምመሰክርላቸው ተግባራት አንዱ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ነው፡፡ መርሃ ግብሩ የተራቆቱ አካባቢዎችን በደን ለመሸፈን አስችሏል ብዬ አምናለሁ፤ የኢትዮጵያ የደን ሽፋን በ2011 ዓ.ም ከነበረበት 17 ነጥብ 2 በመቶ አሁን ወደ 23 ነጥብ 6 በመቶ ከፍ ብሏል፤ ሥራው ለመንግሥት ብቻ የተተወ አለመሆኑና መላውን ህብረተሰብ ባሳተፈ መልኩ መተግበሩ ደግሞ ውጤታማነቱን ከፍ አድርጎታል ብዬ አምናለሁ፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ ደረጃም በአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብሩ ሳቢያ ቀላል የማይባል የደን ሽፋን እድገት ተገኝቷል ብል ማጋነን አይሆንብኝም። መርሃ ግብሩ ከመጀመሩ በፊት 15 ነጥብ 8 በመቶ የነበረው የአዲስ አበባ ከተማ የደን ሽፋን አሁን ወደ 23 በመቶ ከፍ ብሏል፡፡ በቅርብ ጊዜ ውስጥም ሽፋኑን ወደ 30 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ እየተሰራ ይገኛል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ ከገላጣ ቦታዎች ባሻገር የመንገድ አካፋዮች፣ መናፈሻዎች፣ የጋራ መኖሪያ ቤቶች እንዲሁም ኪስ ቦታዎች ሁነኛ የችግኝ መትከያ ስፍራዎች ናቸው፡፡ እንዲህ ባሉ ስፍራዎች ባለፉት ተከታታይ ዓመታት በተከናወነው በዚህ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር አብዛኞቹ የከተማዋ ክፍት ቦታዎች በተለያዩ የእፅዋት ዝርያዎች ተሸፍነዋል፡፡ በተለይ የኮሪደር ልማት ስራ ከተጀመረ ወዲህ የመንገድ አካፋዮች እና የመንገድ ዳርቻዎች በተለያዩ የእፅዋት ዝርያዎች አሸብርቀዋል፡፡

ነገር ግን ከተከላ በኋላ ችግኞችን በኃላፊነት ከመንከባከብ አንፃር ምን እየተሰራ ነው? የሚለው ጉዳይ አጠያያቂ ነው፡፡ በየዓመቱ ያለው የፅድቀት መጠን ሲታይም የእንክብካቤ ውስንነት መኖሩን መገንዘብ ይቻላል። ስለዚህ በክረምት ወቅት የተተከሉ ችግኞችን በበጋው ወቅት ያለውን የአየር ሁኔታ ክብደት እንዲቋቋሙ ተገቢውን እንክብካቤ ማድረግ የውዴታ ግዴታ ይሆናል፤ በዚህ ረገድ ክፍተት እንዳይፈጠር በትኩረት መስራት እንደሚገባ አምናለሁ፡፡

በመንገድ ዳርቻዎች፣ በከተማዋ ክፍት ቦታዎች እና ከእይታ በራቁ አካባቢዎች የተተከሉ ችግኞች ከእንክብካቤ እጦት የተነሳ እየተጎዱ እንደሆነ ይሰማኛል፡፡ ስለዚህ እነዚህ ችግኞችን ከቤት እንስሳት ጥቃትና ሌሎች አደጋዎች መታደግ የውዴታ ግዴታ ነው፡፡

ዕድገቱ የተስተካከለ፣ ጤናማና ለተከላ ብቁ የሆነ ችግኝ ለማዘጋጀት ዘር ከተዘራበት ጊዜ አንስቶ ችግኙ ከጣቢያው እስከሚነሳበት ጊዜ ድረስ ችግኞች ሥርጭቱ የተስተካከለ የውሃ አቅርቦት ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡

ጠንካራና ጤናማ ችግኞችን ለማብቀል የሚያስችል አፈር ሊኖረውም ይገባል፡፡ ችግኞችን ተክሎ ዞር ማለት ሳይሆን ጽድቀታቸውን መከታተልም ያስፈልጋል እላለሁ፡፡ በአንዳንድ አከባቢዎችም ተተክለው በጉዲፈቻ መልክ ለተቋማት የተሰጡ ችግኞች አስታዋሽ ይፈልጋሉና ትኩረት ሰጥተን ልንከባከባቸው ይገባል እላለሁ፡፡

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እየተዘጋጀች

ዘወትር ቅዳሜ ወደ አንባቢያን
የምትደርሰው ይህች ጋዜጣ

ግንቦት 1985 ዓ.ም
ተመሰረተች

**አድራሻ**
አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት
በሚገኘው ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን
ስልክ ቁጥር 0111-574923
ፖ.ሣ.ቁ 27080 code 1000
ፋክስ - 559368
addislisan1985@gmail.com

**የገበያ አገልግሎት እና የማስታወቂያ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት**
ስልክ 0111 - 112218

**አታሚ**
ሜልባ ፕሪንቲንግ ፐብሊሺንግ ኤንድ ፓኬጂንግ ሼር ካምፓኒ

**ግራፊክስ ዲዛይን**
ዳንኤል ተስፋይ

**ሌይአውትና ዲዛይን**
ፍልሰታ አየለ
መና ዮሐንስ

**የእርምት ባለሙያ**
ቸርነት ዋለልኝ
ገነት መላኩ

**የዕለቱ አዘጋጆች**
ለይላ መሀመድ
ይግለጡ ጓዴ
ሄለን ጥላሁን
ፋንታነሽ ተፈራ

**ዋና አዘጋጅ**
ተካልኝ አማረ
Tekalignteke123@gmail.com
አድራሻ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
ወረዳ 3 የቤት ቁጥር B91/17

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ
መለስ ተሰጋ

**ከፍተኛ አርታኢያን**
ደረጀ ታደሰ
ጊዜው አማረ
ስንታየሁ ምትኩ
ሳህሉ ብርሃኑ

# የአዲስ ... ከገጽ 1 የዞረ

ጥገናም ሆነ ለሌላ ህክምና መዘጋጀት የሚችሉበት ደረጃ ላይ ተደርሷል።

በጤናው ዘርፍ እዚህ ደረጃ ላይ ደርሰው በጤና ቱሪዝም ታዋቂ መዳረሻ ከሆኑ ሀገራት መካከል ህንድ፣ ቱርክ፣ ታይላንድ፣ ማሌዢያ፣ አሜሪካ እና ደቡብ አሜሪካ በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ፡፡ የዓለም የጤና ቱሪዝም ማህበር እ.ኤ.አ በ2024 ባወጣው መረጃ መሰረትም በየዓመቱ እስከ 14 ሚሊዮን የሚደርሱ ሰዎች ለህክምና ወደ ሌሎች ሀገራት ይጓዛሉ። የዓለም አቀፉ የህክምና ቱሪዝም ገበያ በየዓመቱ በአማካኝ በ8 ነጥብ 8 ቢሊዮን ዶላር እያደገ ሲሆን፣ እ.ኤ.አ በ2024 የገበያው ግምት ከ 41 ነጥብ 7 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር በላይ ነበር። ይህ ገቢ እ.ኤ.አ በ2034 ወደ 186 ቢሊዮን ዶላር እንደሚያድግ ተገምቷል።

በዘርፉ ከሚንቀሳቀሰው ከፍተኛ ሀብት ውስጥ በቀዳሚነት ከሚቋደሱ ሀገራት መካከል ደግሞ ህንድ ትገኝበታለች፡፡ እ.ኤ.አ በ2023 ለንባብ የበቃው የግሎባል ሄልዝ አክሪዲቴሽን (Global Healthcare Accreditation) መረጃ እንደሚያሳየው፣ ህንድ በጤና ቱሪዝም ዘርፍ ዋና ተዋናይ ስትሆን ሀገሪቱ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመታገዝ ውስብስብ የልብ ቀዶ ጥገና፣ የካንሰር ህክምና እና የአካል ክፍሎች ንቅለ ተከላ የመሳሰሉ አገልግሎቶችን ትሰጣለች። ለጤና ቱሪስቶች የተመቻቸ የቪዛ አሰራር መኖሩ ብዙ ሰዎች ህንድን እንዲመርጡ የሚያግዝ ሲሆን፣ በዚህም የጤና ቱሪዝም ዘርፍ የሀገሪቷ ዓመታዊ ገቢ በ2022 ወደ 7 ነጥብ 4 ቢሊዮን ዶላር ደርሶ እደነበር መረጃው ያሳያል።

ጉዳዩን ወደ አህጉረ አፍሪካ መልሰን እንመልከት፡፡ የጤና ቱሪዝም በአፍሪካ እያደገ ያለ ኢንዱስትሪ ቢሆንም፣ ከሌሎች የዓለም ክልሎች ጋር ሲወዳደር ገና በጅምር ላይ ያለ ነው ማለት ይቻላል። ምንም እንኳን አንዳንድ የአፍሪካ ሀገራት ከጤና ቱሪዝም ገቢ የሚያገኙ ቢሆንም፣ አፍሪካ በአጠቃላይ ለህክምና ወደ ውጭ ሀገራት ለሚጓዙ ዜጎቿ በየዓመቱ ከፍተኛ ገንዘብ ታወጣለች። የአፍሪካ ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ እንደገለጸው፣ አፍሪካ በየዓመቱ ወደ 7 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር በጤና ቱሪዝም ምክንያት ታወጣለች።

ወደ ኢትዮጵያም መለስ ስንል አዲስ አበባን የጤና ቱሪዝም መዳረሻ ለማድረግ እንቅስቃሴዎች እንደተጀመሩና በመንግስት ደረጃ ከሚሰሩ ስራዎች ባሻገር የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ በማሳተፍ በርካታ ተግባራት በመከናወን ላይ እንደሚገኙ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በቅርቡ መናገራቸው የሚታወስ ነው፡፡

አዲስ አበባ በአፍሪካ ደረጃ የጤና ቱሪዝም ማዕከል ለመሆን ያላትን አቅም ለመጠቀምና ደረጃዋን ለማሳደግ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ተጨባጭ ጥረቶችን እያደረገች ትገኛለች። ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ የ2017 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት እና የ2018 በጀት ዓመት ዋና ዋና አቅጣጫዎችን ለአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ባቀረቡበት ወቅት እንደገለፁት፣ የጤና ቱሪዝምን ከማሳካት አንፃር በርካታ ጥረቶች እየተደረጉ ነው። ለአብነትም በኮልፌ ቀራንዮ እና በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተሞች የሁለት



ፎቶ- ከገፀ ድር

አዲስ አበባ የጤና ቱሪዝም መዳረሻ በሚያደርጋት ልክ የአዳዲስ ሆስፒታሎች ግንባታና ነባሮቹንም የማደስ ተግባር እያከናወነች ትገኛለች

አዳዲስ ግዙፍ አጠቃላይ ሪፈራል ሆስፒታሎች ግንባታ በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል፡፡ እንዲሁም በጥሩነሽ ቤጂንግ፣ በራስ ደስታ፣ በዘውዲቱ እና በሚኒሊክ ሆስፒታሎች የተሰሩ ግዙፍ የማስፋፊያ ስራዎችም ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ከንቲባ አዳነች የዘውዲቱ መታሠቢያ ሆስፒታል የሕክምና ማዕከል የማስፋፊያ ግንባታን መርቀው በከፈቱበት ወቅት እንደገለፁት፣ በከተማዋ 28 የጤና ተቋማት ተጠናቅቀው ወደ ስራ መግባት ችለዋል፡፡ የዘውዲቱ መታሠቢያ ሆስፒታል ግንባታም ሆስፒታሉን የልህቀት ማዕከል ማድረግ የሚያስችል ነው።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ ኃላፊው ዮሐንስ ጫላ (ዶ/ር) በበኩላቸው፣ በመዲናዋ በጤናው ዘርፍ ተደራሽነትን፣ ፍትሐዊነትን እና ጥራትን መሠረት ያደረጉ ውጤታማ ሥራዎች መሰራታቸውን ተናግረዋል። እንደዚሁም የነባር ሆስፒታሎችን ደረጃ ከማሳደግ ባለፈ፣ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ ሊሆኑ የሚችሉ ዘመናዊ ሆስፒታሎችን ግንባታ አጠናቅቆ ወደ አገልግሎት ለማስገባት በሂደት ላይ እንገኛለን ብለዋል፡፡

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ እና በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ እየተገነቡ ያሉ ሆስፒታሎችም እያንዳንዳቸው ከ500 በላይ አልጋዎችን መያዝ የሚችሉ መሆናቸውን የጠቀሱት የቢሮ ኃላፊው፣ የጥራት ደረጃቸውም ዓለም አቀፋዊ እንዲሆን ጥረት እየተደረገ ነው ብለዋል፡፡

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ገላን አካባቢ የተገነባው እና ከ511 በላይ አልጋዎች ያሉት ሆስፒታልም፣ በምስራቅ አፍሪካ የመጀመሪያው ሊሆን እንደሚችል እና ይህም ከተማዋን የጤና ቱሪዝም መዳረሻ ለማድረግ የተጀመረውን ጉዞ እውን ለማድረግ እየተሰራ ያለውን ስራ ማሳያ ናቸው፡፡

እንደዚሁም ረጅም እድሜ ያስቆጠሩ የዘውዲቱ እና የራስ ደስታ ሆስፒታሎችን ጨምሮ ሌሎችንም በማደስ፣ ግዙፍ ዘመናዊ ሆስፒታሎች በማድረግ አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርገዋል፡፡ በእነዚህ ሆስፒታሎች እያንዳንዱ ታካሚ በቂ ኦክሲጅን እንዲያገኝ ለማስቻል ኦክሲጅንን ከማምረት ጀምሮ ሌሎች የህክምና ግብዓቶችም ተሟልተው መገንባታቸውን ተናግረዋል፡፡ የግሉን የጤና ዘርፍ ለማበረታታትም ለጤና ተቋማት ግንባታ የሚውል የመሬት አቅርቦት በመደረጉ ሰፋፊ ስራዎች በመከናወን ላይ እንደሚገኙ የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ መረጃ ያሳያል፡፡

በሌላ በኩል ስምንት አዳዲስ ጤና ጣቢያዎች በቅርቡ ስራ የሚጀምሩ ሲሆን፣ በአራት ነባር ሆስፒታሎች እና ሌሎች ተጨማሪ ጤና ጣቢያዎች የተቋማቱን አቅም በሚያሳድግ መልኩ ሰፊ እድሳቶች ተሰርተዋል፡፡ የአዳዲስ ሆስፒታሎች ግንባታዎች እና የነባሮቹን ደረጃ የማሻሻል ስራ ከተማዋ እየሄደችበት ላለው የጤና ቱሪዝምን የማስፋፋት ውጥን እንደሚያግዙ እሙን ነው፡፡

የአፍሪካ የጤና ልህቀት ማዕከል (Africa CDC) በመዲናዋ መገኘት መዲናዋ የአፍሪካ የጤና ዋና መዲና እንድትሆን ትልቅ ሚና ይጫወታል። አዳዲስ የግልና ግዙፍ የሕክምና መንደሮች ግንባታ በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር ወጪ እየተደረገባቸው ነው። እነዚህ ተቋማት ቀደም ሲል ኢትዮጵያውያን ወደ ውጭ ሀገር ሄደው የሚታከሙባቸውን እንደ ካንሰር፣ የልብና የኩላሊት ንቅለ ተከላ ያሉ ሕክምናዎችን እዚሁ ለመስጠት የሚያስችሉ ናቸው።

የጤና ቱሪዝም ከሕክምናው ባለፈ የታካሚው የማገገሚያ ጊዜ ምቾት የተሞላበት ያደርጋል። የፓርኮችና የመዝናኛ ስፍራዎች ግንባታ ከተማዋን ለጎብኚዎች ሳቢ አድርጓታል። የሆቴልና ትራንስፖርት አገልግሎት ዘርፍም ለጤና ቱሪዝም ዕድገት ከፍተኛ ሚና ያለው በመሆኑ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከአፍሪካና ከዓለም ጋር ያለውን ትስስር በመጠቀም "Medical Tourism" ፓኬጆችን ለማዘጋጀት ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር ዮሐንስ (ዶ/ር) ይገልጻሉ።

አዲስ አበባ በርካታ የሕክምና ኮሌጆችና የምርምር ተቋማት መገኛ በመሆኗ፣ የልዩ ባለሙያዎችን (Specialists) ቁጥር ለማሳደግና ጥራቱን ለመጠበቅ ከውጭ ሀገር የሕክምና ተቋማት ጋር የቴክኖሎጂና የእውቀት ሽግግር ስምምነቶች እየተደረጉ ነው። የአፍሪካ ሕብረትና የዓለም አቀፍ ድርጅቶች መቀመጫ በመሆኗ፣ በከተማዋ የሚኖሩና ለስብሰባ የሚመጡ ዲፕሎማቶች እዚሁ ሕክምና እንዲያገኙ በማድረግ የጤና ቱሪዝሙን የማስተዋወቅ ስራ እየተሰራ መሆኑ መዲናዋ የሕክምና መዳረሻ ለመሆን እየተጋች ስለመሆኑ ማሳያዎች ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ።

በእርግጥ በዘርፉ ተወዳዳሪ ለመሆን በመሰረተ ልማት፣ በቴክኖሎጂ እና በባለሙያዎች ስልጠና ላይ ትልቅ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስ እንደሚያስፈልግ የዘርፉ ባለሙያዎች ይስማማሉ። 'ማፒንግ ዘ ሰስቴይነብል ደቨሎፕመንት ኢን ሄልዝ ቱሪዝም' (Mapping the Sustainable Development in Health Tourism) የተሰኘ ጥናታዊ ጥሑፍ ላይ እንደሰፈረው አንድ ከተማ የጤና ቱሪዝም ማዕከል (Medical Tourism Hub) ሆናለች ሲባል፣ ከተማዋ ጥራት ያለው የሕክምና አገልግሎት ፍለጋ ወደ ሀገር ቤት ለሚመጡ ተጓዦች ተመራጭ መዳረሻ ሆናለች ማለት ነው።

ምቹ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያና የከተማ ትራንስፖርት፣ ለታካሚዎችና ለቤተሰቦቻቸው የሚሆኑ ሆቴሎችና የእንግዳ ማረፊያዎች እንደዚሁም ለሕክምና ለሚመጡ ሰዎች የሚሰጥ ፈጣንና ቀላል የቪዛ አሰጣጥ ሂደት ሊኖር እንደሚገባም ጥናቱ ላይ ሰፍሯል።

ጥናታዊ ጽሑፉን ያቀረቡት የዘርፉ ተመራማሪዎች ሆሴ ሉይስ አብራንቴስ እና ሳንድራ ኮስታ እንደሚያብራሩት፣ ሕክምናው ብቻ ሳይሆን፣ ከሕክምና በኋላ ያለው የማገገሚያ ጊዜ በከተማዋ በሚገኙ የመዝናኛ ቦታዎች፣ ስፓዎች (Spas) ወይም የተፈጥሮ መዳረሻዎች እንዲያሳልፍ ይደረጋል። ይህም ከተማዋን የጤና እና የደህንነት (Wellness) ማዕከል ያደርጋታል።

ተመራማሪዎቹ አያይዘው ሲገልፁም አንድ ከተማ የጤና ቱሪዝም ማዕከል ናት ሲባል፣ ፈውስን ከጉብኝት ጋር አቀናጅታ ለዓለም ገበያ የምታቀርብ፣ በዘርፉ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬና ዝና የምታገኝ ከተማ ትሆናለች ማለት ነው። በተጨማሪም ወደ ውጭ ለሕክምና የሚሄዱ ዜጎችን ቁጥር በመቀነስ የሚባክነውን የውጭ ምንዛሬ ከማዳኑም በላይ የጤና ቱሪዝም መስፋፋት ለሕክምና ባለሙያዎች ብቻ ሳይሆን ለሆቴሎችና ለትራንስፖርት ዘርፍ የሚፈጥረው ዕድል ከፍተኛ ነው።

የአዲስ አበባ ከተማ ኮሚኒኬሽን ቢሮ ከሰሞኑን ባወጣው መግለጫ የጤና ቱሪዝም አሁን ከደረሰበት ደረጃ ይበልጥ በማጠናከር የከተማዋን ስማርት ሲቲ የማረጋገጥ ጉዞ እውን የሚሆንበት ጊዜ ሩቅ አይደለም ብሏል፡፡

በተጨማሪም የነባር ሆስፒታሎችን ደረጃ ከማሳደግ ባለፈ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ ሊሆኑ የሚችሉ ዘመናዊ አዳዲስ ሆስፒታሎችን ግንባታ በፍጥነትና በጥራት በማጠናቀቅ የጤና አገልግሎትን በማሳለጥ ረገድ ረጅም እርቀት መጓዝ ተችሏል።

በመዲናዋ በሁሉም ክፍለ ከተሞች ጭምር ከመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል አገልግሎት ጋር እኩል ደረጃ ያላቸው ጤና ጣቢያዎች በውስጥ አቅም ከፍተኛ በጀት በመመደብ በዘመናዊ የህክምና መሳሪያ እና ሙያዊ ብቃት ባላቸው ባለሙያዎች ጭምር እንዲደራጁ ማድረግ ስለመቻሉም ቢሮው ይገልጻል፡፡

# አዲሱ የህይወት ምዕራፍ

**“ስልጠናው ከሰው በታች እንደሆንኩ ይሰማኝ የነበረውን ስሜት ቀይሮልኛል”**

**የ‘ለነገዋ’ የሴቶች ተሃድሶና ክህሎት ማበልፀጊያ ማዕከል ተጠቃሚ ወጣት እሌኒ ውድነህ**


ፎቶ- ከገፀ ድር
የ‘ለነገዋ’ የሴቶች ተሃድሶና ክህሎት ማበልፀጊያ ማዕከል ከፊልገፅታ



ፎቶ- ከፋይል
በ‘ለነገዋ’ የሴቶች ተሃድሶና ክህሎት ማበልፀጊያ ማዕከል ሰልጥነው ስራ ከተፈጠረላቸው ሴቶች መካከል ጥቂቶቹ

**በሸዋርካብሽ ቦጋለ**

ወጣት ሳራ አዱኛ አብዛኛውን የልጅነት እድሜዋን በብዙ መከራና ውጣ ውረድ ማሳለፏን ትናገራለች፤ ቤተሰቦቿ የልጆቻቸውን የዕለት ጉርስ ለማሟላት እንኳን በእጅጉ የሚቸገሩ፣ ለሰው ልጅ ከሚያስፈልጉ መሰረታዊ ፍላጎቶች አንዱ የሆነውን መጠለያ በቅጡ ያላሟሉ፣ በአዲስ አበባ ጎዳናዎች ላይ እየተዘዋወሩ ሸራ ወጥረው በሚቀልሱት ጎጆ የሚኖሩ ችግረኞች ሆነው ለበርካታ ዓመታት መኖራቸውን ታስታውሳለች፡፡

ኑሮ በእነ ሳራ ቤት በእጅጉ የከበደና ከእጅ ወደ አፍ ከሚባለው ደረጃ እንኳ ያነሰ ነበር፡፡ ለቤተሰቦቿ የመጀመሪያ ልጅ የሆነችው ሳራ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ተከታትላለች፤ የቀን ስራ ሰርተው ቤተሰቡን የሚያስተዳድሩት አባቷ ድንገት ለህልፈት መዳረጋቸው ለእርሷ ብቻ ሳይሆን በቤተሰቡ ዘንድ ያልተጠበቀ አስደንጋጭና መጥፎ አጋጣሚን አስከተለ፡፡ ይህም ቤተሰቦቿን የማስተዳደር ኃላፊነትን መሸከም ነው፡፡ ሳራ በቀጥታ በጉልበት ስራ ተሰማራች፡፡ ያም ሆኖ የጠበቀችውን ያህል የቤተሰቡን ፍላጎት ለመሸፈን አልሞላ ሲላት ሃያ ዓመት እንኳን ሳትደፍን በወጣትነት እድሜዋ ለስደት ተዳረገች፡፡

ከበርካታ ውጣ ወረድ በኋላ ምንም ጥሪት ሳትቋጥር ወደ ኢትዮጵያ ተመለሰች፤ በወቅቱ እዚህም የረባ ስራ ባለማግኘቷ ኑሮ ገፍትሮ ወደ ጎዳና ህይወት አስገባት፤ በሂደት ሱስ እና ሌሎች አልባሌ ድርጊቶች ውስጥ ገባች። ከለውጡ ወዲህ ለተለያዩ ማህበራዊ ቀውሶች የተጋለጡ ሴቶችን ህይወት ለመታደግ በተደረገ ጥረት ተጠቃሚ ሆና አሁን ህይወቷ እየተሻሻለ መሆኑን ከአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ጋር በነበራት ቆይታ ተናግራለች። በካዛንቺስ ‘ሴቶች አደባባይ’ አካባቢ የስራ ዕድል ከተፈጠረላቸው እንስቶች መካከልም አንዷ ሆናለች፡፡

ለወጣት ሳራ እና ሌሎች መሠል ችግር ውስጥ ለነበሩ እንስቶች ህይወት መቃናት መሠረት የጣለው፣ ‘ለነገዋ’ የሴቶች ተሃድሶና ክህሎት ማበልፀጊያ ማዕከል ነው፡፡ ማዕከሉ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ በ53 ሺህ 700 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ያረፈ ሲሆን፣ ደረጃቸውን የጠበቁ የሕንጻ ብሎኮችን፣ ዘመናዊ የስፖርት ማዘውተሪያ ሜዳ፣ ግዙፍ ኤል ኢ ዲ ስክሪን የተገጠመለት የመዝናኛ አምፊ ቴአትር፤ 4 ነጥብ 1 ሄክታር በላይ ስፋት ላይ ያረፈ የአትክልት እርሻ ማሳ እንዲሁም ከፍተኛ መጠን ያለው የራሱ የከርሰ ምድር ውሃ ያካተተ ራሱን ችሎ መንደር ተብሎ ሊጠራ የሚችል ግዙፍ ማዕከል ነው።

ማዕከሉ ለተለያዩ ማህበራዊ ቀውስ የተጋለጡ ሴቶችን ተቀብሎ ሁሉን አቀፍ መሠረታዊ ፍላጎቶች አቅርቦ ከሶስት እስከ ስድስት ወራት የሚቆይ ሙያዊ እና ሥነ-ልቦናዊ ድጋፍና ስልጠናዎችን በመስጠት ለሥር-ነቀል ለውጥ ለማብቃት ታስቦ ነው የተመሰረተው፡፡ ማዕከሉ የሥነ-ውበት፣ የሞግዚትነት፣ የመስተንግዶ፣ የኤሌክትሪክና የሸክላ እንዲሁም የእንጨት ሥራዎች፣ የጋርመንት ስልጠናዎች እና ሌሎች ዘርፈ ብዙ አገልግሎቶችን በመስጠት ላይ ይገኛል። ብዙዎችን አስመርቆ ወደ ስራው ዓለም አስገብቷል፡፡ ወጣት ሳራ ከእነዚህ እንስቶች መካከል አንዷ ነች፡፡ በማዕከሉ ቆይታዋ በልብስ ስፌት፣ ሹራብና ጥልፍ ስራ ሰልጥና አሁን በካዛንቺስ ኮሪደር እና መልሶ ግንባታ ውስጥ በተዘጋጁ ሱቆች ውስጥ ትሰራለች፡፡

ወጣት ሳራ ለስድስት ወራት በማዕከሉ የወሰደችው ስልጠና ከአስቸጋሪ የህይወት መስመር አውጥቶ ዛሬ ላይ በተቃና መንገድ ህይወቷን ለመምራት አስችሏታል፡፡ ከመሰል ጓደኞቿ ጋር በሰለጠነችበት ሙያ ተደራጅታ በሙሉ ፍላጎትና ተነሳሽነት እየሰራች እንደሆነ ትናገራለች፤ ይህም ለነገ ማንነቷ ትልቅ መሰረት እንደሚሆናት ትልቅ ተስፋ አሳድሮባታል፡፡ ማዕከሉ በፈጠረላት የስራ እድል በምታገኘው ልምድና ክህሎት ነገ የራሷን ድርጅት ከፍቶ የመስራት ትልቅ ህልም እንዳላት ስትናገርም በልበ ሙሉነት ነው፡፡

የ‘ለነገዋ’ የሴቶች ተሃድሶና ክህሎት ማበልፀጊያ ማዕከል ተጠቃሚ የሆኑ ሴቶች ታሪክ የጽናትና የድል ታሪክ ነው ቢባል የተጋነነ አይደለም የምትለዋ ወጣት እሌኒ ውድነህ ናት፡፡ ወጣት እሌኒ ልክ እንደ ወጣት ሳራ ሁሉ ከ‘ለነገዋ’ የሴቶች ተሃድሶና ክህሎት ማበልፀጊያ ማዕከል የህይወት ክህሎት እና የሙያ ስልጠና አግኝታ በተለምዶ ካዛንቺስ ‘የሴቶች አደባባይ’ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የስራ እድል የተፈጠረላት ሴት ናት። “ስልጠናው ከሰው በታች እንደሆንኩ ይሰማኝ የነበረውን ስሜት ቀይሮልኛል። እኔም መስራት እችላለሁ፤ እኔም ለሀገሬ ጠቃሚ ነኝ የሚል መንፈስ እንዲያድርብኝ አስችሎኛል” ብላለች፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ የሴቶችን ኢኮኖሚ አቅም ለማሳደግና መብቶቻቸውን ለማስከበር ጠንካራ ጥረት እየተደረገ መሆኑን የማህበራዊ ሳይንስ ምሑር ብስራት አስፋው (ዶ/ር) ይናገራሉ፡፡ ባለሙያው ከአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ጋር ባደረጉት ቆይታ፣ በከተማዋ የተገነቡት ‘ለነገዋ’ የሴቶች ተሃድሶና ክህሎት ማበልፀጊያ ማዕከል እና ጉለሌ የተቀናጀ የልማት ስራ በድህነት ቅነሳና ማህበረሰባዊ ግንባታ ረገድ ጉልህ አስተዋፅኦ እንዳላቸው ገልፀዋል፡፡

ድህነት አዋራጅ ነው ያሉት ምሑሩ፣ “ድህነት ሰዎች አካላቸውን እስከመሸጥ ለሚደርስ ውርደት እንዲጋለጡ ያስገድዳል፡፡ የ‘ለነገዋ’ የሴቶች ተሃድሶና ክህሎት ማበልፀጊያ ማዕከል ተጠቃሚዎች ደግሞ በአብዛኛው በዚያ አይነት ሁኔታ ውስጥ ያለፉ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ ከማዕከሉ ያገኙት ስልጠናና አዲስ የህይወት ምዕራፍ በድህነት ቅነሳ ረገድ ጉልህ ሚና ይኖረዋል፤ ድህነት ሲቀንስ ደግሞ ማህበረሰባዊ ክብር ይጎለብታል። ይህም ለሀገር ዕድገት በጎ አስተዋፅኦ ያደርጋል” የሚል ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

የማህበራዊ ሳይንስ ምሑሩ ብስራት (ዶ/ር) ሴቶችን በኢኮኖሚና ማህበራዊ ጉዳዮች ማብቃት ሀገርን እንደማብቃት ይቆጠራል ብለው፣ መንግስትና ሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በሴቶች ላይ የሚደርሱ ልዩ ልዩ ኢ ፍትሐዊ ድርጊቶችና አሰራሮችን መቅረፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡ የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ከማጎልበትና የስራ አጥነት ችግርን ከመቅረፍ አኳያ የተጀመሩ ስራዎች መጠናከር አለባቸው። በተለይም በክህሎት፣ በፋይናንስ፣ በመስሪያ ቦታና በገበያ ትስስር ረገድ ያሉባቸውን ተግዳሮቶች ደረጃ በደረጃ ለማቃለል የሚያስችሉ የግንዛቤና ንቅናቄ ስራዎችን በስፋት መሥራት ይኖርባቸዋል ሲሉ መክረዋል፡፡

እንደከተማ በጥቃቅን ንግድ ላይ በተለይ በ‘ለነገዋ’ የሴቶች የተሃድሶና ክህሎት ማበልፀጊያ ማዕከል በልብስ ስፌት፣ በሹራብ ስራ እና በሌሎች የእደ ጥበብ ሰራዎች ሰልጥነው ወደ ስራ የተሠማሩ ሴቶች በተለያየ መንገድ ድጋፍና የገበያ እድል እንዲያገኙ ስራዎቻቸውን የሚያቀርቡባቸው ኤግዚብሽንና በዛሮች እንዲመቻችላቸው መደረግ እንዳለበትም ጠቁመዋል፡፡

ከ‘ለነገዋ’ የሴቶች ተሃድሶና ክህሎት ማበልፀጊያ ማዕከል ባገኘነው መረጃ መሰረት፣ ማዕከሉ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ ሴቶች ወደ ማህበረሰቡ በብቃት እንዲቀላቀሉ ከማድረግ አኳያ ቀላል የማይባል አስተዋፅኦ አድርጓል። በዘመናዊ መልክ የተደራጁ የስልጠና ክፍሎች ያሉት ሲሆን፣ በእነዚህም የእድሉ ተጠቃሚ የሆኑ ሴቶች ልብስ ስፌትና ዲዛይን፣ የባህልና ዘመናዊ ልብሶችን የመስፋት ጥበብን ይቀስማሉ። የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር ምግቦች አሰራር፣ የፀጉር ስራና ውበት አጠባበቅ ስራዎች ስልጠና ይሰጣል።

ማዕከሉ የሙያና የህይወት ክህሎት ስልጠና ከመስጠት ባሻገር ለሰልጣኞቹ መጠለያ፣ ምግብ፣ የህክምና አገልግሎት እና ለልጆቻቸው የቀን ውሎ ማቆያ በማዘጋጀትም ሁለንተናዊ ድጋፍ ያደርጋል። ይህም ሴቶቹ ያለ ስጋት በትምህርታቸው ላይ እንዲያተኩሩ ይረዳቸዋል። የተቋሙ አገልግሎት በዚህ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን ሴቶቹ የስልጠና ጊዜያቸውን አጠናቅቀው በሰለጠኑበት ዘርፍ የስራ እድል ከተመቻቸላቸው በኋላም ከገበያ ጋር እንደሚያገናኝም ነው ከተቋሙ ያገኘነው መረጃ የሚያመላክተው፡፡

እንደመረጃው ተቋሙ ስልጠናውን ያጠናቀቁ ሴቶች የስራ እድል እንዲያገኙ ከግል ድርጅቶች ጋር ስምምነት ያደርጋል። በተጨማሪም የጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራትን በማደራጀት የመስሪያ ቦታና የመነሻ ካፒታል እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል። በካዛንቺስ አካባቢ የስራ እድል የተፈጠረላቸው ብቻም ሳይሆኑ ሌሎችም በልብስ ስፌት የሰለጠኑ ሴቶች አሁን የራሳቸውን ሱቅ ከፍተው ቤተሰቦቻቸውን የሚያስተዳድሩ አሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ በትልልቅ ሆቴሎች ውስጥ በምግብ ዝግጅት ስራ ተቀጥረው በማገልገል የተረጋጋ ህይወት እየመሩ ይገኛሉ።

ከዚህ ቀደም በጎዳና ላይ ልጆቻቸውን ይዘው ይሰቃዩ የነበሩ እናቶች፣ ዛሬ ልጆቻቸውን ትምህርት ቤት ልከው ማታ በሰላም የሚገቡበት ቤት እንዲኖራቸው ማዕከሉ መሰረት ሆኗቸዋል። ይህንን በካዛንቺስ ተገኝተን ያነጋገርናቸው እናቶችም ይመሰክራሉ፡፡ ተቋሙ ሴቶችን በክህሎትና በስነ-ልቦና በማነፅ፣ ድህነትንና ማህበራዊ መገለልን ለመዋጋት ትልቅ አቅም መሆኑን በተግባር አሳይቷል። ይህ ተቋም ይበልጥ እንዲጠናከርና መሰል ማዕከላት እንዲስፋፉ ማድረግ፣ በችግር ውስጥ ያሉ ብዙ ወገኖችን ማዳን ነውና የሁሉንም ትኩረት ይሻል፡፡

# ሌላኛው የዲፕሎማሲ እርካብ

**• ኮፕ 32 ኢትዮጵያ በዓለም መድረክ ላይ ያላትን ተሰሚነት እንደሚያሳድግ ተጠቁሟል**

**በአብርሃም ገብሬ**

የአየር ንብረት ለውጥ ዓለም አቀፍ ትኩረት ከሚሰጣቸውና የዘመናችንን ዕጣ ፈንታ ከሚወስኑ ቁልፍ ጉዳዮች አንዱ ነው። የዓለም አቀፉ ማህበረሰብም ተደጋጋሚ ምክክሮችን ከማድረግ ቦዝኖ አያውቅም፤ ምንም እንኳን በሚፈለገው ልክ ውጤት መጥቷል ማለት ባይቻልም። ከእነዚህ መድረኮች መካከል የኮንፈረንስ ኦፍ ፓርቲስ (COP) ጉባኤ አንዱ ነው። ኢትዮጵያም 32ኛውን የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ (COP-32) እንድታዘጋጅ መመረጧ ለሀገሪቱ ትልቅ ክብር ብቻም ሳይሆን አዳዲስ የዲፕሎማሲ ዕድሎችን ይዞ እንደሚመጣ ይጠበቃል፡፡

በወርሃ ህዳር 2018 ዓ.ም በብራዚል ቤሌም የኮፕ-30 የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ ተደርጓል፡፡ በዚህ ጉባኤ ከሁለት ዓመት በኋላም በሺህዎች የሚቆጠሩ ተሳታፊዎች የሚታደሙበትን የ"ኮፕ-32" የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ ኢትዮጵያ እንድታስተናግድ ተመርጣለች፡፡ የአዲስ ልሳን ዝግጅት ክፍልም ኢትዮጵያ ይህን ጉባኤ እንድታዘጋጅ መመረጧ፣ ከዲፕሎማሲ አንጻር ይዞት የሚመጣው ዕድል ምንድን ነው? ይህን ዕድል አሟጥጦ ለመጠቀም ከወዲሁ ሊታሰብባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ምንድ ናቸው? የሚሉ ጉዳዮች ላይ አጭር ዳሰሳ አድርጓል፡፡

## ኮፕ 32 እና ኢትዮጵያ

ኮፕ- 32ን ማስተናገድ ኢትዮጵያ በዓለም መድረክ ላይ ያላትን ተሰሚነት እንደሚጨምረው፣ የውጭ ግንኙነት እና ዓለም አቀፍ ገጽታዋን ወደ ላቀ ደረጃ እንደሚያሳድገው ለዝግጅት ክፍላችን አስተያየታቸውን የሰጡ ምሁራን ተናግረዋል፡፡ የፖለቲካ ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ምሁር ዴያሞ ዳሌ ዴጋ፣ የኢትዮጵያ መመረጥ ያጋጣሚ ወይም የዕድል ጉዳይ እንዳልሆነ ተናግረዋል፡፡ በዚህ ወቅት የሰው ልጆች ህልውና ስጋት ከሆኑ ዓለም አቀፍ ችግሮች መካከል አንዱ የአየር ንብረት ለውጥ መሆኑን ያወሱት ምሁሩ፣ "ኢትዮጵያ ይህን ችግር በሚቀርፉ የመፍትሄ ጉዳዮች ላይ ንቁ ተሳትፎ አድርጋለች፣ እያደረገችም ትገኛለች፡፡ ለአብነትም በየዓመቱ በርካታ ችግኞችን ትተክላለች፡፡ አረንጓዴ አሻራ ፕሮጀክት ላይ በመመስረት ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ኢኮኖሚ ለመገንባት ስትራቴጂ ነድፋ እየሰራችም ነው፡፡ እነዚህ ሥራዎች ደግሞ ዓለም አቀፍ ዕውቅና እያገኙ የመሆናቸው አንዱ ማሳያ ይህን ጉባኤ እንድታዘጋጅ መመረጧ ነው" ብለዋል፡፡

ይህ ጉባኤ በርካታ ሀገራትን የሚያሰባስብና ዓለም አቀፍ ተቋማትን የሚያሳትፍ መሆኑን የተናገሩት ምሁሩ፣ "የጊዜው የሰው ልጅ ህልውና ጥያቄ በመሆኑ ኢትዮጵያ ይህን ዕድል ማግኘቷ በአንድ በኩል የዲፕሎማሲ ድል ነው። በአረንጓዴ አሻራ ላይ እየተሰሩ ያሉ ሥራዎች ዕውቅና ማግኘታቸውን ያሳያል። በሌላ በኩል ደግሞ በቀጣይ በአዲስ አበባ በሚደረገው ዓለም አቀፍ ጉባኤ ላይ



ፎቶ- ከገፀ ድር
ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በኮፕ 32 ጉባኤ ዝግጅት ዙሪያ ከአፍሪካ ህብረት ኮሚሽን ሊቀ መንበር ማህሙድ አሊ የሱፍ ጋር በተወያዩበት ወቅት

የኢትዮጵያን አቋም ለሌሎች ሀገራት ለማስረዳት፣ ተጽዕኖዋንም ይበልጥ ለማሳደግ ቁልፍ ሚና እንደሚጫወት" ተናግረዋል፡፡

በተባበሩት መንግስታት በአስተዳደር፣ ድህነትና ዘላቂ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ የፖሊሲ አማካሪ ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ (ዶ/ር) በዚሁ ጉዳይ ላይ ቀደም ብሎ ለአዲስ ልሳን ዝግጅት ክፍል በሰጡት አስተያየት፣ ጉባኤውን ለማስተናገድ ኢትዮጵያ የተመረጠችው በአፍሪካ ትልቅ የህዝብ ቁጥርና አቅም ካላት ናይጀሪያ ጋር ተወዳድራ ነው፡፡ ለዚህም ያበቃት የአየር ንብረት ለውጥ አጀንዳን ቀዳሚ አድርጋ በመስራቷ ነው። በኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) መሪነት በአረንጓዴ አሻራ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ችግኝ በመትከል የተገኘ ውጤት ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር አዲስ አበባ የአፍሪካ የዲፕሎማሲና የፖለቲካ ከተማ፣ ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን አፍሪካን የምትወክል በመሆኗ ኢትዮጵያ ጉባኤውን የማዘጋጀት እድል እንድታገኝ አድርጓታል ብለዋል፡፡

ይህንን ጉባኤ ለማዘጋጀት በኢትዮጵያ በኩል የሚደረገው ዝግጅት፤ ለተሳታፊዎች የተሻለ አገልግሎት ማቅረብ እና የመንግስት ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ ዝግጁነትን ማሳደግ ነው። በቀጣይ የአየር ንብረት ለውጥ ላይ የሚሰሩ ዓለም አቀፍ ተቋማት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚቋቋሙበትና ጥናትና ምርምር የሚደረግበት ሁኔታ እንደሚፈጥር ቆስጠንጢኖስ (ዶ/ር) አክለዋል፡፡

ኢትዮጵያ ለአስተናጋጅነት መመረጧ፣ ከራሷም አልፎ የአፍሪካን ወሳኝ ፍላጎቶች በባለቤትነት ይዛ ለማቅረብ ትልቅ አጋጣሚ እንደሆነ የፖለቲካ ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ምሁር ዴያሞ አብራርተዋል፡፡ ምሁሩ አክለውም አዲስ አበባ እያከናወነቻቸው ያሉ የልማት ሥራዎች እንደ ኮፕ 32 ያሉ ታላላቅ ጉባኤዎችን ለማዘጋጀት አቅም እየፈጠረላት መሆኑንም ተናግረዋል፡፡

ኮፕ 32ን ምክንያት በማድረግ የበርካታ ሀገራት የመንግስት ከፍተኛ ባለስልጣናትና ከፍተኛ የዓለም አቀፍ ተቋማት ኃላፊዎች ወደ አዲስ አበባ ይመጣሉ። ይህም አዲስ አበባ እንደ አፍሪካ የዲፕሎማሲ መቀመጫነቷ የዓለምን ትኩረት በላቀ ደረጃ እንድትስብ ያደርጋል። የኮፕ ጉባኤ ከዚህ ቀደም ያዘጋጁ ሀገራትን ተሞክሮ መነሻ በማድረግ፣ ጉባኤው ለኢትዮጵያ መልከ ብዙ ዕድሎችን ይዞ እንደሚመጣ ይጠበቃል፡፡

የኮፕ ጉባኤዎች ለአየር ንብረት ለውጥ የሚውለውን የገንዘብ ድጋፍ የሚወስኑ ዋና መድረኮች ናቸው። ኢትዮጵያ የአረንጓዴ ኢኮኖሚ እቅዷን በማጉላት፣ ለትግበራ የሚያስፈልገውን ዓለም አቀፍ የገንዘብና የቴክኖሎጂ ድጋፍ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከወዲሁ በማዘጋጀት የመጠየቅና የማስፈጸም ዕድል ይኖራታል። እንዲሁም የአፍሪካን አጠቃላይ አቋም ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም ጋር በማሰናሰል የመሪነት ሚና መወጣት ትችላለች፡፡ ይህን ሚና በአግባቡ ለመወጣት ከወዲሁ ዝግጅቶች እየተካሄዱ እንዳለ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡

በቅርቡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ኢትዮጵያ እና የአፍሪካ ህብረት አፍሪካን በሚገባ የሚወክል ኮፕ 32 ጉባኤ ለማዘጋጀት እንዴት ተቀራርበው መስራት እንደሚችሉ ከአፍሪካ ህብረት ኮሚሽን ሊቀ መንበር እና ከቡድናቸው ጋር ውይይት አድርገዋል፡፡ በአፍሪካ ህብረት ኮሚሽን ሊቀ መንበር ማህሙድ አሊ የሱፍ መሪነት የአፍሪካ ህብረት ኮሚሽን ኮፕ- 32ን የተሳካ ለማድረግ የኢትዮጵያ ቁልፍ አጋር ለመሆን ቁርጠኛ መሆናቸው ጠቅላይ ሚኒስትሩ በማህበራዊ የትስስር ገጻቸው አስፍረዋል፡፡

**ኢትዮጵያ ይህን ዕድል ማግኘቷ በአረንጓዴ አሻራ ላይ እየተሰሩ ያሉ ሥራዎች ዕውቅና ማግኘታቸውን ያሳያል። በሌላ በኩል ደግሞ በቀጣይ በአዲስ አበባ በሚደረገው ዓለም አቀፍ ጉባኤ ላይ የኢትዮጵያን አቋም ለሌሎች ሀገራት ለማስረዳት፣ ተጽዕኖዋንም ይበልጥ ለማሳደግ ቁልፍ ሚና ይጫወታል**

የአዲስ አበባ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤም ባለፈው ሳምንት በሁለተኛው ምዕራፍ የኮሪደር ልማት ፕሮጀክት ከኡራኤል እስከ ብራስ፣ ከቦሌ መድኃኔዓለም- ጎላጎል እስከ እንግሊዝ ኤምባሲ የሚዘልቀውን የኮሪደር ልማት ፕሮጀክት እና የፒኮክ (ማዕከላዊ) ፓርክ ግንባታን እንቅስቃሴ በመስክ በጎበኙበት ወቅት "ኢትዮጵያ የዓለምን ትኩረት የሚስበውን የኮፕ 32 ጉባኤ የምታስተናግድ መሆኗ እድለኛ..." መሆኗን በመግለጽ፣ ለጉባኤው ከወዲሁ ዝግጅቶች እየተደረጉ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ በኮሪደር ልማቱ የአደይ አበባ ስታዲየም ግንባታ የሚከናወንበት አካባቢ አንዱ ጉባኤው የሚካሄድበት ማዕከል በመሆኑ አስቀድመዉ የተጀመሩ የኮሪደርና ሌሎች መሠረተ ልማት ግንባታዎች በፍጥነትና በጥራት እንዲከናወኑ እየተሰራ እንደሆነም ጠቁመዋል፡፡

ከንቲባዋ በማህበራዊ ትስስር ገፃቸው ባሰፈሩት መልእክት፣ "የኮፕ 32 ጉባኤ ከዓለም ዙሪያ በርካታ ቁጥር ያላቸው ተሳታፊዎች የሚታደሙበት በመሆኑ፣ ጉባኤው በአዲስ አበባ መዘጋጀቱ ከሀገር መልካም ገፅታ ግንባታ በተጨማሪ በንግድ፣ በኢንቨስትመንት፣ በሥራ ዕድል ፈጠራ፣ በገበያ ትስስር እንዲሁም መሰል ዓለም አቀፍ ኩነቶችን ወደ ሀገራችን በቀጣይነት ለማምጣት ጉልህ አስተዋፅኦ ይኖረዋል።

መላው የከተማችን ነዋሪዎችና የንግዱ ማህበረሰብ በተሰማራንበት የሥራ መስክ ጉባኤው ይዞት የሚመጣውን መልካም ዕድል አሟጠን እንድንጠቀም፣ ለጉባኤው ስኬታማነትም ከወዲሁ ሁላችንም ዝግጅት እንድናደርግ" ሲሉም ጥሪ አቅርበዋል፡፡

የኮፕ 32 ጉባኤን በአዲስ አበባ ማስተናገድ ለኢትዮጵያ ታላቅ የዲፕሎማሲ ዕድል እንደሆነ ለዝግጅት ክፍላችን አስተያየታቸውን የሰጡ ምሁራን በአጽንኦ ተናግረዋል፡፡ ኢትዮጵያ የዓለም መሪዎችን በመሰብሰብ የአፍሪካን አጀንዳ በመያዝ የመሪነት ሚና የምትጫወትበት እንደሚሆን የሌሎችን ሀገራት ተሞክሮ መነሻ በማድረግ አብራርተዋል፡፡ የሀገር ገጽታዋን በማሳደግ እና ለኢኮኖሚ ልማት የሚያግዙ ስምምነቶችን በመፈረም ከዚህ ጉባኤ ከፍተኛውን የዲፕሎማሲ፣ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ትርፍ ልታገኝ እንደምትችልም ጠቅሰዋል። ይህ ጉባኤ እንዲሳካ ከወዲሁ የተለያዩ ሥራዎች እየተሰሩ መሆኑን በመጥቀስ፣ የአገልግሎት ተቋማት ለዓለም አቀፉ ጉባኤ በሚመጥን መልኩ አገልግሎት እንዲያቀርቡ ከወዲሁ የአቅም ግንባታ ሥራዎች መሰራት እንዳለባቸው አሳስበዋል፡፡ በእርግጥ ጉባኤው በተሳካ ሁኔታ በመዲናዋ ተደርጎ እንዲጠናቀቅ የማድረግ ሥራ ለመንግስት ብቻ የሚተው አይደለም፡፡ የግል ዘርፉና የከተማዋ ነዋሪዎችም የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

# አገልግሎትን ... ከገጽ 1 የዞረ



ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

አቶ ፍትህአወቅ አሰፋ በየካ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት የኢ-ካርታ አገልግሎት ሲያገኙ

በአግባቡ መጠቀም ችያለሁ፡፡” ይላሉ በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ ሁለት ነዋሪ የሆኑትና ካርታቸውን ወደ ኢ-ካርታ (ኤሌክትሮኒክስ ካርታ) ለማስቀየር መጥተው ያገኘናቸው አቶ ፍትህአወቅ አሰፋ፡፡

አቶ ፍትህአወቅ በአገልግሎቱ ደስተኛ እንደሆኑና በተለይ ሰራተኞች በቅንነት ተቀብለው በትዕግስት እንዳስተናገዷቸው ተናግረዋል፡፡ ከዚህ ባሻገር ሲስተሙ ላይ የሚታየውን መጓተት መቅረፍ እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡

ሌላኛው ከቂርቆስ ክፍለ ከተማ አገልግሎት ሊያገኙ መጥተው ያነጋገርናቸው አቶ ተመስገን ሰፊው ይባላሉ፡፡ እሳቸውም የኢ-ካርታ አገልግሎት ለማግኘት ነበር የተገኙት። “ከዚህ ቀደም በመሬት ዘርፍ ሲሰጥ የነበረው አገልግሎት አድካሚና ወረፋ የሚበዛበት ነበር፡፡ አሁን ላይ ግን አገልግሎቱ በቴክኖሎጂ ታግዞ የሚሰጥ በመሆኑ ጥሩና ቀልጣፋ የሚባል መስተንግዶ በአጭር ጊዜ አግኝቻለሁ፤ ጊዜና ወጪዬን ቆጥቦልኛል፤ አሁን በቶሎ ወደ ታክሲ ስራዬ እመለሳለሁ” ብለዋል፡፡

አቶ ተመስገን እንደገለፁት፣ አገልግሎቱ በሲስተም የታገዘ በመሆኑ የተገልጋዩን ምልልስ መቀነስ አስችሏል፡፡ በስልክ በሚደርሳቸው መልእክት መሰረት ጉዳያቸውን ተከታትለው ክፍያ ሲከፍሉ ቆይተው የኢ-ካርታ (ኤሌክትሮኒክስ ካርታ) አገልግሎት አግኝተዋል፡፡

አቶ ይድነቃቸው በንቲ በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 1 ነዋሪ ናቸው፡፡ ቤት ገዝተው በስማቸው እንዲመዘገብላቸው የስም ዝውውር አገልግሎት ለማግኘት ተገኝተው ነበር ያገኘናቸው፡፡ አገልጋዮች ባላቸው አቅም በቅንነት አገልግሎት ለመስጠት ጥረት የሚያደርጉ ቢሆንም ሲስተሙ ላይ ችግር እንዳለ ያነሳሉ። ይህንንም ሲያብራሩ፣ “ከዚህ በፊት የስም ዝውውር ይሰጥበት በነበረው ‘ዞካ’ ሲስተም ሂደቶችን ጀምሬ በመሐል አገልግሎቱ ተቋርጦ ቆይቶ አሁን በአዲስ ሲስተም አገልግሎት እየተሰጠ ይገኛል። ነገር ግን አገልግሎቱ አርኪ አይደለም። በአሮጌው ሲስተም የስም ዝውውር ለማድረግ በተለያየ ሰው የቴሌ ብር አካውንት ለስም ዝውውር የፈፀምኳቸው ክፍያዎች የነበሩ ቢሆንም አሁን በአዲሱ ሲስተም መካተት አልቻሉም፡፡ የከፈልኩበትን ደረሰኝ እንደገና እንዳመጣም ተጠይቄያለሁ” ሲሉ በአገልግሎቱ ደስተኛ አለመሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

አቶ ዳዊት ሀይሌ በየካ ክፍለ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ጽህፈት ቤት የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ባለሙያ ናቸው፡፡ እሳቸው እንደሚናገሩት፣ በተቋሙ ሁሉም አገልግሎት በኦንላይን እየተሰጠ ይገኛል፡፡ ተገልጋዮች ወደ ተቋሙ ገፀ ድር በመግባት በመመዝገብና ማመልከቻ ማቅረብ አገልግሎት ያገኛሉ፡፡ አቅመ ደካማና ኢንተርኔት ቤት ከፍለው መመዝገብ የማይችሉ ተገልጋዮችም በቢሮው ተመዝግበው የአገልግሎቱን ሂደት በስልክ መልእክት እየተላከላቸው ይከታተላሉ፡፡ የአገልግሎት ክፍያ፣ የመሀንዲስ ቀጠሮ፣ ያልተያያዘ ወይም የጎደለ ሰነድ ካለና ተቀባይነት ከሌለው እንዲሁም ሌሎች ሂደቶች በስልክ መልእክት ይደርሳቸዋል፡፡

አገልግሎቱ በቴክኖሎጂ በመሰጠቱ በማንዋል ይሰጥ ከነበረው ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ ልዩነት እንዳለው አቶ ዳዊት ያስረዳሉ፡፡ የሌብነትና የሰነድ መጥፋት ችግርን ይቀርፋል፡፡ በሲስተም በመሆኑ የወረቀት ምልልስን አስቀርቷል፤ ምክንያቱም ፋይሎች ስካን ተደርገው ገብተዋል፡፡

ከዚህ ቀደም የመሬት ነክ አገልግሎቶች ሲሰጡ የነበረው “ዞካ” በተሰኘ ተቋም የለማ ነበር፡፡ ከሁለት ወር በፊት የኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስትቲዩት ባለማው ሲስተም አገልግሎት መስጠት ጀምሯል፡፡ በአዲሱ ሲስተም ኢ-ካርታ ለመውሰድ 15 ቀን ወይም በዛ ቢባል 20 ቀን ብቻ ነው የሚወስደው። ከዚህ በፊት ግን ተደጋጋሚ የሲስተም መቆራረጥ ያጋጥም ነበር፡፡ ለአንድ ቀን ብቻ ሳይሆን አንድ ወር ድረስ ሲስተም ተቋርጦ የሚቆይበት ጊዜ ነበር፡፡ አዲሱ ሲስተም ከተጀመረ በኋላ የሲስተም መቆራረጥም ሆነ መዘግየት እንደሌለ ባለሙያው ይናገራሉ፡፡

ከስም ዝውውር አገልግሎት ጋር በተያያዘ ከተገልጋይ የተነሳውን ችግር በተመለከተም፣ አንዳንድ ተገልጋዮች በአሮጌው ሲስተም ኢ-ካርታ ለማግኘት ክፍያ ፈፅመው ሊወስዱ ሲሉ ነው ሲስተሙ የተቋረጠው፡፡ እነዚህ ተገልጋዮች የከፈሉበትን ደረሰኞች ይዘው በመምጣት አዲሱ ሲስተም ላይ መረጃቸው እንዲያያዝ ይደረጋል፤ ሁለተኛ ክፍያም አይከፍሉም ብለዋል፡፡

በየካ ክፍለ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ፅህፈት ቤት ኃላፊ አቶ መልካሙ ተገኝ ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፁት፣ የመሬት ልማትና አስተዳደር አገልግሎቶችን ለማዘመን በኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት የለማው ሲስተም ወደ ስራ ከገባ ጀምሮ የተቀላጠፈ አገልግሎት እየተሰጠ ይገኛል። አዲሱ ሲስተም ወደ ስራ ከገባ አንድ ወር የሞላው ሲሆን ረጅም ጊዜ ሲወስዱ የነበሩ አሰራሮችንና አገልግሎቶችን በማሳጠር ባለጉዳዮች በአጭር ጊዜ አገልግሎቱን እንዲያገኙ አስችሏል። ለምሳሌ፡- የኢ-ካርታ አገልግሎት ባለጉዳዮች ጥያቄ ካቀረቡ በኋላ የመረጃ ስህተት እንዳያጋጥም የተሰራውን ኢ-ካርታ መጨረሻ ላይ ትክክል መሆን አለመሆኑን እንዲያዩት ተደርጎ ታትሞ ይሰጣቸዋል። ከዚህ በፊት ግን ባለጉዳዮች ‘ካርታው ላይ እንዲህ ዓይነት ችግሮች አሉ፤ አልተስተካከለም’ በሚል ይመላለሱ ነበር፡፡ አዲሱ ሲስተም ይህን በመቅረፍ ቀልጣፋ አገልግሎትና ብዙ ተገልጋዮችን ማስተናገድ አስችሏል፡፡

ባለጉዳዮች አገልግሎት ለማግኘት በኦንላይን ጥያቄ ካቀረቡ በኋላ በማግስቱ በሲስተም መጫን የሚቻልበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ለምሳሌ የኢ-ካርታ አገልግሎት ከዚህ ቀደም አንድ ወርና ከዚያ በላይ ጊዜ ይወሰዳል፡፡ በአዲሱ ሲስተም ባለጉዳዮቸ መረጃዎችን ካሟሉ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ አገልግሎት እንደሚያገኙ አቶ መልካሙ ተናግረዋል፡፡

ከስም ዝውውር ጋር በተያያዘ አንድ ተገልጋይ ያነሱትን ጥያቄ በተመለከተ አቶ መልካሙ ሲመልሱ፤ ተገልጋዩ በቀድሞ ሲስተም ክፍያ ከፈፀሙ ድጋሜ እንዲከፍሉ አይጠየቁም፤ በቴክኒክ ረገድ የገጠማቸው ችግር ካለም እንደሚታይና በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ባለሙያዎች ድጋፍ እንደሚደረግላቸው ጠቁመዋል፡፡

ከሲስተም መዘግየት ጋር በተያያዘም ሲስተሙ ፈጣን አገልግሎት መስጠት የሚያስችል መሆኑን አቶ መልካሙ አንስተዋል፡፡ ከዚህ ቀደም በነበረው ሲስተም 1 ሺህ 297 ፋይሎችን ወደ ሲስተም ለማስገባት (upload) ወራትን ይወስድ የነበረው በአዲሱ ሲስተም ግን በአንድ ወር ጊዜ በመጫን ወደ ባለሙያዎች እንዲደርስ እና ተገልጋዮች አገልግሎቱን እንዲያገኙ መደረጉን አቶ መልካሙ ጠቁመዋል፡፡

በአዲስ አበባ የመሬት ልማትና አስተዳደር ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ተቋማት አገልግሎቶችን በቴክኖሎጂ በማስደገፍ ፈጣንና ቀልጣፋ ለማድረግ እየተሰራ ይገኛል፡፡ በማዕከል ደረጃ ከሚሰጠው የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል አገልግሎት በተጨማሪ በቅርቡ በቦሌ ክፍለ ከተማ ተጨማሪ ቅርንጫፍ በመክፈት አገልግሎቶችን በአንድ ማዕከል በቴክኖሎጂ በመታገዝ እየተሰጠ ነው፡፡

እነዚህን ለአብነት አነሳን እንጂ እንደ የንግድ ቢሮ፣ የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን፣ የኢንቨስትመንት ኮሚሽንና ሌሎች በርካታ ተቋማት አገልግሎቶችን በቴክኖሎጂ አስደግፎ በመስጠት የተገልጋዮችን እንግልትና እሮሮ መቀነስ እንደተቻለ ለዝግጅት ክፍላችን በተለያየ ጊዜ አስተያየታቸውን ከሰጡ ተገልጋዮች መረዳት ይቻላል፡፡

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

## ምን ልርዳዎ?

### አገልግሎት አሰጣጡን ከሚያሳለጡ ቴክኖሎጂዎች ጥቂቶቹ

የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥን ፈጣንና ቀልጣፋ ለማድረግ ቴክኖሎጂ ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር የሚገኙ የመንግስት ተቋማትም በቴክኖሎጂ በመታገዝ ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት በትኩረት እየተሰሩ ይገኛል፡፡ በቅርቡ ለምተው ወደ ስራ ከገቡ እና አገልግሎት አሰጣጡን ከሚያቀላጥፉ ሲስተሞች ወይም ቴክኖሎጂዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

- **የአምራች ኢንዱስትሪ የተቀናጀ አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት** (Integrated Industry Management Information System)፡- ይህ በቅርቡ ወደ ስራ የገባ አንዱ ስርዓት ሲሆን በአዲስ አበባ ከተማ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ የለማ ነው፡፡ ቴክኖሎጂው የአምራች ኢንዱስትሪዎችን ከምዝገባ እስከ ምርት ያለውን መረጃ አካትቶ የያዘ ነው፡፡ አምራች ኢንዱስትሪዎች በኦንላይ መረጃ እንዲያገኙ እንዲሁም የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር የገበያ ትስስር ለመፍጠር የሚያስችል ነው፡፡
- **አዲሱ የተቀናጀ የሲቪል ምዝገባና የነዋሪነት አገልግሎት ዲጂታል ስርአት** (Civil Registration and Vital Statistics with e-ID)፡- በቅርቡ በአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ተመርቆ ወደ ስራ የገባ ቴክኖሎጂ ነው፡፡ ሲስተሙ በኢትዮጵያ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት የበለጸገ ነው፡፡ ባለጉዳዮች የሞባይል ስልካቸውን እና የተለያዩ የቴክኖሎጂ አማራጮችን በመጠቀም በአካል ሳይገኙ ባሉበት ሆነው አገልግሎት እንዲያገኙ ያስችላል፡፡ የሚከሰቱ ወሳኝ ኩነቶችን በወቅቱ መመዝገብ በሚቻልበት ሁኔታ ከኢሚግሬሽን፣ ከጤና፣ ከፍርድ ቤት እና ከሌሎችም ተቋማት ቅንጅት እና መናበብን ይፈጥራል። ከብሔራዊ መታወቂያ ጋር የተሳሰረ እና የተናበበ አገልግሎት መስጠት የሚያስችልም ነው፡፡
- **ፖርታል፡-** በከተማ አስተዳደሩ ስር ያሉ የቀዳማይ ልጅነት ፕሮግራም (ECD) የህፃናት ማቆያ እለታዊ፣ ወርሃዊና ዓመታዊ ሪፖርት የሚያሳይ ፖርታል በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ለምቶ ወደ ስራ ገብቷል፡፡

**ምንጭ፡-** የአዲስ አበባ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ እና የሲቪል ምዝገባና የነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ የማህበራዊ ትስስር ገፆች

## ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ የሚቀርብ

# ስለቤተሰብ ህግ ምን ያህል ያውቃሉ?

**የኃላሸት ወሰኔ(ዓቃቤ ህግ)**



በተሻሻለው የፌደራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አባትነትን እና እናትነትን ስለማወቅ በምዕራፍ ዘጠኝ ላይ ከአንቀጽ 123 እስከ 179 ድረስ በሰፊው ደንግጎ እናገኛለን፡፡ በዚህ መሰረትም የቤተሰብ ህጉ ሦስት አባትነትን የማወቂያ መንገዶችን ይዘረዝርልናል፡፡

### 1. አባትነት በህግ ግምት

የቤተሰብ ህጉ ሁለት አይነት ግንኙነቶችን እውቅና ይሰጣቸዋል፤ እነሱም ጋብቻ(ባልና ሚስት) እና እንደ ባልና ሚስት ናቸው፡፡ አባትነት በህግ ግምት የሚታወቀው ከእነዚህ ሁለት ተቋማት መካከል በአንዱ ልጅ በሚወለድበት ጊዜ ነው፡፡ ይህ ማለት ልጅ በሚፀነስበት ወይም በሚወለድበት ጊዜ በእናትየዋና በአንድ ወንድ መካከል በህግ የታወቀ ግንኙነት መኖሩ በመረጋገጡ ምክንያት አባትነት ይታወቃል፡፡

### 1.1. ጋብቻ

በጋብቻ ውስጥ ልጅ በሚፀነስበት ወይም በሚወለድበት ጊዜ ባልየው የልጁ አባት መሆኑን የህግ ግምት ይወሰዳል (አንቀፅ 126)፡፡ የልጁ የልደት ምስክር ወረቀት ባልየው አባት ያለመሆኑን ወይም የልጁ አባት ሌላ ሰው መሆኑን የሚያመለክት ቢሆንም እንኳን፣ የልደት ምስክር ወረቀቱ እንዲታረም ይደረጋል (አንቀጽ 127)፡፡ ይህ ማለት የልጁ የምስክር ወረቀት ላይ በአባትነት የተመዘገበው ሰው ሌላ ቢሆንም እንኳን ጋብቻ ውስጥ ያለው (ባል) አባት እንደሆነ ህጉ ግምት ይወስዳል ስለዚህ የልደት ምስክር ወረቀቱን በህግ ግምት መሰረት እንዲስተካከል ይደረጋል። ጋብቻው ከተፈፀመ ከ180 ቀናት በኋላ ወይም ጋብቻው በፈረሰ በ300 ቀናት ውስጥ የተወለደ እንደሆነ ልጁ በጋብቻው ውስጥ እንደተፀነሰ ይቆጠራል(አንቀጽ 128)።፡ በዚህ መሰረት ጋብቻ ከተፈፀመ ከ180 ቀናት በፊት ወይም ጋብቻ ከፈረሰ ከ300 ቀናት በኋላ ከተወለደ፣ ልጁ ከጋብቻ ውጭ እንደተፀነሰ ይቆጠራል፡፡

### 1.2. እንደባልና ሚስት

ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብረው በሚኖሩበት ጊዜ የተፀነሰ ወይም የተወለደ ልጅ አባት በዚሁ ግንኙነት ከእናትየዋ ጋር አብሮ የሚኖረው ሰው ነው (አንቀጽ130)፡፡ ከላይ እርግዝናው ስለሚቆይበት ጊዜ የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደባልና ሚስት ተቋም ውስጥ ለሚወለድ ልጅ የህግ ግምት ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

### 2. ልጅነትን መቀበል

በህግ ግምት የልጁን አባት ለማወቅ ካልተቻለ ወይም ልጅ በሚፀነስበት ወይም በሚወለድበት ጊዜ በእናትየዋና በአንድ ወንድ መካከል በህግ የታወቀ ግንኙነት መኖሩ ማረጋገጥ ካልተቻለ አባትየው ልጁን ልጄ ነው ሲል በመቀበል አባትነት ሊታወቅ ይችላል፡፡ ይህ ማለት በህግ ግምት አባትነት ከታወቀ ልጅነትን መቀበል የሚለው ተፈፃሚ አይሆንም። በህግ ግምት አባትነት ሊታወቅ የማይችልበት ሁኔታ በሚፈጠርበት ጊዜ አባት ነኝ የሚል ግለሰብ የተፀነሰ ወይም የተወለደ ልጅ ልጄ ነው ሲል በመቀበሉ ምክንያትም አባትነት ይታወቃል(አንቀፅ 131 እና 132)፡፡

ስርዓቱን በምንመለከትበት ጊዜ አንድ ሰው በክብር መዝገብ ሹም ፊት በመቅረብ አባት መሆኑን በመግለፅ በሚሰጠው ቃል ወይም በፅሑፍ በሚደረገው ኑዛዜ ወይም በሌላ በማናቸውም ስልጣን በሰጠው ባለስልጣን በተረጋገጠ ሰነድ አማካይነት አባት መሆኑን በመግለፅ ልጅነትን ለመቀበል ይችላል (አንቀፅ 133)፡፡ ስለዚህ አባት መሆኑን መግለፅ የሚፈልግ አንድ ሰው በክብር መዝገብ ሹም ፊት በመቅረብ በቃል፣ በጽሑፍ በሚደረግ ኑዛዜ ወይም ስልጣን በተሰጠው ባለስልጣን በተረጋገጠ ሰነድ አማካይነት አባትነቱን መግለጽ ይችላል፡፡

አካለ መጠን ያልደረሰ ቢሆንም እንኳን ልጄ ነው ሲል ቃል ለመስጠት የሚችለው አባት ብቻ ነው፡፡ ቃሉን ሌላ ሰው እንዲሰጥለት ማድረግ የሚችለው በፍርድ ቤት የፀደቀ ልዩ የውክልና ስልጣን በመስጠት ብቻ ይሆናል፡፡ በፍርድ ቤት የተከለከለ ሰውን በተመለከተ ቃሉን በራሱ ወይም ፍርድ ቤት ሲፈቅድ በእርሱ ስም በህጋዊ ወኪሉ አማካይነት ሊሰጥ ይችላል (አንቀፅ 134)፡፡ የልጁ አባት የሞተ ወይም ፈቃዱን ለመስጠት የማይችል በሆነ ጊዜ፣ ከአባትየው ወላጆች አንዱ በእርሱ ስም ልጁን ሊቀበል ይችላል፡፡

የልጁ እናት የተቀባዩን አባትነት እውነት ያለው መሆኑን ካላመነች በስተቀር አባት ልጄ ነው ሲል የሚሰጠው ቃል በህግ ፊት ውጤት አይኖረውም። የልጁ እናት በህይወት የሌለች ወይም ፈቃዷን ለመግለፅ የማትችል ሆና የተገኘች እንደሆነ፣ የእምነት ቃሉ ከልጁ እናት ወላጆች በአንደኛው ሊሰጥ ይችላል (አንቀፅ 136)፡፡ ልጁ አካለ መጠን ከደረሰ በኋላ ከሆነ አባት ልጅነትን የተቀበለው አባት ልጁን መቀበሉ ውጤት የሚያገኘው ልጁ አባትነቱን የተቀበለ እንደሆነ ነው (አንቀፅ 138)፡፡ ልጅነትን የመቀበል ተግባር ልጁ ሞቶ ከሆነ ልጅየው ወደታች የሚቆጠሩ ተወላጆችን ተክቶ ካልሞተ በስተቀር ልጅነቱን አውቆ መቀበል አይቻልም፡፡ በተጨማሪም ልጄ ነው ሲል አባት የሰጠውን ቃል መሻር አይችልም፡፡

### 3. በፍርድ ቤት የአባትነት ውሳኔ

አባትነት በህግ ግምት እና ልጅነትን በመቀበል መታወቅ ካልተቻለ ወይም የተከዳ እንደሆነ በፍርድ ቤት ውሳኔ አባትነት ሊረጋገጥ ወይም ሊታወቅ ይችላል፡፡ ይህ ማለት ከላይ በጠቀስናቸው አባትነትን የማወቂያ መንገዶች በአንዱ አባትነት ከታወቀ ወደ ፍርድ ቤት ውሳኔ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡ በዚህ መሰረትም አባትነት ምን አይነት ሁኔታዎች ሲሟሉ በፍርድ ቤት ውሳኔ እንደሚረጋገጥ የቤተሰብ ህጉ በግልጽ ይደነግጋል፡፡ እነሱም፡-

- ልጁ በተፀነሰበት ጊዜ በእናቲቱ ላይ የመደፈር ወይም የመጠለፍ ተግባር የተፈፀመባት ሲሆን፣
- ሆን ተብሎ በተደረገ የተንኮል ድርጊት፣ ስልጣንን ያለአግባብ በመጠቀም፣ አገባሻለሁ ሲል የተስፋ ቃል በመስጠት ወይም በሌላ ተመሳሳይ መንገድ ልጁ በተፀነሰበት ጊዜ በእናቲቱ ላይ ማሳት ተግባር የተፈፀመባት ሲሆን፣
- አባት ነው በተባለው ሰው የተጻፉና በማያሻማ ሁኔታ አባትነቱን የሚያረጋግጡ ደብዳቤዎች ወይም ሌሎች ጽሑፎች ሲኖሩ፣
- በህግ የታወቀ ግንኙነት ሳይኖራቸው የልጁ እናትና አባት የተባለው ሰው በህግ በተመለከተው የእርግዝና ጊዜ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ በግብረ ስጋ ግንኙነት አብረው የኖሩ እንደሆነ፣
- አባት ነው የተባለው ሰው ልጁን በመንከባከብ ወይም በማስተማር ወይም በማሳደጉ ላይ እንደአባት በመሆን የተሳተፈ እንደሆነ፡፡

### አባትነትን በመወሰን ላይ ስለሚኖረው የህግ ግጭት

ከዚህ በላይ የተመለከቱትን አባትን የማወቂያ መንገዶችን ተፈፃሚ በማድረግ አንድ ልጅ ከአንድ በላይ አባቶች አሉት ከተባለ የልጅ አባትነት በህግ በሚሰጣቸው ሰዎች መካከል በሚደረግ ስምምነት ሊወሰን ይችላል (አንቀፅ 147)። ይህ ማለት አንድ ልጅ ሁለት አባቶች አሉት ከተባለ ሁለቱ አባቶች ስምምነት በመፈፀም በሶስት ምስክሮች በማረጋገጥ እና ፍርድ ቤት እንዲያፀድቀው በማድረግ መስማማት ይቻላል፡፡ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ካላጋጠመ በስተቀር የልጁን እናት ቃል መስማት ይገባል(አንቀፅ 147)፡፡ ስለአባትነት በሚደረገው ክርክር ስምምነት ያልተገኘ እንደሆነና አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባል ከሚኖር ሰው ይልቅ፣ ህጋዊው ባል ይመረጣል እና ልጁ በተፀነሰበት ጊዜ ከነበረው ባል ወይም ከሴትየዋ ጋር አብሮ ይኖር ከነበረው ሰው ይልቅ እናቲቱ ልጁን ስትወልድ የነበራት ባል ወይም አብሮ የሚኖር ሰው የልጁ አባት ነው ማለት ይገባል፡፡ አባትነትን በስምምነት የመወሰን ወይም የማስተላለፍ ድርጊት ሊሻር አይችልም፡፡

### መካድ

በአባት በኩል ያለን መወለድ መቃወም የሚቻለው የመካድ ክስ በማቅረብ ብቻ ነው (አንቀጽ 167)፡፡ የልጁ አባት ነህ ተብሎ በህግ አባትነት የሚሰጠው ሰው ልጁ ከመወለዱ በፊት በ180ኛው እስከ 300ኛው ቀናት መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ ከልጁ እናት ጋር የሩካቤ ስጋ ግንኙነት ላለመፈፀሙ በማያጠራጥር ሁኔታ ያስረዳ እንደሆነ የተባለውን ልጅ ልጄ አይደለም ለማለት ይችላል (አንቀጽ 168)፡፡ አባትነትን ፈቅዶ የተቀበለ እና በፍርድ ቤት ውሳኔ አባት ነህ የተባለው ሰው ወይም ከዚሁ ሰው መብቱ የተላለፈለት ሰው የመካድ ክስ ለማቅረብ ህግ አይፈቅድለትም፡፡

# ለጋራ ትርክት መሰረት የሚጥሉ አሻራዎች

- በአዲስ አበባ ኮሪደርን ጨምሮ በተለያየ ልማት ላይ እየተካተቱ ያሉ ጥበባዊ ስራዎች ለአሰባሳቢ ትርክት አጋዥ መሆናቸው ተገልጿል

**በስንታየሁ ምትኩ**



ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

በአራዳ ፓርክ ከሚገኙት የጥበብ ሰራዎች መካከል ለዓድዋ ድል መገኘት አስተዋፅዖ የነበራቸውን ኢትዮድያውያን የሚዘክሩት ተጠቃሾች ናቸው

አቶ ደጀኔ ቶላ የካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 4 ነዋሪ ናቸው፡፡ ለዓይን ማራኪ ሆኖ በተገነባው "የአራዳ ፓርክ" የተሰራውን ልማት በአግራሞት እየተመለከቱ ነበር ያገኘናቸው፡፡ "በአዲስ አበባ በጥቂት ዓመት እንዲህ ዓይነት ስራ መሰራቱ ተአምራዊና አስደማሚ ነው፤ የተሰሩት ነገሮች ታይተው የሚጠገቡ አይደሉም። የወንዝ ዳርቻው ከመዝናኛነት ባሻገር ለከተማዋ ገቢ ያስገኛል፡፡ ታሪካዊ ምልክቶችና ሀብቶችን፣ የተለያዩ ዕፅዋቶች፣ ልጆችንና አረጋዊያንን ታሳቢ ያደረጉ መዝናኛዎችን አካትቶ የተሰራ በመሆኑ ለህብረተሰቡና ለከተማዋ ትልቅ ስጦታ ተደርጎ የሚወሰድ ነው" ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በወንዝ ዳርቻው ታሪክን የሚያስታውሱ ሐውልቶች ለምሳሌ የዓድዋ ዘማቾችን የሚያሳየው ለትውልዱ ልዩ ትርጉም ያለው መሆኑን የሚናገሩት አቶ ደጀኔ፣ "ታሪካችንን በልዩ መልክ እንዲታይ፣ እንዲዳሰስና ለትውልድ መማሪያ እንዲሆን የሰሩ እጆች ምስጋና ይገባቸዋል፡፡ በዓድዋ ጦርነት አባቶቻችንና እናቶቻችን በባዶ እግራቸው ረጅም ርቀት በመጓዝ፣ ባህላዊ የጦር መሳሪያ ይዘው፣ በአጋሰስ ስንቅና ትጥቅ ጭነው ላብና ደማቸውን አፍስሰው፣ አጥንታቸውን ከስክሰው፣ ደክመው ሀገርን አስረክበዋል፡፡ የአሁኑ ትውልድ ልማቱን በማፋጠን የእነሱን አሻራና ታሪክ እየመዘገቡ ማስቀመጥ ትልቅ ፋይዳ አለው፡፡" ብለዋል፡፡

በዓድዋ የተለያየ ቋንቋ፣ እምነት፣ ባህል፣ አመለካከት ያላቸው ኢትዮጵያውያን ለአንድ ዓላማ ተሰልፈው የሀገርን ዳር ድንበር አስከብረዋል፡፡ ለእነሱ በየቦታው በተለያየ መልኩ መታሰቢያ መስራት ተገቢ ነው፡፡ ትውልዱ አኩሪ ታሪኮችን አውቆ ተኮትኩቶ እንዲያድግ አላደረግንም፡፡ ከዚህ አኳያ በሚስብ መልኩ በቅርፃ ቅርፅና ስዕል የተሰራው ማስታወሻ ትውልዱ አያቶቹ እና ቅድመ አያቶቹ ሀገርን ለማስከበር የከፈሉትን መስዋዕትነት እንዲረዳ ያግዛል፡፡ አንድነትን እና ዘላቂ ሰላምን ለማጠናከር አስተዋጽኦ አለው ሲሉ አቶ ደጀኔ ተናግረዋል፡፡

"ሾላ" እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ነዋሪ የሆኑት አቶ ቴዎድሮስ ፀሐይ በበኩላቸው፣ በከተማዋ የተሰሩ የልማት ስራዎች ከፍተኛ በጀትና ጉልበት የፈሰሰባቸው ናቸው፡፡ የአዲስ አበባና ኢትዮጵያን ማንነት እንዲይዙ ተደርገው መሰራታቸውን ይናገራሉ፡፡

ለምሳሌ፡- የአንድነትና ትብብር መገለጫ የሆነው የዓድዋ ድልን የሚዘክሩ ነገሮች በሚስብና በሚያምር መልኩ ተቀርፀው መቀመጣቸው ኢትዮጵያውያን አንድነትን፣ ሰላምንና ህብረትን እንዲያጠናክሩ ያደርጋል፡፡ ትውልዱ በትምህርት ቤትና በማንበብ ስለ ሀገሩ ከሚያገኘው በተጨማሪ የተለያዩ የማንነት መገለጫ የሆኑ ቅርሶችን በአካል በማየትና በመዳሰስ ፍቅርና አንድነትን ይማራል፡፡ አንዱ የሌላውን ባህል፣ ቅርስ፣ ባህልና ሀብት ማወቅና የአንዱ መገለጫ የሁሉም መሆኑን እንዲረዳ፣ ብሎም 'የእኔ ብቻ ሀሳብ ትክክል ነው' የሚለውን አመለካከት በመቅረፍ ለጋራ ትርክት ግንባታ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው አስረድተዋል፡፡

በአዲስ አበባ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አነሳሽነት በገበታ ለሸገር የተሰሩ የአንድነትና የእንጦጦ ፓርኮች፣ ወዳጅነት አደባባይ እንዲሁም በዓድዋ ድል መታሰቢያ፣ በኮሪደርና ወንዝ ዳርቻ እና ሌሎች ልማቶች የኢትዮጵያን መልክና ማንነት፣ ታሪክ፣ ባህል፣ እሴት የሚያሳዩ መገለጫዎች በቅርፃ ቅርፅ፣ በስዕል፣ በጽሑፍና በተለያየ ስነ ጥበባዊ ቅርፅ ሳቢ በሆነ መልኩ ተካትተው ተሰርተዋል፡፡

ለምሳሌ፡- ከእንጦጦ እስከ ፒኮክ እየተሰራ ባለው የወንዝ ዳርቻ፣ አራዳ ፓርክ ከዓድዋ ድል መታሰቢያ ወረድ ብሎ የዓድዋ ዘማቾች የተሰባሰቡበት ቦታ የሀገርን ዳር ድንበርና ነፃነት ለማስከበር ኢትዮጵያዊያን ስንቅና የጦር መሳሪያ በፈረስ ላይ ሆነውና ጭነው፣ ጀግኖች አርበኞች ጋሻና ጦር ይዘው ወደ ዓድዋ ጉዞ ሲያደርጉ የሚያሳዩ ሐውልቶች ቆመውና በግድግዳ ላይ ስዕሎች ተስለው ይታያሉ። ነጭ ቀለም ያላቸው ፈረሶች እንዲሁም ተራራማ በሆነው መልክዓ ምድር የሚኖሩ ብርቅዬ ጭላዳ ዝንጀሮዎች በልዩ ስነ ጥበባዊ መልኩ ተሰርተው ይታያሉ፡፡

ከአራዳ ፓርክ ሳንርቅ፣ በዓድዋ ጦርነት ከተሳተፉ የጦር መሪዎች አንዱ በሆኑት ጀግናው ራስ መኮንን ወልደሚካኤል ጉዲሳ ስም ተሰይሞ ለትውልድ የተሻገረው የራስ መኮንን የመስታወት ድልድይም፣ ጀግኖች አርበኞች ይጠቀሙባቸው የነበሩ እንደ ጋሻና ጦር ያሉ ምልክቶችን አካትቶና የሚያምር ስነ ጥበባዊ ውበት ይዞ ተሰርቷል፡፡ የራስ መኮንን ድልድይን ተሻግረን ከጋምቤላ ሆቴል ጎን ወደ ስድስት ኪሎ በሚወስደው መወጣጫ ደረጃ አካባቢ የኢትዮጵያ መለያና ዋነኛ የውጭ ምንዛሬ ምንጭ የሆነው ቡና ብቻ የሚሸጥበትና የሚቀመስበት የቡና ፓርክ ይገኛል፡፡ በዚያው አካባቢም ባለቅኔው ሎሬት ፀጋዬ ገብረ መድህን ወንበር ላይ ቁጭ ብሎ እየፃፈና እያሰላሰለ የሚያሳይ ሐውልትም ይገኛል፡፡

ወደ አንድነት ፓርክ ስናቀናም፤ በፓርኩ ውስጥ የኢትዮጵያን ካርታ ከሚያሳየው ቅርፃ ቅርፅ ጀምሮ በብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች እልፍኝ በተለያዩ ክልሎች የሚኖሩ ህዝቦች ባህል፣ ታሪክና ወግ፣ የቱሪዝም መስህቦች የሚያሳዩ መገለጫዎች እንዲቀመጡ ተደርጓል፡፡ በእንጦጦ ፓርክና ወዳጅነት አደባባይ፣ በኮሪደር ልማት በተለያዩ ስፍራዎች ጥቅም ላይ የዋሉ ቁሳቁሶች፣ ቅርሶችና የተለያዩ ምልክቶች ባህላዊና ሀገራዊ ይዘት ያላቸው ናቸው፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ "የኢትዮጵያ ማንሰራራት ማሳያ፡- የወንዝ ዳርቻ" በሚል ርዕስ በአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ከአራት ወራት በፊት በተላለፈው ጥናታዊ ፊልም ላይ እንደተናገሩት በአራዳ ፓርክ የዓድዋ ዘማቾችን ታሪክ የሚያሳዩ ሐውልቶች እንዲቆሙ የተደረገው ለቱሪስት መስህብነትና ትውልድ እንዲማርባቸው ለማድረግ ታስቦ ነው። "ታሪካችንን ማቅለል አይገባንም፡፡ ለትውልድ ለጋራ ትርክት መገንቢያችን ነው፡፡ ዓድዋ ኢትዮጵያውያን አንድ በመሆን፣ ሀይል፣ አቅምና ሀሳባቸውን በማሰባሰብ ሀገራቸውን የታደጉበት፣ ዛሬ የምንኮራባትን ሀገር ያስረከቡን አበውና እመው በምን ሚስጢር ነው? የሚለውን ትውልዱ የሚማርበትን ሁኔታ ይፈጥራል" ብለዋል፡፡

በጂማ ዩኒቨርሲቲ የታሪክና ቅርስ አስተዳደር መምህር ኑሩ ይማም ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፁት፣ በኢትዮጵያ ባለፉት ሶስት አስርት ዓመታት ሲራመድ የነበረው ትርክት ለልዩነት ከፍ ያለ ቦታ የሰጠ፣ አንድነትን ደግሞ የዘነጋ ነበር፡፡ ኢትዮጵያውያንን ከማሰባሰብ ይልቅ ሁሉም በየአካባቢው፣ በየጎራው የራሱን ትርክት ፈጥሮ እንዲንቀሳቀስ በር የከፈተ ነበር፡፡ የተለያዩ ብሔሮችን፣ ብሔረሰቦችንና ህዝቦችን የሚወክሉ ሐውልቶችና ምልክቶች፣ የተለያዩ የስነ ጥበብ ስራዎችም ከአሰባሳቢነት ይልቅ ለተናጠል ትርክት እንዲውሉ ይሰራ ነበር።

አዲስ አበባ አዳዲስ በተገነቡና በታደሱ ሙዚየሞች፣ በኮሪደር እና ወንዝ ዳርቻ ልማት፣ በፓርኮች የኢትዮጵያውያን ማንነት መገለጫዎችን፣ ታሪኮችንና ጀግኖችን በተለያየ ስነ ጥበባዊ መልኩ መሰራቱ አሰባሰቢ ትርክት ለመገንባት የሚደረገውን ጥረት ያግዛል፡፡ አዲስ አበባ ውብና ፅዱ እንድትሆን ማድረግ ብቻ ሳይሆን በልዩነት ውስጥ አንድነትን ለማጠናከር ከፍተኛ እገዛ ያደርጋሉ፡፡ ይህ ጥረት የሚበረታታ ነው ይላሉ የታሪክ ምሁሩ ኑሩ፡፡

ሌላው እንዲህ ዓይነቱ ስራ የአዲስ አበባን ብሔራዊ ምልክትነት ያሳድጋል። ሁሉም ኢትዮጵያውያን ራሳቸውን የሚያዩበት ሁኔታ ይፈጥራል። ለምሳሌ፡- አንድ ከውጭ ሀገር የመጣ ቱሪስት አዲስ አበባን ሲጎበኝ በሁሉም አካባቢዎች የሚገኙ ቅርሶችን፣ ምልክቶችን፣ ታሪካዊ ሁነቶችን በቀላሉና በአጭር ጊዜ መረዳት ይችላል፡፡ ኢትዮጵያውያንም በአንድ

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

# እየጎለበተ ያለው የአዲስ አበባ ኢንዱስትሪዎች አቅም

- **በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ አራት ወራት ኢንዱስትሪዎቹ 5 ሚሊዮን 53 ሺህ 487 ቶን ተኪ ምርቶችን ለሀገር ውስጥ ገበያ አቅርበዋል**

**በደረጀ ታደሰ**



ፎቶ በገነት ወንድሙ

የአልማኪር ጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ማምረቻ ድርጅት ተኪ ምርቶችን በማምረት ሂደት ላይ

ኢትዮጵያ ከኢንዱስትሪ ዘርፍ ጋር በመተዋወቅ ረገድ ረጅም ዕድሜ አስቆጥራለች፡፡ ይሁን እንጂ ያለፈችበት ጉዞ የኢንዱስትሪው ዘርፍ የዕድሜውን ያክል ውጤት እንዳያመጣ አድርጎ ቆይቷል፡፡ ነገር ግን ከትንሽ እስከ ትልቅ የኢንዱስትሪ ምርቶችን በከፍተኛ ደረጃ ከውጭ ሀገር በማስገባት ትጠቀማለች፡፡ በዚህ ምክንያት ለምርት ግዢ ለከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ወጪ ስትዳረግ ቆይታለች፡፡

ረጅም ዘመናትን በተሻገረ ሂደት ውስጥ እንደ ሀገር በሚደረገው የገቢና የወጪ ንግድ እንቅስቃሴ ምጣኔ ላይ፤ የገቢ ምርቶች መጠን ከወጪ ምርቶች መጠን አብላጫ መያዙ ነው፡፡ ይህንን ትልቅ ክፍተት ለማጥበብ፣ በሂደትም የወጪ ምርቶች ከገቢ ምርቶች አብላጫ እንዲኖራቸው ለማስቻል የመደመር ፍልስፍና አካል የሆነው የሀገር በቀል ኢኮኖሚያዊ እሳቤ እየተተገበረ ይገኛል፡፡ በሀገር ውስጥ ያሉ ኢንዱስትሪዎችን አቅም በማሳደግ ከውጭ ሀገር የሚገቡ ምርቶችን ተክተው እንዲያመርቱ ማስቻል የሚለው እና ወደ ተግባር ተለውጦ ተጨባጭ ውጤት እያመጣ ያለው የኢንዱስትሪ ልማት እሳቤ በምሳሌነት የሚጠቀስ ነው፡፡

አምራች ኢንዱስትሪዎች እንዲስፋፉ፣ አቅማቸው እንዲያድግ፣ ምርትና ምርታማነታቸው እንዲጨምር እንደ ሀገር ባለፉት ጥቂት ዓመታት በተሠራው ሥራ ከፍተኛ ውጤት ስለመምጣቱ ሪፖርቶች ያመለክታሉ፡፡ መዲናችን አዲስ አበባም ለዘርፉ ዕድገት የበኩሏን ድርሻ እየተወጣች ስለመሆኑ፤ ከከተማ አስተዳደሩ የኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል፡፡ እንደቢሮው መረጃ ከሆነ፤ በመዲናዋ በሕጋዊ መንገድ ተመዝግበው፣ አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል እየተደረገላቸው ምርት በማምረት ላይ የሚገኙ ኢንዱስትሪዎች ብዛት 3 ሺህ 822 ደርሷል (ይህ መረጃ እስከ ሕዳር 2018 ዓ.ም. ድረስ ያለውን የሚመለከት ነው)፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ በቢሮ ኃላፊ ደረጃ የአምራች ኢንዱስትሪ ድጋፍ ዘርፍ ኃላፊ አቶ ጳውሎስ ኩሳ ለአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ለአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል በሰጡት ማብራሪያ እንደገለጹት፤ በከተማዋ በሥራ ላይ ካሉ አምራች ኢንዱስትሪዎች መካከል ቁጥራቸው 2 ሺህ 265 የሚሆኑት ከውጭ ሀገር የሚገቡ ተኪ ምርቶችን የሚያመርቱ ናቸው፡፡ እነዚህ ኢንዱስትሪዎች በዋናነት በአራት ንዑስ ዘርፎች ማለትም፡- በቆዳና ጨርቃ ጨርቅ፣ በእንጨትና ብረታ ብረት፣ በግብርና ምርት ማቀነባበር ወይም አግሮ ፕሮሰሲንግ እንዲሁም ኬሚካልና ኮንስትራክሽን ውስጥ የሚካተቱ ሲሆን፤ ኢንዱስትሪዎቹ ከውጭ ሀገራት የሚገቡ ምርቶችን በመተካት ትልቅ አስተዋፅኦ እያደረጉ ነው፡፡

> **በአሁኑ ጊዜ በአዲስ አበባ የአምራች ኢንዱስትሪዎች የማምረት አቅም 66 ነጥብ 6 ከመቶ ደርሷል። ይህንን በ2022 በጀት ዓመት ወደ 85 ከመቶ ለማድረስ ታቅዶ እየተሠራ ነው**

የካቫ፣ የቆዳና ቆዳ ውጤቶች አምራች ኢንዱስትሪ እንዲሁም የአልማኪር ጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ማምረቻ ኢንዱስትሪ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደረጃ ከውጭ ሀገር የሚገቡ ተኪ ምርቶችን በማምረት ሥራ ከሚገኙት በሺዎች የሚቆጠሩ ኢንዱስትሪዎች መካከል ይካተታሉ፡፡ የዝግጅት ክፍላችንም የእነዚህ አምራች ኢንዱስትሪዎች የሥራ እንቅስቃሴ ምን እንደሚመስል ለመቃኘት ሞክሯል፡፡ በቅኝቱም ኢንዱስትሪዎቹ ተኪ ምርቶችን በማምረት ለዘርፉ ዕድገት የበኩላቸውን ሚና እየተወጡ መሆናቸውን መገንዘብ ችሏል፡፡

ወጣት ቤተል ተካ፤ የካቫና የቆዳና ቆዳ ውጤቶች አምራች ድርጅት ሥራ አስኪያጅ ናት፡፡ በ2009 ዓ.ም. በአንድ ማሽንና በአንድ ሠራተኛ ሥራውን የጀመረው ድርጅቱ ዛሬ ላይ በምርቶቹ ለሀገር በሚጠቅም ደረጃ የተገኘበት የዓመታት ጉዞ እንደሆነ ትናገራለች። እንደ ወጣት ቤተል ገለፃ፤ የድርጅቱ መሥራች የአርክቴክት ሙያተኛዋ ሰመሐል ጎሽ ትባላለች፡፡ አጀማመሯም በውስጧ የታመቀውን ዕውቀትና ክህሎት ለመግለጥ የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ምርት ሥራ ሁነኛ ዘርፍ ሆኖ ስላገኘችው ነው። በዚህ የተነሳም ሩቅ ሳትሄድ በገዛችው አንድ ማሽን፣ የእናቷን ቤት በመሥሪያ ቦታነት በመጠቀምና ራሷን ሠራተኛ አድርጋ በማሰማራት ሥራዋን አንድ ብላ ጀመረች፡፡ ጅምሯ ሊያድግ የሚችል እንደሆነ በመረዳቷ፤ ተጨማሪ አንድ ማሽንና አንድ ሠራተኛ ወደ ሥራ ቦታው አካተተች፡፡

የስምንት ዓመት ዕድሜ ያስቆጠረው የሰመሐል የሥራ እንቅስቃሴ አሁን ላይ ተስፋ የሚጣልበት ድርጅት ሆኗል፡፡ በ850 ካሬ ባረፈ ሼድ ውስጥ፣ የቆዳና ቆዳ ውጤቶችን ማምረት የሚያስችሉ ዘመናዊ ማሽኖችን በመጠቀም፣ ከ50 በላይ ቋሚ ሠራተኞችን በመቅጠር ምርቶችን ለሀገር ውስጥ እና ለውጭ ሀገራት ገበያዎች በማቅረብ ላይ ይገኛል፡፡

የተለያዩ ቦርሳዎችን፣ የሴት ጫማዎችን፣ የቢሮ መገልገያዎችን፣ የአበባ ማስቀመጫዎችን፣ ለዓለም አቀፍ ስብሰባና ኮንፈረንስ ተሳታፊዎች የሚቀርቡ የተቋማት ሎጎ የታተመባቸው ቦርሳዎች፣ የፅሕፈት መሳሪያ መያዣዎች እና መሰል ምርቶችን የሚያመርተው የካቫና የቆዳና ቆዳ ውጤቶች አምራች ኢንዱስትሪ ከምርቶቹ መካከል ከ90 ከመቶ በላይ ለውጭ ሀገር ገበያዎች እንደሚያቀርብ የጠቆመችው ሥራ አስኪያጇ፤ ከነዚህም አሜሪካ፣ ሩዋንዳ፣ ጣሊያን፣ ጀርመን፣ ሲውዘርላንድ፣ ካናዳ ይጠቀሳሉ፡፡ በዚህ ሥራ ለሀገር ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ማስገኘት ችሏል፡፡ ለአብነት በ2015 ዓ.ም. ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ካስገኙ መሰል አምራቾች መካከል የተሻለ ደረጃ በማግኘት ከመንግስት ዕውቅናና ሽልማት ተሰጥቶታል፡፡

“የኢትዮጵያ ቆዳ ምርት በዓለም አቀፍ ደረጃ በጣም ተመራጭ እና ተወዳጅ ነው።” ስለዚህ የቆዳ ምርቶች በጥራትና የዓለም ገበያን ባገናዘበ መልኩ ከተዘጋጁ የምርቱ ገበያ የማግኘት ዕድል ቀላል ነው" ያለችው ወጣት ቤተል፤ ለሥራቸው ውጤታማነት የመንግስት ድጋፍ ከፍተኛ መሆኑን አንስታለች፡፡ ይህም ምቹ የሥራ ቦታ ከመስጠት ጀምሮ ጥራት ያለውን ምርት ለማምረት የሚያስችሉ ማሽኖችን እና መለዋወጫዎችን ከቀረጥ ነጻ እንዲያስገቡ ዕድል ማመቻቸቱን ጠቅሳለች፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የውጭ ምንዛሬ ገቢ ተጠቃሚነት ላይ የነበረው አሠራር በመሻሻሉ ለአምራቾች ከሚሰጠው ተጠቃሚነት መቋደስ መቻላቸው ለስኬታቸው አጋዥ አቅም እንደሆናቸው አልሸሸገችም፡፡ በቀጣይ ምርታቸውን በብዛት፣ በዓይነት እና በጥራት በማሳደግ የሀገር ውስጥ ፍላጎትን ከማሟላት ባሻገር በዓለም ገበያ ላይ በስፋት ለመሳተፍ ድርጅቱ አቅዷል፡፡

በተመሳሳይ የአልማኪር ጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ማምረቻ ድርጅት ተኪ ምርቶችን በማምረት ለሀገር ውስጥ ገበያ እንዲሁም የውጭ ገበያን በመድረስ ከኢንዱስትሪው የሚጠበቅበትን ኃላፊነት እየተወጣ ስለመሆኑ የድርጅቱ መስራችና ሥራ አስኪያጅ አቶ ክብሮም ፍፁም ያስረዳሉ፡፡ እንደ እሳቸው ማብራሪያ፤ ድርጅቱ በ2007 ዓ.ም. የተመሰረተ ነው። ሲመሰረት በ18 ማሽኖች እና በ18 የሠው ኃይል በህትመትና የአልባሳት ስፌት ሥራ ላይ በማተኮር ነበር፡፡ በሂደትም አቅሙን በማሳደግ እና በማሻሻል በአሁኑ ወቅት በ374 ማሽኖች የጨርቃ ጨርቅና የአልባሳት ምርት ሥራን በስፋት እና በብዛት እያከናወነ ይገኛል፡፡ በዚህም ለ318 ሠራተኞች ቋሚ የሥራ ዕድል ፈጥሯል፡፡

የአልማኪር ጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ማምረቻ ድርጅት ከምስረታው ማግስት ጀምሮ በምርቶቹ የዓለም ገበያን እንደደረሰ የጠቆሙት አቶ ክብሮም፤ “ለሦስት ተከታታይ ዓመታት ያለማቋረጥ ምርቶቻችንን ለውጭ ሀገራት ገበያዎች ስናቀርብ ቆይተናል፡፡ የምናቀርበው ከምናመርተው 95 ከመቶ የሚሸፍን ነበር፡፡ ምርቶቻችንን ከምንልክባቸው ሀገራት መካከል ጀርመን፣ ጅቡቲ እና ኡጋንዳ በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ” ብለዋል፡፡

አያይዘው እንዳብራሩት፤ ድርጅቱ ካለፉት ሦስት ዓመታት ጀምሮ፤ ከሚያመርታቸው ምርቶች መካከል 95 ከመቶ የሚሆነውን ከውጭ ሀገራት የሚገቡ ምርቶች በመተካት ለሀገር ውስጥ ገበያ እያቀረበ ይገኛል፡፡ ከምርቶቹ መካከል፡- የወንድ እና የሴት ሸሚዞች፣ ቲሸርቶች፣ የልጆች አልባሳት፣ ጃኬቶች፣ ከረባት ይጠቀሳሉ፡፡ ለውጭ ገበያ ከምናቀርበው ውስጥ 5 ከመቶ የሚሆነውን ምርት የሚይዘው የወንዶች ከረባት ሲሆን የገበያ መዳረሻውም ናይጄሪያ ነው፡፡

የአልማኪር ጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ማምረቻ ድርጅት አሁን ለደረሰበት ስኬት የከተማ አስተዳደሩ አስተዋፅኦ የላቀ ስለመሆኑ አቶ ክብሮም አልሸሸጉም። ይህንንም አስመልክቶ ሲገልጹ፤ “ከመንግስት 300 ካሬ ሜትር

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

# ኪነ ጥበባዊ መሰናዶዎች

በጊዜው አማረ

በአዲስ አበባ ባሳለፍነው ሳምንት የተለያዩ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች ለጥበብ አፍቃሪያን ሲደርሱ ቆይተዋል፡፡ ዛሬን ጨምሮ በሚቀጥሉት ቀናትም ይኸው የሚቀጥል ይሆናል፡፡ ከተሰናዱ ዋና ዋና ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች መካከል የመጽሐፍ ምርቃት፣ የንባብ ውይይት፣ የሥዕል አውደ ርዕይ እና የቴአትር መርሃ ግብር ይገኙበታል፡፡ ለመረጃ ይሆንዎት ዘንድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል የተወሰኑትን እንደሚከተለው አዘጋጅቷቸዋል፡፡

## የንባብ ፌስቲቫል

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል እና ኪነ-ጥበብ ቢሮ ለ13ኛ ጊዜ የንባብ ሳምንት አዘጋጅቷል፡፡ የንባብ ፌስቲቫሉ "ንባብ ለላዕላይ መዋቅር ለውጥ" በሚል መሪ ሀሳብ በከተማ ደረጃ ከታኅሣሥ 16 እስከ 20 ቀን 2018 ዓ.ም ባሉት ተከታታይ 5 ቀናት ካዛንቺስ በሚገኘው የህዝብ መዝናኛ/ወተር ፓርክ/ እየተካሄደ ነው። ፌስቲቫሉ የተዘጋጀው የትውልዱን የንባብ ባህል በማጎልበት ብቁ ዜጋ ለመፍጠር፤ የህብረተሰቡን መስተጋብር ለማጎልበት፤ የሥነ-ጽሑፍ እና የፈጠራ ስራን ለማሳደግ፤ መጻሕፍት ቤቶችን እና ደራሲያንን ለማበረታታት፣ ከአንባብያን ጋር የሚገናኙበትን አውድ ለመፍጠር በተጨማሪም የመጽሐፍት ሻጮች በሥራቸው እንዲጠናከሩ መነቃቃትን ለመፍጠር ታስቦ እንደሆነ ተነግሯል። ከንባብ ፌስቲቫሉ ጎን ለጎን በዘርፉ ምሁራን ተዘጋጅቶ የሚቀርብ የፓናል ውይይት /ቶክሾው/ እንደሚካሄድም ቢሮው አስታውቋል፡፡

## መጽሐፍት

በዛሬው እለት "ጊዜን መሸከም" የተሰኘው የግጥም መጽሐፍ ተመርቆ ለንባብ ይበቃል፡፡ የገጣሚ ዘውዴ አለልኝ የግጥም ስብስቦችን የያዘው ይህ መጽሐፍ ከለም ሆቴል ወደ ኢምፔሪያል ጥቂት መቶ ሜትሮች ገባ ብሎ በሚገኘው በመሶብ የባህል ሙዚቃ ማዕከል ተመርቆ ከአንባቢያን እጅ ይደርሳል፡፡ የመጽሐፍ ምረቃ መርሃ ግብር ከ10 ሰዓት ጀምሮ የሚካሄድ ሲሆን ወጣት ገጣሚያን እና ሐያሲያን እንደሚታደሙ ተገልጿል፡፡

በሌላ መረጃ የራስ ሳባ ሲሳይ የግጥም መድብል ለንባብ በቅቷል፡፡ "የብርሃን ጥሞና" የተሰኘው ይህ መጽሐፍ የብርሃንን ውበት፣ የብርሃንን ሙቀት፣ የብርሃንን ህይወትነት፣ የብርሃንን እምነት እና ጥበብነት የሚያሳይ ነው ተብሏል። ደራሲዋ በተለያዩ ጋዜጣዎች እና ሬድዮን ጣብያዎች የግጥም ስራዎችን በማቅረብ የምትታወቅ ሲሆን አሁን ደግሞ የመጀመሪያ የሆነችውን "የብርሃን ጥሞና" የተሰኘ የግጥም መጽሐፍ ለንባብ አብቅታለች፡፡

## የስዕል አውደ ርዕይ

"የራስ መንገድ" የተሰኘው የስእል አውደ ርእይ በእይታ ላይ ይገኛል። በዮሴፍ ሰቦቅሳ (ሰናይት) የቀረበው ይህ የስእል አውደ ርእይ ከቀናት በፊት ለእይታ ሙብቃቱ የሚታወስ ነው፡፡ አውደ ርእዩ እስከ ታህሳስ 27 ቀን 2018 ዓ.ም ድረስ በእይታ ላይ እንደሚቆይም ተገልጿል። የስዕል አውደ ርዕዩ እየታየ የሚገኘው መስቀል አደባባይ አጠገብ በሚገኘው በሃያት ሬጀንሲ ሆቴል ፈንደቃ የባህል ማዕከል ውስጥ ነው፡፡

## ፊልም

አቀንቃኙ (ዘ ሲንገር) የተሰኘ አዲስ ፊልም ለእይታ ሊበቃ ነው፡፡ ፊልሙ የተሰራው በተስፋጽዮን መኩሪያ መሆኑም ተጠቅሷል፡፡ በፊልሙ ታዋቂና አዳዲስ ተዋንያን ተሳትፈውበታል፡፡ ከእነዚህም መካከል ሰይፈሚካኤል ተስፋዬ፣ ፍሬህይወት ታምራት፣ ሙሉአለም ጌታቸው፣ ኤፍሬም ታደሰ፣ ሳሙኤል ተስፋዬ፣ ቲና ገብረአምላክ፣ መስከረም አማረ እና ሌሎችም ይጠቀሳሉ፡፡ ፊልሙ በቅርቡ ተመርቆ ለእይታ እንደሚበቃ ተገልጿል፡፡

## የቴአትር መርሃግብር

በመዲናችን አዲስ አበባ ቅዳሜ እና እሁድ የተለያዩ ቴአትሮች ይታያሉ፡፡ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር በተለያዩ ቀናት የተለያዩ ቴአትሮች ለጥበብ አፍቃሪያን የሚቀርቡ ይሆናል፡፡ እነዚህም ቅዳሜ ቀን 8፡30 ሰዓት ላይ 12ቱ እንግዶች እንዲሁም 11፡30 ሰዓት ባሎችና ሚስቶች ለእይታ ይበቃሉ፡፡ እሁድ በ8፡30 ሰዓት ንጉሥ አርማህ ቴአትር፣ በ11፡30 እምዩ ብረቷም እንዲሁ ለተመልካች ይቀርባሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ማክሰኞ 11፡30 ሰዓት ሶስቱ አይጦች፣ ረቡዕ በ11፡30 ሰዓት የቅርብ ሩቅ፣ ሐሙስ በ11፡30 ሰዓት ሽምጋይ እንዲሁም አርብ በተመሳሳይ ሰዓት ዴጊያ የተሰኙ ቴአትሮች ከሚታዩት መካከል ይጠቀሳሉ፡፡ ከቀናት በፊት የተመረቀው "የመጨረሻው ፍርድ" የተሰኘ ቴአትር ደግሞ ዘወትር እሁድ ከቀኑ 11:30 እስከ ምሽቱ 1:30 በሀገር ፍቅት ቴአትር ቤት ለእይታ እንደሚበቃ ተገልጿል፡፡













ፎቶ- ከገፀ ድር

በከተማችን ከተዘጋጁ ኪነ ጥበባዊ መሰናዶዎች በከፊል

# የቁጥር ጨዋታ

## የባለፈው ሳምንት ጥያቄ መልስ

ውድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ አንባቢዎቻችን ባለፈው ሳምንት የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችሁ ነበር፡፡ የጥያቄው ትክክለኛ አሰራርና መልስ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ ከታች በኩል በስተቀኝ የሚገኘውን ቁጥር ለማግኘት የሌሎችን ሁለት ቁጥሮች ድምር ለ8 እናካፍላለን፡፡ በዚህም የመጀመሪያው ክብ (39+17)÷8=7 ይሆናል፡፡ የሁለተኛው ደግሞ (53+19)÷ 8=9 ነው፡፡ በዚህ መሰረት ሶስተኛውና መጨረሻው(18+14)÷8=4 ይሆናል፡፡ስለዚህ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛ ቁጥር **4** ነው፡፡




## የዛሬው የቁጥር ጨዋታ

ውድ አንባቢዎቻችን ከታች በምስሉ ላይ የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችኋል፡፡ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛው ቁጥር ስንት ነው? በጥያቄው ራስዎን እየፈተኑ ይዝናኑ፡፡ የጥያቄውን መልስ በቀጣይ ሳምንት እትማችን ይዘን እንቀርባለን፡



# የሰባ ደረጃ ፍካት

**በአብርሃም ገብሬ**

አንዳንድ ሥፍራዎች ስማቸው ከትውልድ ትውልድ ሳይደበዝዙ ይዘልቃሉ፡፡ በጊዜ ጅረት ውስጥ እየፈሰሱም ዋነኛ መገለጫቸውን ሳይለቁ ዘመን ይሻገራሉ፡፡ የትናንቱን ከዛሬው ጋር በማስተሳሰር ትውስታን ይቀርጻሉ፡፡ ህይወት ዘርተው ትዝታን ያፈራሉ፡፡ ልክ እንደ 'ሰባ ደረጃ' ያሉ ሥፍራዎች ትናንትን ከዛሬ፤ ዛሬን ከነገ ጋር በማሰናኘት የዝመና ሂደት አብነት ይሆናሉ፡፡ በአዲስ መልክ የተሰራው ሰባ ደረጃም ይህንኑ ነው የሚመሰክረው፡፡

በእርግጥ ሰባ ደረጃ የስሙና የታሪኩን ያህል ውብ አልነበረም፡፡ በጥበብ ሥራዎች የተደነቀውን ያህል፣ በአካል ሲያዩት ስሙን ከተግባሩ ጋር ማሰናኘት ተስኖት ደብዝዞ ነበር፡፡ አንዱ ምክንያት ትውልድ ሄዶ በመጣ ቁጥር ይሄ ነው የሚባል ማሻሻያ ሳይደረግለት እዚህ ዘመን ላይ መድረሱ ነበር፡፡ ውበቱም ሆነ ቀለሙ እንደደበዘዘ አልፎ ሂያጁን ሲታዘብ ለዘመናት ኖሯል፡፡ የማታ ማታ ግን ሰባ ደረጃ ስሙን ከግብሩ ጋር ያሰናኘ ለውጥ አድርጓል፡፡

አሁን ሰባ ደረጃ ያ የደበዘዘው መልኩ ተቀይሯል፡፡ ስሙን ብቻ ሳይሆን ግብሩም ገዝፏል፡፡ አቧራ ጠጥተው የነበሩት የደረጃዎቹ ጡቦች በአዲስ መልክ ተቀይረዋል፡፡ መውጫ መውረጃዎቹም በአበቦች ተጊጠዋል፡፡ ጠባብ የነበረው ሰባ ደረጃ ወደ ጎን ሰፍቶ ጥሩ የመዝናኛ ሥፍራ ሆኗል፡፡ ይኸው! ታሪኩንና ስሙን በሚመጥን ደረጃ ተሰርቶ የሕዝቡ ማረፊያ ከሆነ ውሎ አድሯል፡፡ የአዲስ ልሳን ዝግጅት ክፍልም ሰባ ደረጃን አመሻሽ ላይ የጎበኘ ሲሆን፣ በስፍራው የነበሩ ግለሰቦችን አነጋግሮ ቀጣዩን መጣጥፍ አጠናቅሯል፡፡



ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

በኮሪደር ልማቱ ውበት የተጎናጸፈው ሰባ ደረጃ

## ሰባ ደረጃ ትናንትና ዛሬ

ባለፈው ሳምንት ረዕቡ ሰባ ደረጃን ተዘዋውሬ ለመጎብኘት 12፡00 ሰዓት ገደማ ወደ ሥፍራው ለማቅናት ጉዞዬን ጀመርኩ፡፡ የንፋሱ ሽውታ በጆሮዬ ሽውው... ብሎ እያለፈ ከአራት ኪሎ ቀኜን ይዤ እየተጓዝኩ ነው፡፡ በአጠገቤ ሥራ ውለው ወደ ቤት ለመጓዝ ፈጠን ፈጠን እያሉ የሚራመዱ አዲስ አበቤዎችን እየቃኘሁ፣ የአርመን ኦርቶዶክስ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ጋር ደረስኩ፡፡ ከዚህ ቀደም ከነበረው በተሻለ ታሪካዊው ቤተ ክርስቲያን በግልጽ ስለሚታይ፣ ለአካባቢው ተጨማሪ ግርማ ሞገስ ሰጥቶታል፡፡ በቤተክርስቲያኑ ደጃፍ ላይ የተተከሉት አረንጓዴ ጽዶችን እየቃኘሁ ወደ ነጩ ህንጻ አለፍኩ፡፡

## የሰባ ደረጃ ሌላኛው ገጽ

ሰባ ደረጃ የቀደመ ገጽታውን ሳይለቅ ዘምኗል፡፡ መውጫ መውረጃው ጠባብ የነበረው ሰባ ደረጃ ወደ ጎን ሰፍቷል። በብርሃንና በአበባ ተሽቆጥቁጦ ውበት ላይ ውበት ደርቧል፡፡ ከነጩ ህንጻ ሥር ያለው ካፌ በስተቀኝ በረንዳ ላይ ቡና የሚጠጣው ወጣት አጠገብ ቁጭ ብዬ ቡና አዘዝኩ፡፡ ወጣቱ ልጅ የሆነ ነገር ላወራው እንደፈለኩ ገብቶታል፡፡ ራሴን አስተዋውቄው ጨዋታ ጀመርን። እሱባለው አወቀ ይባላል፡፡ ዕድሜው በግምት ሰላሳዎቹ መጀመሪያ ላይ ይሆናል፡፡ የሚኖረው ደግሞ ሽሮ ሜዳ ነው፡፡ እሱባለው ሥራ ከጨረሰ በኋላ ብዙ ጊዜ በእግር መንሸራሸር ይወዳል፡፡ ከሚሰራበት በተለምዶ ጊዮርጊስ እየተባለ ከሚጠራው አካባቢ በእግሩ እንደመጣና እግረ መንገዱን እዚህ ጎራ እንዳለ አጫወተኝ፡፡

"ሰባ ደረጃን እንዴት አገኘሽው?" አልኩት፡፡

"በጣም አስገራሚ ለውጥ ነው የተደረገለት፡፡ የትናንትና ገጽታውን ሳይለቅ በዚህ ልክ ውብ ተደርጎ መሰራቱ አስገርሞኛል፡፡ እንደምታየው ሰባ ደረጃ ደንበኛ የማረፊያና የመዝናኛ ሥፍራ ሆኗል" በማለት፤ ፊቱን ወደ ቀኝ አዙሮ ሰባ ደረጃን በጉንጮቹ እያመለከተ ስለ ዛሬው ሰባ ደረጃ ለውጥ አወጋኝ፡፡

እሱባለው ሰባ ደረጃ ከመሰራቱ በፊት አልፎ አልፎ ይመጣ ነበር፡፡ ነገር ግን ሰባ ደረጃ ስሙ ግዝፈት ቢኖረውም፣ ለመቀጣጠሪያና ለመተላለፊያ እንጂ ማረፊያ አልነበረም ሲል አጫውቶኛል፡፡

እሱባለውን ተሰናብቼው የሰባ ደረጃን ጡቦች እየቆጠርኩ ወደ ላይ መውጣት ጀመርኩ፡፡ ትንሽ ደረጃውን እንደወጣሁ፣ ዕድሜያቸው በግምት ሰላሳዎቹ መጨረሻ ላይ የሚገኙ ጥንዶች ትኩረቴን ሳቡት፡፡ ደረጃው ላይ ቁጭ ብለው ያወጋሉ፡፡ 'ሄጄ ላውራቸው ወይስ ልለፋቸው...' እያልኩ ለሴኮንድ እያመነታሁ ቆየሁ፡፡ 'ግድ የለም' ብዬ ቀረብ በማለት 'ሰላም!' አልኳቸው፡፡

ወንዱ ቀና ብሎ በስሱ ፈገግ በማለት 'ሰላም!' አለኝ፡፡ ራሴን አስተዋውቄ ከአጠገባቸው ቁጭ አልኩኝ፡፡ ባልና ሚስት ናቸው፡፡ ወንዱ ሰለሞን ሃይሉ፣ ሴቷ ቤተልሄም ጣሰው ትባላለች፡፡

"ፍቅራችሁን የሮሚዮና ጁልዬት ያድርግላችሁ!" አልኳቸው፡፡

"የበዛብህና የሰብለወንጌል ቢሆን አይሻልም?" ሰለሞን ፈገግ ብሎ ተመለከተኝ፡፡

"ትክክል ብለሃል፡፡ አሜን! የበዛብህና የሰብለወንጌል ያድርግላችሁ!" ራሴን አርሜ ፈጠን ብዬ ምላሽ ሰጠሁ፡፡

ቤተልሄም በተጠቀለለ ወረቀት ላይ ከያዘችው ቺብስ እንድይዝ ጋበዘችኝ፡፡ ቺብሱን እየቆረጠምኩ፣ "ወንደላጤዎች እዚህ እንዳይቀመጡ ተከልክሏል እንዴ?" ጥያቄዬ በቀልድ አዋዝቼ ጀመርኩ፡፡ ሁለቱም ፈገግ ብለው ተመለከቱኝ፡፡

"ያላገቡ ሰዎች በፍጥነት ያግቡ፡፡ ይኸው ጎዳናዎቹም ፍቅር ይዘምራሉ፡፡ ሰባ ደረጃ እንኳን ከወንደላጤዎቹ ይልቅ ጥንዶችን ኑልኝ ብላ እየተጣራች ነው" ሰለሞን ፈገግ ብሎ መለሰልኝ፡፡ በእርግጥ ፈንጠር ፈንጠር ብለው የተቀመጡት በአብዛኛው ጥንዶች ናቸው፡፡ አልፎ አልፎ ለብቻቸው የተቀመጡ ጥቂት ወጣቶችም ይታያሉ፡፡

"እንዴት ነው ሰባ ደረጃ?" ሰለሞንን ጠየኩት፡፡

"በጣም አምሮበታል! ግሩም ተደርጎ ነው የተሰራው" እኔና ቤተልሄምን አፈራርቆ እየተመለከተ መለሰልኝ፡፡

ሰለሞን ቀበና ነው ተወልዶ ያደገው። አሁን ላይ ባሻ ወልዴ ችሎት አካባቢ ኮንዶሚኒየም ቤት ውስጥ ከሚስቱ ቤተልሄምና ከአንድ ሴት ልጃቸው ጋር ይኖራሉ፡፡

ሰባ ደረጃ የበፊትና የአሁኑ ገጽታው በቀልድ አስመስዬ የግል ትውስታዬን በጨረፍታ አወጋኋቸው፡፡ የእኔን ጨዋታ ተከትሎ፣ ሰለሞን ሰባ ደረጃ ከልጅነቱ አንስቶ እንደሚያውቀው አጫወተኝ፡፡ ያለፈው ትዝታውን ከአሁኑ የሰባ ደረጃ ገጽታ ጋር እያነጻጸረ ብዙ አወጋን፤ "ሰባ ደረጃን ይበልጥ የማስታውሰው ከጓደኞቼ አመሻሽ ላይ ከቀበና ተነስተን በመምጣት ደረጃው ላይ ቁጭ ብለን አልፎ ሂያጁን እንመለከት ነበር፡፡ በፊት በአብዛኛው ደረጃው መተላለፊያ ድልድይ ሆኖ ነበር የሚያገለግለው፡፡ ከወደ ናዝሬት ትምህርት ቤት የሚመጣውና ከታች ወደላይ የሚወጣው የሰው ግርግር ማብቂያ አልነበረውም፡፡ ደረጃው በግራና በቀኝ ያለው ጠበብ ያለ ስለሆነ ለመቀመጥ ብዙም የሚመች አልነበረም። በዚህ ላይ ጥሩ ያልሆነ ሽታ እንደነበረው ትዝ ይለኛል፡፡

ነገር ግን ሰባ ደረጃ ስሙ ታዋቂ ስለሆነ ለመቀጣጠር ምቹ ነበር፡፡ እኔና ጓደኞቼ ሰባ ደረጃ ላይ ቁጭ ብለን ካወጋን በኋላ ፊት ለፊት ወደሚገኘው ትራኮን ሆቴል ጎራ እንል ነበር፡፡ ያን ጊዜ ፑል ቤት ብርቅ ስለነበር ፑል ለመጫወት ነበር ትራኮን የምንመጣው፡፡ ሌላው ሰባ ደረጃን የማስታውሰው እሁድ ማለዳ ላይ ስፖርተኞች ደረጃውን ወጥተው ሲወርዱ ነው፡፡ ደረጃዎቹ ለስፖርት ምቹ ስለሆኑ በብዙዎች ዘንድ ይመረጥ ነበር፡፡ ከዚህ ያለፈ ግን ሰባ ደረጃ እንደ መዝናኛ ሥፍራ የሚቆጠር አልነበረም፡፡ አሁን ላይ ግን ሰባ ደረጃን መልሶ ውብ ተደርጎ በዚህ መልኩ በመሰራቱ ለአካባቢው ተጨማሪ የአይን ማረፊያ ለመሆን በቅቷል፡፡ ከሁሉም በላይ አዲስ አበባ እንዲህ አይነት ክፍት የመዝናኛ ሥፍራዎች ያስፈልጓት ነበር፡፡ ታሪካዊው ሰባ ደረጃ ታሪካዊነቱን ሳይለቅ በዚህ መንገድ እንደገና መሰራቱ ይበል የሚያሰኝ ነው!" በማለት ሰለሞን የሰባ ደረጃ ትዝታውን ከዛሬው ጋር እያነጻጸረ አጫውቶናል፡፡

"በፊት ከሰለሞን ጋር እዚህ ሰባ ደረጃ ተቀጣጥራችሁ አታውቁም?" በአትኩሮት ወጋችን ስትሰማ የነበረችው ቤተልሄምን ጠየኳት፡፡

አንገቷን ግራና ቀኝ በመነቅነቅ "ተቀጣጥረን አናውቅም" አለችኝ። ሀዋሳ ተወልዳ ያደገችው ቤተልሄም፣ በእግር መንሸራሸር ትወዳለች፡፡ እንደ ሰባ ደረጃ ያሉ ክፍት ሥፍራዎች ላይ ቁጭ ብሎ መዝናናት እንደሚያስደስታት አጫውታኛለች፡፡ ሰባ ደረጃ ከተሰራ በኋላ ሰለሞን ባይኖርም ከልጇ'ጋ አመሻሽ ላይ አዘወትራ እንደምትመጣም አክላ አወጋችኝ፡፡

ሰባ ደረጃ ታሪካዊ ከሆኑ የአዲስ አበባ ቀደምት ሥፍራዎች መካከል አንዱ ነው፡፡ ነገር ግን ለዓመታት ይሄ ሥፍራ ዓይን ውስጥ የሚገባ ዕድሳት ተደርጎለት አያውቅም ነበር፡፡ ስመ ገናናው ሰባ ደረጃ፣ ስሙን የሚመጥን ቁመና ላይ አልነበረም፡፡ የአዲስ አበባ የኮሪደር ልማት ፕሮጀክት አካል በመሆን፣ የተደረገለት ዕድሳትና መልሶ ግንባታ ግን ሰባ ደረጃ ስሙን ከተግባር ጋር እንዲያሰናኝ አስችሎታል፡፡ እኔም የበፊቱን ሰባ ደረጃና እንደገና ተሰርቶ ክፍት የተደረገው ሰባ ደረጃን በምናቤ እያመላለስኩ በናዝሬት ትምህርት ቤት አልፌ ወደ ቤቴ አቀናሁ፡፡

# ትውልዱን ከኈጂ ልማዳዊ ድርጊቶች የሚታደገው እርምጃ

**• የውጭ ባህላዊ ድርጊቶችን እና ክብረ በዓላትን የሚያከብሩ ትምህርት ተቋማት ወይም ግለሰቦች 150 ሺህ ብር እንደሚቀጡ ተገልጿል**

**በሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ**

"በቅርብ ርቀት ነው፤ አንዳች የሚያስተጋባ ድምፅ ከፊት ለፊቴ ድንገት አቃጨለ፡፡ ድምፁ የብዙ ሰዎች እንደሆነ ገምቻለሁ፡፡ ቆም ብዬ አዳመጥኩ፤ በምሄድበት የአስፓልት መንገድ እየመጡ እንደሆነም አረጋገጥኩ፡፡ ከተወሰነ ደቂቃ በኋላ ወደ ፊት ሳማትር ጭቃ የተለቀለቁ ወጣቶችን ተመለከትኩ፡፡

እየተጠጋሁ ስሄድ ማንነታቸውንና የፊታቸውን ገፅታ መለየት ባልችልም በትከሻቸው ባነገቡት ቦርሳ ተማሪዎች እንደሆኑ ገምቻለሁ፡፡ ግምቴ ትክክል ነበር፡፡ ግን የየትኛው ትምህርት ቤት ተማሪዎች እንደሆኑ ልብሳቸው በቀይ አፈር የተጨማለቀ በመሆኑ ልለያቸው አልቻልኩም፡፡ ከአራት ኪሎ ወደ ስድስት ኪሎ እየተጓዙ ስለነበር የዚያው አካባቢ ትምህርት ቤት ተማሪዎች እንደሚሆኑ ገመትኩ፡፡ ከላይ እስከ ታች ጭቃ መቀባታቸው 'ክሬዚዴይ' መሆኑ ነው፡፡"

እኔ የምለው ይህ "ክሬዚ ዴይ፣ወተር ዴይ፣ አልዲስ ዴይ፣ ፒጃማ ዴይ፣ ቫላንታይን ዴይ፣ ቶማቶ ዴይ... እያሉ በምዕራባውያን ባህል ውስጥ ዘው ብሎ መግባትና ግራ ተጋብቶ ሌሎችን ግራ ማጋባት ምን የሚሉት ዘመናዊነት ነው?" የሚለው አንድ ወዳጄ የገጠመውን በአንድ ወቅት በፌስ ቡክ ገፁ ካጋራው የተጋራሁት ነው፡፡

ስማቸው እንዳይገለጽ የፈለጉ ወላጅ ይህን ትዝብት የሚያጠናክር አስተያየት እንደሚከተለው አጋርተውኛል፤ "ጫማውን የገዛሁት በወቅቱ ውድ በሚባል ዋጋ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ልጄ የጫማውን ዋጋ እና አቅም ያህል አልተጠቀመችበትም፡፡ ይልቅስ አንድ ቀን ከትምህርት ቤት መልስ ጫማው በውሀ በስብሶ እና በተለይ የአንደኛው እግር ከፊት ለቆ ማድረግ ባለመቻሏ ከቦርሳዋ በተጨማሪ እሱንም በእጇ ይዛ መጣች፡፡ የለበሰችው ልብስ በውሀ ርሷል፡፡ ጸጉሯም እንደረጠበ ነው፡፡ በንዴት ምክንያቱን ስጠይቃት በትምህርት ቤታቸው ወተር ዴይ (የውሀ ቀን) በመከበሩ እንደሆነ በኩራት ነገረችኝ፡፡"

እኚህ ወላጅ በወቅቱ በአስፈላጊነቱ ላይ ከልጃቸው ጋር ያደረጉት ውይይት መግባባት ላይ ያላደረሳቸው እንደሆነ ነግረውን፤ በጉዳዩ ላይ ትምህርት ቤት በመሄድ ለመነጋገር ጥረት ቢያደርጉም ተገቢ ምላሽ ሳያገኙ እንደቀሩ ገልጸዋል። በየትምህርት ቤቱ ቀን ተሰጥቷቸው ይከበሩ የነበሩ መጤ ባህሎች ወላጆችን ለኢኮኖሚያዊ ጫና እና ሌሎች ችግሮች፤ ተማሪዎችን ደግሞ የራሳቸውን ባህል በአግባቡ እንዳያውቁ አድርጓቸው ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት ግን መንግስት ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቶ እንዲቀር ማድረጉ ትውልድን መታደግ ነው ሲሉ አስተያየታቸውን አክለው ገልጸዋል፡፡

የትምህርት ጥራትን ለመጠበቅ


ፎቶ- በገነት ወንድሙ
የዳግማዊ ምኒልክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር አቶ ግርማ ነገሬ


ፎቶ- በገነት ወንድሙ
የዳግማዊ ምኒልክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ11ኛ ክፍል ተማሪ ክርስቲና ነጋሽ

የሀገሪቷን ባህልና ወግ የሚቃረኑ፣ ከባህላችን ጋር የማይሄዱና የመጡበት የማይታወቅ እንደ የእብደት ቀን (Crazy Day)፣ የዋህ ቀን (Gentle Day)፣ የድሮ ቀን(Olds Day)፣ የፍቅረኛሞች ቀን (Valentine Day)፣ የቀለም ቀን (Color Day)፣ የፒጃማ ቀን (Pyjama Day)፣ የትምህርት ማጠናቀቂያ ዝግጅት በተለይ 12ኛ ክፍሎች ከሀገር አቀፍ ፈተና በኋላ የሚዘጋጁት ፕሮግራም (When I Grow Up Party...) እና የመሳሰሉትን የውጭ ባህላዊ ድርጊቶች ማክበር ፈፅሞ የተከለከለ መሆኑን የሚገልጽ ደንብ ስለመዘጋጀቱ ትምህርት ሚኒስቴር አስታውቋል፡፡

በዚህ ደንብ ከላይ የተዘረዘሩትን ጨምሮ የውጭ ባህላዊ ድርጊቶች የሚያከብሩ ትምህርት ተቋማት ወይም ግለሰቦች 150,000 (መቶ ሃምሳ ሺህ) ብር ቅጣት እንደሚቀጡ ተገልጿል። በመመሪያው መብትና ግዴታዎች የተቀመጡ ሲሆን፤ በተማሪዎች ግዴታ ስር ፀጉርን በአግባቡ መስራት/ማሳጠር እና ከተፈጥሯዊ ጸጉራቸው ውጪ እንዳይጠቀሙ ተቀምጧል።

የሴቶች የትምህርት ቤት የደንብ ልብስ ቀሚስ ቁመት ከባት በታች መሆን ያለበት ሲሆን ከአካባቢው ባህል ጋር የማይቃረን ልብስ መልበስ የሚለውም ተካትቷል። ከተከለከሉት ተግባራት መካከልም ሲጋራ ማጨስ፣ አልኮል መጠጣት፣ ጫት መቃም፣ ዕፆችን መጠቀም/ማዘዋወር እንደዚሁም ሞባይልና የሙዚቃ ማዳመጫዎችን ወደ ትምህርት ቤት ይዞ መምጣት ይገኙበታል።

ከዚህ በተጨማሪም በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ኃይማኖታዊ አምልኮ ስርዓትና የፖለቲካ እንቅስቃሴዎችን ማከናወን፣ ሰውነትን መነቀስ፤ ሴት ተማሪዎች የጥፍር፣ የፀጉርና የከንፈር ቀለም መቀባትና መኳኳል እንደዚሁም አላስፈላጊ ጌጥ ማድረግን ይከለክላል።

የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ አዲስ ልሳን ዝግጅት ክፍልም ረቂቅ ደንቡ ከያዛቸው በተለይም የውጭ ባህላዊ ድርጊቶች ትውልድ ግንባታ ላይ ስላላቸው አሉታዊ ተፅዕኖ የሚመለከታቸውን አካላት አናግሯል፡፡

ተማሪ ክርስቲና ነጋሽ የዳግማዊ ምኒልክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ11ኛ ክፍል ተማሪ እና የወተመ (የወላጅ፣ ተማሪ እና መምህራን) አባልና የተማሪዎች ተወካይ ነች፡፡ "የውጭ ባህላዊ ድርጊቶች ለእኛ ለተማሪዎች ምንም ጥቅም የላቸውም፤ ምክንያቱም ቀን አስቀምጠን የምናደርገው ድርጊት በትምህርታችን ውጤታማ እንዳንሆን ከማድረግ ባሻገር የራሳችንን ባህል ትተን የሌሎች አድናቂና ተገዢ አድርጎናል፡፡ ተማሪው ቀናቱን ሲያከብር እንደቀላል ተመልክቷቸውም ይሆናል፡፡ ነገር ግን ስር የሰደደ ችግር የሚያመጣ እና የመማር ማስተማሩን ስራ የሚያስተጓጉል ነው" ስትል ገልጻልናለች፡፡

"ባህሎቹን የሚከተሉ ራሳቸውን እንደ ስልጡን ይቆጥራሉ፡፡ ባህሉ ወደ ሀገራችን ለምን እንደገባ ባልተረዳነው ሁኔታ ይህን ተግባራዊ ማድረግ እራስን ያለማወቅ ብቻ ሳይሆን ማንነትን መርሳት ነው፡፡" በማለትም አክላለች፡፡

"በትምህርት ቤታችን የሰንደቅ ዓላማ ቀን፣ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ቀን፣ የሰራተኞች ቀንን... እናከብራለን፡፡ እነዚህ ቀናት ትርጉም ያላቸው ናቸው። በመሆኑም እኛ ተማሪዎች በእነዚህ ቀናት አማካኝነት ስለ ማንነታችን እና ሀገራዊ ክብራችን ለማወቅ ያስችለናል፡፡ እራስንም ሆነ ሀገርን የሚያሳድገው ደግሞ የራስ የሆነ ባህል ነው፡፡" ስትል ሀሳቧን ሰንዝራለች፡፡

አበበ አክመል በትምህርት ቤቱ መምህር እና የወተመ ዋና ፀሐፊ ናቸው። እንደሳቸው ገለፃ፤ የውጭ ባህላዊ ድርጊቶች ከመማር ማስተማሩ ባሻገር ትውልዱ ላይ የሚፈጥሩት አሉታዊ ተፅዕኖ በቀላል የሚታይ አይደለም፡፡ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን የተማሩት በዚሁ ትምህርት ቤት እንደሆነ ገልጸው፤ በወቅቱ እነዚህ የውጭ ባህላዊ ድርጊቶች እንዳልነበሩና የሆነ ወቅት እንደስልጡን እራስን በማየት የማክበር ሁኔታ እንደመጣ ይናገራሉ፡፡

"እንደ አጋጣሚ ሆኖ ለሥራ ጉዳይ አንዳንድ ሀገሮች ሄጃለሁ፤ አደጉ የምንላቸው ሀገራት ያላቸውን ባህል እና ትውፊት የመጠበቅ ግድታ ይጣልባቸዋል፤ ምክንያቱም የሀገሪቱ ሀብት ናቸውና፡፡ ለእኛ የሚልኩት ባህል ደግሞ ለእድገትም ሆነ ለለውጥ የማይጠቅም ነው፡፡ እኛም ሳንለይ እንቀበላቸዋለን፡፡ ነገር ግን ዋጋ አስከፍለውናል፡፡ እንደ ሀገር በዓለም ደረጃ የምንኮራበት የቅኝ ግዛት ያለመገዛት ታሪክ አለን፡፡ ያንን ክብራችንን ከማስጠበቅ ጎን ለጎን ያለንን ባህልና ትውፊት ትውልዱ በአግባቡ ተረድቶ አለመተግበሩ በእጅ አዙር ቅኝ ግዛት እየተገዛን ነው፡፡ ይህን ችግር ለመፍታት መንግስት ትኩረት ሰጥቶ ሲሰራ በዋናነት ከቤተሰብ ጀምሮ የአካባቢው እና የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ፣ በትውልዱ ላይ ትኩረት አድርጎ መስራት ይጠበቅበታል፡፡ ለዚህ በትምህርት ቤታችን ከተማሪዎች፣ ከወላጆች፣ ከመምህራንና ከትምህርት ቤቱ አመራር ጋር እየሰራን እንገኛለን፡፡" ሲሉ ሀሳባቸውን አጋርተውናል፡፡

አቶ ስንታየሁ እንድሪስ በትምህርት ቤቱ የወተመ ሰብሳቢ ናቸው፡፡ የውጭ ባህላዊ ድርጊቶችን በተመለከተ ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት አስተያየት፣ "ትውልዱ የተጫነበት ጎጂ የውጭ ባህላዊ ድርጊቶች ከፍተኛ ዋጋ የሚያስከፍሉ ናቸው፡፡ ይህ የመጣው ደግሞ አሁን ባለንበት የዲጂታል ዘመን ተፅዕኖ ነው፡፡ የተዘጋጀው ደንብ ለችግሩ መፍትሔ የሚያመጣ ነው" ብለዋል፡፡

የዳግማዊ ምኒልክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር አቶ ግርማ ነገሬ በበኩላቸው፤ እንደ ሀገርም ሆነ እንደከተማ ብሎም እንደ ትምህርት ቤት የውጭ ባህላዊ ድርጊቶች በተለያየ መልኩ ተስፋፍተው ይታዩ ነበር፡፡ ትምህርት ቤታችን ካለበት ቦታ እና ተያያዥ ጉዳዮች አንጻር ችግሩ የሰፋ ነበር፡፡ ችግሩን ለመቅረፍ ከሄደበት ርቀት አንዱ የምክር አገልግሎት የሚሰጡ ባለሙያዎችን መቅጠር ነው፡፡ የባለሙያዎችን ቢሮ በተሟላ ሁኔታ በማደራጀት ተማሪዎች የትምህርት ቤቱን ህግና ደንብ በጠበቀ መልኩ ከአለባበስ ጀምሮ እንዲያከብሩ የማድረግ ስራ ይሰራሉ፡፡ ችግር አለባቸው ተብለው የተለያዩ ተማሪዎችን ደግሞ የክትትል እና የምክር አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ ሌላው በትምህርት ቤቱ የወተመ (ወጣት፣ተማሪዎች እና መምህራን) አደረጃጀት ነው፡፡ ወተመ ከወላጅ፣ ከተማሪዎች እና ከመምህራን የተዋቀረ እንደመሆኑ ጠንካራ አደረጃጀት እና ለመማር ማስተማሩ ትልቅ እገዛ እያደረገ ነው ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተውናል፡፡

ርዕሰ መምህሩ አያይዘውም፤ ደንቡ ቀደም ሲል በትምህርት ቢሮ አማካኝነት በተለያየ መልኩ ወርዶ ወደ ተግባር የተገባበት ነው፡፡ ሆኖም በዚህ መንገድ መቅረቡ የጋራ ጉዳይን በጋራ እና በተቀናጀ ለመስራት ያስችላል፡፡ አሁንም ተማሪዎች ላይ የሚስተዋል ያልተገባ ተግባር እንደሚስተዋል ያልሸሸጉት ርዕሰ መምህሩ በተለይ ሀገር አቀፍ ፈተና ለመውሰድ የሚዘጋጁት የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች የተለየ ፕሮግራም ለማድረግ እና ልብስ ለማሰፋት የሚያደርጉት ሙከራ አንዱ ነው፡፡ ነገር ግን አስፈላጊነቱ ላይ ከወላጅም ሆነ ከተማሪዎች ጋር ውይይት እየተደረገ እንደሆነ አያይዘው ነግረውናል፡፡

"ደንቡ የውጭ ባህላዊ ድርጊቶች አላስፈላጊ ከመሆናቸው ባሻገር ለማስተናገድ እድል የሚሰጥ አይደለም" ያሉት ደግሞ በቅድስተ ማርያም ካቶሊክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር አቶ ኢዶሳ መርጋ ናቸው፡፡

በትምህርት ቤቱ ውስጥ ሦስት በዓላት እንደሚከበር የገለጹት ርዕሰ መምህሩ፤ "አንዱ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ቀን ነው፡፡ ተማሪዎቻችን ቀኑን 'ካልቸር ዴይ' ብለው ይጠሩት ነበር። የተለያየ ባህል አለ የትኛው ነው። የምዕራባውያን፣ የአፍሪካ ወይስ የኢትዮጵያ? ስለዚህ ቀኑ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ህገ መንግስታዊ መብታቸው የተከበረበት መሆኑን እንነግራቸዋለን፡፡ ልብሱንም ለብሰው እንዲመጡ እናደርጋለን"፡፡ ሲሉ ካልቸር ዴይ እና የብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ቀንን ለይተው እንዲያውቁ እንደሚያደርጉ አብራርተዋል፡፡ ሌላው የሰራተኞች ቀን እና የባንዲራ ቀን እንደሆነ ገልጸው በተለያዩ ሁነቶች እንደሚከበር ተናግረዋል፡፡

ወደ ገጽ 18 ዞሯል

# ልጆች፤ ስለምትኖሩበት አካባቢ አድራሻ ምን ያህል ታውቃላችሁ?

**በፋንታነሽ ተፈራ**

ልጆች፤ እንዴት ናችሁ? በዛሬው ርዕሰ ጉዳያችን የምትኖሩበትን አድራሻ በማወቃችሁ ምን ትጠቀማላችሁ? ባለማውቃችሁ ምን ችግር ያጋጥማችኋል? የሚሉትን ሃሳቦች እናነሳለን፡፡ ለዚህ ያነጋገርናቸውን ልጆች ልምዳቸውን እንደሚከተለው አቅርበንላችኋል፡፡



ፎቶ በገነት ወንድሙ
እያሱ ሲሳይ



ፎቶ በገነት ወንድሙ
ዮርዳኖሰ ሃይሉ



ፎቶ በገነት ወንድሙ
እየሩስ ዘለቀ

እያሱ ሲሳይ እባላለሁ፡፡ 12 ዓመቴ ነው፡፡ የምኖረውም ጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 3 መነን ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ነው፡፡ ወደ ትምህርት ቤት የምሄደው ብቻዬን ነው፡፡ በአንድ ወቅት ከእናቴ ጋር ከእኛ ሰፈር ራቅ ወዳለ አካባቢ ሄድን፡፡ ገበያ ነበር፡፡ ከእሷ ጋር ድንገት ተጠፋፋን፡፡ እናቴ እንደነገረችኝ ብትፈልገኝም ሊታገኘኝ አልቻለችም፡፡ ስልክ ቁጥሯን ግን በቃሌ አውቀው ነበር፡፡ ሰዎች ደውለው እንዲያገናኙኝ አደረግኩ። የእናቴን ስልክ ቁጥር ባላውቀው ኖሮ ችግር ሊገጥመኝ ይችል ነበር፡፡ ይህ እንዳይሆን የቤተሰቦቼን ስልክ ቁጥር መያዜ ጠቅሞኛል፤ ጠፍቶ ከመቅረትም ታድጎኛል፡፡

ከቤት በወጣንበት አጋጣሚ የህመም ወይም ሌሎች ችግሮች ሲገጥሙንም ደውሎ ቤተሰብ እንዲወስደን ለማድረግ ይረዳል፡፡ ቤተሰቦቼ ስልክ ቁጥራቸውን እንዳልረሳው ያስጠነቅቁኛል፡፡ ችግር ከገጠመህ ደውል ብለው ይመክሩኛል። እኔም በጥንቃቄ እይዛለሁ፡፡ በዚህም ተጠቅሜበታለሁ፡፡

ዮርዳኖስ ኃይሉ እባላለሁ፡፡ 15 ዓመቴ ነው፤ የምኖረውም ሽሮ ሜዳ ወረዳ 02 ወጣት ማዕከል አካባቢ ነው። ከትምህርት ቤት ወደ ቤቴ ስመለስ እንዳይጠፋብኝ በሰፈር ባለ ሱቅ፣ የቤት ቀለም እንዲሁም በሰፈሩ ስያሜ ነው አድራሻዬን ለይቼ የማውቀው፡፡ ለችግርና ለተለያዩ ነገሮች የሚደርሱልኝን የቤተሰቦቼን ስልክ ቁጥርም በቃሌ ይዣለሁ፡፡

በትምህርት ቤት ጉብኝት ለመሄድም ይሁን አንዳንድ ቃለ መጠይቅ ሲኖር የወላጅ ፍቃድ ስለሚያስፈልግ አድራሻቸውን ነግሬ እንዲደወል አደርጋለሁ፡፡ ከእናትና አባቴ በተጨማሪ የዘመዶቼን ስልክ ቁጥርም እንደ አማራጭ ይዣለሁ፡፡

እየሩስ ዘለቀ እባላለሁ፡፡ ሽሮ ሜዳ አሜሪካን ኤምባሲ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ነዋሪ ነኝ፡፡ 11 ዓመቴ ነው። ከ7 ዓመቴ ጀምሮ ቤተሰቦቼ ስልክ ቁጥራቸውን ደብተሬ ላይ ይፅፉልኝ ነበር። 'ችግር ሲገጥምሽም ስልክ ያለው ሰው ፈልገሽ በዚህ ቁጥር ደውይልን' ይሉኝ ነበር፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የምኖርበትን አድራሻ አውቃለሁ፡፡

አድራሻ ማወቄ ወደምፈልገው ቦታ ለመሄድና ለመመለስ ረድቶኛል፡፡። በሄድኩበት ችግር ቢገጥመኝ እንኳን ቶሎ ደውዬ ወይም ያለሁበትን አድራሻ በመንገር ቤተሰቦቼ እንዲደርሱልኝ አደርጋለሁ፡፡ የምኖርበትንም ሆነ የቤተሰቦቼን ስልክ ቁጥር እንዳውቅ ላደረጉኝ ለቤተሰቦቼ አመሰግናለሁ፡፡

ልጆች፤ እናንተም የምትኖሩበትን አድራሻ ማወቅ፣ የቤተሰቦቻችሁን ስልክ ቁጥር መያዝ ለተለያዩ ችግሮች እንዳትጋለጡ ይረዳችኋልና ይኼንኑ መልካም ተግባር ብታደርጉ ጥሩ ነው፡፡

# 10 ልዩነቶችን ፈልጉ



## እንቆቅልሽ

### ያለፈው ሳምንት ጥያቄ

እህል በልቶ የማይጠጣ

መልስ፦ ሀ. ነቀዝ

### የዚህ ሳምንት ጥያቄ

**ላይጠቅማት ሸክሙ ባሳት**

ሀ. የላም ቀንድ
ለ. የበግ ላት
ሐ. የፍየል ጅራት

ልጆች መልስ ይሆናል የምትሉትን በዌብ ሳይታችን አድርሱን፤ እኛም በተደጋጋሚ የመለሰውን እንሸልማለን፤ ስለዚህ ተሳተፉ፤ ተሸለሙ።

ከተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየወሩ የሚቀርብ

# ከመታየት ወደ መጠቀሚያነት

**• ኮሌጁ የቴክኖሎጂ እና የፈጠራ ስራዎችን ሰርቶ ለኢንተርፕራይዞች እያስተላለፈ ነው**

በሄለን ጥላሁን

ወቅቱ የሰው ልጆችን ድካም የሚያቃልሉ የቴክኖሎጂ ውጤቶች እየተሻሻሉ የቀረቡበት ነው፡፡ ዓለማችንም አሁን ላይ የት ደርሳለች? ብለን የጠየቅን እንደሆነ አይናችን ያየውን ጆሯችን የሰማውን ማመን በቂ ይሆናል፡፡ ታድያ ዓለም በዚህ ልክ የተሻሻሉ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ይፋ ስታደርግ፤ ሀገራችንም ለዚህ የቴክኖሎጂ እድገት የሰጠችው ምላሽ ምን ይመስላል? ለሚለው ጥያቄ? በተለይ ከሀገራዊ ለውጡ ወዲህ ያለው እንቅስቃሴ ተስፋ ሰጪ ነው የሚል ምላሽ መስጠት በቂ ነው፡፡ ለዚህ አቅም እየሆኑ ካሉ የትምህርት ተቋማት መካከል ተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ አንዱ ነው፡፡

ከማስተማር ልምድ ባሻገር በርካቶችን የሙያ ባለቤት ለማድረግ በሚደረገው ጥረት የአሰልጣኞች ሚና እጅግ የላቀ ነው፡፡ ይህንን ያልንበት ምክንያት እንደ ተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ በመሳሰሉ የማሰልጠኛ ተቋማት የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በመፍጠር ረገድ እንደ ሀገር እያበረከቱት ያለው ሚና ከፍተኛ በመሆኑ ነው፡፡ በርካቶችን የሙያ ባለቤት ያደረገው ኮሌጁ ለፈጠራ ብሎም ለቴክኖሎጂ ስራዎች ትኩረት ሰጥቶ የተለያዩ ስራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡

ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጁ በበርካታ የትምህርት መስኮች ስልጠናዎችን ለተማሪዎቹ ይሰጣል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ችግር ፈቺ፣ ሀገር ከጎደላት ላይ የሚሞላ፣ ትውልድን በማብቃት ረገድ በርካታ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል፡፡ በኮሌጁ የቴክኖሎጂ ዲዛይንና አዋጭነት የማረጋገጥ የስራ ክፍል አስተባባሪ የሆኑት አቶ አሰፋ ዳኜ ከዝግጅት ክፍላችን ጋር በነበራቸው ቆይታ፤ በርካታ የቴክኖሎጂ እና የፈጠራ ስራዎች በኮሌጁ እየተሰራ፣ ወደ ኢንተርፕራይዞች የማስተላለፍ ስራም በስፋት እየተከናወነ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

እንደ አቶ አሰፋ ገለፃ፤ የውስጥ አቅምን በማሳደግ፣ ሀገራዊ ተልዕኮን ለማሳካት በሚደረገው ጥረት በፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆች የሚሰጡ የንድፈ ሃሳብ እና የተግባር ልምምድ ስልጠናዎች በሀገር ሁለንተናዊ እድገት ላይ አበርክቷቸው እጅግ የላቀ ነው። በተለይም ለኤግዚቢሽንና ለውድድር ተብለው የሚዘጋጁ የቴክኖሎጂ እና የፈጠራ ውጤቶች አቧራቸውን አራግፈው ጥቅም እንዲሰጡ፣ የፈጠራ ባለሙያዎችን ብቃትና ክህሎት እንዲተዋወቁ፣ የውስጥ አቅምን እንዲደግፉ እንዲሁም የኢንተርፕራይዞች ምርታማነታቸው እንዲጨምር ትልቅ አቅም እየፈጠረላቸው ይገኛል፡፡

የተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ የቴክኖሎጂ ዲዛይንና አዋጭነት የማረጋገጥ የስራ ክፍል በተለይ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ውስጥ የሚገኙ ኢንተርፕራይዞች ላይ የዳሰሳ ጥናት ያካሄዳል፡፡ በዚህም ለመስራት የታሰበውን የቴክኖሎጂ ውጤት አዋጭነቱን በመተንተን፣ በኮሌጁ ውስጥ ያሉ የስልጠና ክፍሎች የቴክኖሎጂ ውጤቶቹን እንዲሰሩ ፍቃድ ይሰጣል፡፡ ኢንተርፕራይዞቹ በሚፈለገው ልክ ምርትና ምርታማነታቸው እንዲጨምር የሚያስችል ማንኛውንም አገልግሎት በቴክኖሎጂ ለመደገፍ ያስችል



ፎቶ፡- በገነት ወንድሙ

በኮሌጁ የተሰራ የመኖ ማቀነባበሪያ ማሽን

> **የተሰሩ በርካታ የምርትና የማምረቻ ቴክኖሎጂዎች ወደ ኢንተርፕራይዞቹ ተሸጋግረው የውጪ ምንዛሬ ከማስቀረት ባሻገር ዜጎች ሀገራዊ ምርቶችን በማምረት የኢኮኖሚ አቅማቸውን ለማሳደግ አበርክቷቸው የጎላ ነው**

ዘንድ አዋጭ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን በኮሌጁ የሚገኙ አሰልጣኞች አማካኝነት ይሰራሉ፡፡ አሰልጣኞች እንደየ ዘርፋቸው የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ተደራሽ በማድረግ የኢንተርፕራይዞችን የምርት መጠን ለማሳደግ እንደሚሰሩ ጭምር አስታውቀዋል፡፡

እስካሁን በፖሊ ቴክኒክ ኮሌጁ አሰልጣኞች የተሰሩ የቴክኖሎጂ የፈጠራ ስራዎችን በተመለከተ አቶ አሰፋ ሲያስረዱ፤ ከተሰሩት በርካታ የቴክኖሎጂ ፈጠራ ውጤቶች መካከል፡- የወተት ማርጊያ እና የአፈር ማዳበሪያ ማምረቻ ማሽኖች ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ የፈጠራ ውጤቶች በኮሌጁ አሰልጣኞች ተሰርተው ለኢንተርፕራይዞች የተሸጋገሩ ናቸው። በተጨማሪም፤ የከተማ ግብርና ዘርፉን ለማሳደግ በሚደረገው ጥረት የመኖ ማቀነባበሪያ ማሽን በመስራት በኮሌጁ ለሚገኙ ዶሮዎችና ላሞች የተመጣጠነ መኖ ለማዘጋጀት ተችሏል፤ በቀጣይም ለኢንተርፕራይዞች የማሸጋገር ስራ እንደሚሰራ ጠቁመዋል፡፡

በኮሌጁ የቴክኖሎጂ ዲዛይንና አዋጭነት የማረጋገጥ የስራ ክፍል አስተባባሪው እንዳስረዱት፤ የተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ችግር ፈቺ የሆነውን የመኖ ማቀነባበሪያ ማምረቻ ማሽን ለመስራት ከየዲፓርትመንቱ የተውጣጡ አሰልጣኞችን በማቀናጀት ወደ ስራ አስገብቷል፡፡ በዚህም መሰረት ምርቱን ለማምረት የተሳተፉ አካላት የብረታ ብረት፣ የሜካኒክስ፣ የኤሌክትሪካል ኤሌክትሮኒክስ፣ የአውቶ እንዲሁም የከተማ ግብርና የትምህርት ክፍሎች አሰልጣኞች በ2017 ዓ.ም የመኖ ማቀነባበሪያ ማምረቻውን ሰርተውታል፡፡ በፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚገኙ ዶሮዎችና ላሞች በመኖ ማቀነባበሪያ አማካኝነት የተዘጋጀውን መኖ እንደሚጠቀሙ ጭምር አስታውቀዋል፡፡

”የመኖ ማቀነባበሪያ ማምረቻው ከውጭ ሀገር ገዝተን ብናስገባ 1 ነጥብ 1 ሚሊየን ብር ያስወጣን ነበር” ያሉት አቶ አሰፋ፤ ነገር ግን የፈጠራ ስራው በኮሌጁ አሰልጣኞች መሰራት በመቻሉ ቴክኖሎጂውን ለማምረት የፈጀው ገንዘብ 600 ሺህ ብር ብቻ ሊሆን ችሏል፡፡ ይህ ቴክኖሎጂ በተግባር ተፈትሾ ውጤታማነቱ የተረጋገጠ ሲሆን፤ 100 ኩንታል የሚሆን ለመኖ ማቀነባበሪያነት የሚውል ግብዓትን በ30 እና በ40 ደቂቃ ውስጥ አድቅቆ የማውጣት አቅም እንዳለው አስረድተዋል፡፡

በተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ የከተማ ግብርና ትምህርት ክፍል የእንስሳት እርባታ አሰልጣኝ የሆኑት ወይዘሮ ባንቺአየሁ ጌታሁን እንዳብራሩት፤ የከተማ ግብርና ስራ ደጋፊ አንድ አካል የሆነው የመኖ አቅርቦት ነው፡፡ አንድ በከተማ ግብርና ዘርፍ ተሰማርቶ የሚሰራ አካል እንስሳትን ለማደለብ፣ የወተት ምርት ለማግኘት እንዲሁም ደግሞ የእንቁላል ጣይ ዶሮዎችን በስፋት ምርት እንዲሰጡ ለማስቻል በዋናነት ከእንስሳት ምርት ጋር በተያያዘ የመኖ አቅርቦት ትልቁን ስፍራ ይይዛል ብለዋል፡፡

እንደ ተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ የወተት ላም እና የእንቁላል ጣይ ዶሮዎች እርባታ ሥራዎች በመከናወን ላይ ናቸው። ምርት በሚፈለገው ልክ ለማግኘት ከዚህ ቀደም መኖ ከውጭ በመግዛት ይጠቀሙ ነበር፡፡ ከዋጋ እንዲሁም ከጥራት አንፃር የመኖ ምርት ላይ የተወሰነ ክፍተት የታየ መሆኑን ተከትሎ ወደ መፍትሔው ለማቅናት በተደረገው ጥረት የመኖ ማቀነባበሪያ ማምረቻ ማሽን በውስጥ አቅም መስራት ላይ ደርሰዋል፡፡

እንደ ወይዘሮ ባንቺአየሁ ገለጻ፤ ለእንቁላል ጣይ ዶሮዎች የሚዘጋጀው መኖ ከውሃ ውጪ፤ በቆሎ፣ ፉጉሎ፣ ጨው፣ ፍሩሽካ እና ሌሎች ንጥረ ነገሮችን የያዘ መሆን አለበት፡፡ የሚቀነባበረውም ምግብ ሳይንሳዊ ሂደቱን መከተል ያስፈልገዋል፡፡ ከዚህ ቀደም ለእንስሳቱ የሚሆነውን መኖ ለመሸመት 100 ኪሎውን በአራት ሺህ ብር ይገዙ ነበር፡፡ አሁን ግን በውስጥ አቅም የመኖ ማቀነባበሪያ ማምረቻ ከተሰራ በኋላ አስፈላጊ የሆኑ የመኖ ግብዓቶችን በመግዛት በባለሙያ የተመጣጠነ ምርት በማምረት ላይ እንደሚገኙ አስረድተዋል፡፡

ምንም እንኳን ለእንቁላል ጣይ ዶሮዎች የሚሆነውን ምርት በኮሌጁ ማምረት ከተጀመረ አንድ ወር የተቆጠረ ቢሆንም በዶሮዎች ባህሪ ላይ ጥሩ ለውጥ ስለመታየቱ ገልፀዋል፡፡ ከዚህ ቀደም ዶሮዎቹ እርስ በእርስ ይነካከሱ ነበር፡፡ ለዚህም እንደ ምክንያት የሚሆነው ደግሞ የፕሮቲን እጥረት መከሰቱን ተከትሎ ይሁን እንጂ አሁን ላይ ዶሮዎቹ በጥሩ ጤንነት ላይ ይገኛሉ፡፡ በእንቁላል ምርታቸውም ላይ በመቶ እጥፍ ጭማሪ አሳይተውናል የሚሉት ወ/ሮ ባንቺአየሁ እንደ ተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ቁጥራቸው 750 ዶሮዎች ስለመኖራቸው አስታውቀዋል፡፡

በተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን እና ቴክኖሎጂ ሽግግር ምክትል ዲን አቶ ወንድም ሲያምረኝ ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፁት የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ አገልግሎት ተልዕኮውን ያደረገው በአካባቢው የሚገኙ ጥቃቅንና አነስተኛ፣ መካከለኛ እንዲሁም በኢንተርፕራይዝ ተደራጅተው የሚሰሩ ድርጅቶችን ሙያዊ ድጋፍ ከኮሌጅ ውጪ ሄዶ መስጠት ነው። ከሚሰጡ ድጋፎች መካከል የመዝገብ አያያዝ፣ የካይዘን ምርትና ምርታማነትን የማሻሻል የስነ ዘዴ ስልጠና ድጋፍ መስጠት፣ ኢንተርፕራይዞቹ ተሰማርተው በሚሰሩበት ስራ ሙያዊ ስልጠና እና ድጋፍ መስጠት እንዲሁም የኢንተርፕራይዞችን ምርትና ምርታማነታቸውን ለማሳደግ የሚረዱ፣ የውጪ ምርቶችን የሚተኩ እና የውጭ ምንዛሬን የሚያስቀሩ ቴክኖሎጂዎችን በኮሌጅ አሰልጣኞች አቅም ተሰርተው ወደ ኢንተርፕራይዞች እንዲሸጋገሩ ማስቻል ላይ እንደሚያተኩር አብራርተዋል፡፡

እንደ አቶ ወንድሙ ገለፃ፤ ወቅቱ የእውቀት፣ የፈጠራና የቴክኖሎጂ ስራዎች የሚበረታታበት መሆኑን ተከትሎ በርካታ ስራዎች ተከውነዋል፡፡ በአሰልጣኞች የተሰሩ ቴክኖሎጂዎች በተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ውስጥ ተፈትሸው ውጤታማ መሆናቸው ሲረጋገጥ በአካባቢው የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ ማዕቀፍ የተያዙ ኢንተርፕራይዞች ላይ ሽግግር ይፈፀማል፡፡ እንደ ኮሌጁ ተጨባጭ ሁኔታ ከተሰሩ የቴክኖሎጂ ፈጠራ ስራዎች መካከል የእርጎ ማርጊያ ማሽን ተጠቃሽ ነው፡፡ የመስሪያ ማሽኑም በከተማ ግብርና ዘርፍ ተሰማርቶ ለሚሰራ ኢንተርፕራይዝም ተሸጋግሯል፡፡ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በሚደረገው ጥረት የቴክኖሎጂ ውጤቶች አይተኬ ሚናቸውን እየተጫወቱ ይገኛል ብለዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ኮሌጁ በራሱ ተጠቃሚ የሚሆንበትን ስራ ከመስራት አንጻር በከተማ ግብርና ስልጠና ዘርፍ ላይ እያገለገለ የሚገኘውን የእንስሳት መኖ ማቀነባበሪያ አንዱ ስለመሆኑ የሚናገሩት አቶ ወንድሙ የማቀነባበሪያ ማሽኑ ስራ ላይ መዋሉን ተከትሎ በወር ብቻ ከ500 ሺህ ብር በላይ ለማዳን ስለመቻሉ አንስተዋል፡፡ በተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ የተሰሩ በርካታ የምርትና የማምረቻ ቴክኖሎጂ ስራዎች ወደ ኢንተርፕራይዞቹ ተሸጋግረው የውጪ ምንዛሬ ከማስቀረት ባሻገር ዜጎች ሀገራዊ ምርቶችን በማምረትና የኢኮኖሚ አቅማቸውን ለማሳደግ አበርክቷቸው የጎላ ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# የተቋማት የከተማ ግብርና አስተዋጽኦ እስከምን?

- በአዲስ አበባ ከተማ 2 ሺህ 599 የመንግስት፣ የግል እና የኃይማኖት ተቋማት በከተማ ግብርና ተግባር ላይ መሰማራታቸው ተጠቁሟል
- በዓመቱ በሰብል እና በዕፅዋት ልማት ከ152 ሺህ 633 ቶን በላይ ምርት እንደሚገኝ ተመላክቷል

በይግለጡ ጓዴ





ፎቶ- ከገፀ ድር

በአዲስ አበባ የሚገኙ መንግስታዊና የግል ተቋማት ባላቸው ክፍት ቦታ የተቀናጀ የከተማ ግብርና ተግባር በማከናወን ላይ ይገኛሉ

የመንግስት እና የግል ተቋማት ባላቸው ክፍት ቦታዎች ላይ የከተማ ግብርናን ተግባራዊ ማድረግ ከጀመሩ ሰነባብተዋል። በተለይ በጓሮ አትክልት፣ በፍራፍሬ ልማት፣ በእንስሳት እርባታ፣ በዶሮ፣ በከብት ማድለብ እና በንብ ማነብ ዘርፎች አመርቂ ውጤት ያገኙም አሉ። እነዚህ ተቋማት የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ እና የስራ እድል በመፍጠር ረገድም ትርጉም ያለው አስተዋፅኦ ማድረግ ችለዋል፡፡ ‘ሰላም ሮሲዲ ህፃናት ማሳደጊያ ኮሌጅ’ ከእነዚህ ተቋማት አንዱ ነው፡፡

በኮተቤ አካባቢ የሚገኘው ‘ሰላም ሮሲዲ ህፃናት ማሳደጊያ ኮሌጅ’ በግቢው ውስጥ የተቀናጀ የከተማ ግብርና ስራን ያከናውናል፡፡ በተለያዩ የጓሮ አትክልቶች እና እንስሳት እርባታን በማከናወን ተጠቃሚ ሆኗል፡፡

ተቋሙ ባለው 10 ሄክታር መሬት እንደ ሰላጣ፣ ቲማቲም፣ ቀይ ሽንኩርት፣ ነጭ ሽንኩርት፣ ቆስጣ፣ ጥቅል ጎመን፣ ባሮ ሽንኩርት፣ ፎሶሊያ የመሳሰሉ የጓሮ አትክልቶችን ያመርታል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎንም የእንስሳት ሃብት ልማት፣ የንብ ማነብ ተግባር፣ የዓሳ እና የዶሮ እርባታን ያከናውናል፡፡

ምርቱን በግቢው ውስጥ በሚገኘኝ የህጻናት መንደር የሚውሉ ህፃናትን ይመግብበታል፡፡ ይህም ህፃናቱ ተፈጥሯዊ ሂደትን በጠበቀ ጤናማ መንገድ የተመረተ ምግብ እንዲያገኙ አስችሏቸዋል፡፡ አብዛኛውን ምርት ለተቋሙ ሰራተኞች እና ለአካባቢው ነዋሪዎች በተመጣጣኝ ዋጋ ይሸጣል፤ በዚህም የተቋሙን ገቢ ይደጉማል፡፡

በ‘ሰላም ሮሲዲ ህፃናት ማሳደጊያ ኮሌጅ’ ባልደረባ የሆኑት አቶ በለጠ አመነ፣ የከተማ ግብርና ተግባራዊ መሆን ከጀመረ ወዲህ የተቋሙን ክፍት ቦታ ጥቅም ላይ በማዋል በርካቶችን ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን ተናግዋል፡፡ የወረዳ እና የክፍለ ከተማ አርሶ አደር እና የከተማ ግብርና ልማት ፅሕፈት ቤት ባለሙያዎች ሙያዊ፣ የምርጥ ዘር፣ የማዳበሪያ፣ የሞተር ፓምፕና ሌሎች ድጋፎችን የሚያደርጉላቸው መሆኑ ውጤታማ እንዳደረጋቸው ገልፀዋል፡፡

ለከተማ ግብርና ስራ የከርሰ ምድር እና የገጸ ምድር ውሃ በመጠቀም ላይ የሚገኘው ሰላም ሮሲዲ ህፃናት ማሳደጊያ ኮሌጅ በዓመት ከሁለት ጊዜ በላይ ምርት ይሰበስባል፡፡ የከተማ ግብርና በትኩረት ከተሰራበት ከራስ የምግብ ፍጆታ አልፎ ወደ ገበያ በማቅረብ ዜጎችን ተጠቃሚ በማድረግ እና ገቢን ለማሳደግ እንደሚያግዝ አቶ በለጠ ይናገራሉ፡፡

የከተማ ግብርና የከተማዋ ነዋሪዎች ባላቸው ትንሽ ቦታ በጓሮ አትክልት እና በእንስሳት እርባታ በማከናወን ተጠቃሚ እንዲሆኑ እና የዜጎች ህይወት እንዲቀየር ማስቻሉን ይናገራሉ፡፡

የደጃዝማች ወንድይራድ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተቀናጀ የከተማ ግብርና ስራን ተግባራዊ በማድረግ ላይ የሚገኝ ሌላኛው ተቋም ነው፡፡ በትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ተገኝተን ባደረግነው ቅኝት፣ በጥሩ ይዞታ ላይ የሚገኙ ስድስት የወተት ላሞችን እና አምስት የደለቡ ከብቶችን አይተናል። በእንክብካቤ ስራው ተሰማርተው ያገኘናቸው አቶ አድማሱ አለምነው፣ በቀን 2 ጊዜ ወተት እንደሚታለብ ይናገራሉ፡፡

የደጃዝማች ወንድይራድ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ምክትል ርዕሰ መምህር ኬንቦ ተስፋዬ በትምህርት ቤቱ ግቢ ውስጥ የተቀናጀ የከተማ ግብርና ስራ ተግባራዊ መደረጉ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የተማሩትን ትምህርት ወጥተው ለተግባር እንዲማሩበት በማስቻሉ የትምህርት ጥራቱን ማሳደጉን ገልፀዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የከተማ ግብርና በትምህርት ቤቶች አንድ የትኩረት መስክ ሆኖ ተግባራዊ እንዲደረግ ባስቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ትምህርት ቤቱም ይህንኑ እየተገበረ መሆኑን መምህር ኬንቦ ተናግረዋል፡፡

በትምህርት ቤቱ ግቢ ውስጥ ከብት የማድለብ፣ የወተት ላም፣ የበግና የፍየል እርባታ፣ ንብ ማነብ እንዲሁም ዶሮ የማርባት ተግባር ይከናወናል፡፡ በተጨማሪም ጎመን፣ ነጭ ሽንኩርት፣ ዝኩኒ፣ የአበባ ጎመን፣ ቀይ ስርን የመሳሰሉ የጓሮ አትክልቶች ይመረታሉ፡፡ ምርቶቹ ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ እና ለአካባቢው ነዋሪዎች በተመጣጣኝ ዋጋ ይሸጣል፤

ማህበረሰብ ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን መምህሩ ይናገራል፡፡ በአነስተኛ ዋጋ ጥራት ያለው የጓሮ አትክልት፣ የወተት እና የስጋ ምርት በማቅረብ ላይ መሆናቸውን ርእሰ መምህሩ ይገልጻሉ፡፡

ርእሰ መምህር ኬንቦ ትምህርት ቤቱ የከተማ ግብርና ተግባራዊ በማደረግ ከመማር ማስተማር ባለፈ መምህራንን እና የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ በአነስተኛ ዋጋ ተጠቃሚ በማድረግ የኑሮ ውድነቱን ጫና ማቃለል መቻሉን አስታውቀዋል። በቀጣይም በትምህርት ቤቱ የተቀናጀ የከተማ ግብርና በተጠናከረ መልኩ ተግባራዊ በማድረግ የትምህርት ቤቱን ገቢ ለማሳደግ እንደሚሰራ መምህሩ ገልፀዋል፡፡

በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 11 የአርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ጽህፈት ቤት ኃላፊ ሻንበል ዳባ ዋካ እንደ ትምህርት ቤቶች፣ የእምነት ተቋማት፣ የፖሊስ ጣቢያዎችን በመሳሰሉ የመንግስት እና የግል ተቋማት የከተማ ግብርና ስራን በማከናወን አበረታች ውጤት እየተገኘ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በወረዳው በእንስሳት እና በእጽዋት ዘርፍ እየተተገበረ በሚገኘው የከተማ ግብርና ስራ 22 ተቋማት ተሳትፈዋል፤

> “በአዲስ አበባ ከመኸር እርሻ ብቻ 92 ሺህ 328 ነጥብ 22 ቶን አትክልት፣ 140 ቶን ፍራፍሬ እና 18 ሺህ 608 ነጥብ 68 ቶን ሰብል ይገኛል፤ ከበጋ ስንዴ ደግሞ 175 ነጥብ 50 ቶን ምርት ይገኛል”

በግለሰብ ደረጃም 4 ሺህ ተጠቃሚዎች ተሳትፎ በማድረግ ላይ ይገኛሉ። በወረዳው በክላስተር ሼድ ጭምር የዶሮ፣ የእንቁላል፣ የከብት ማድለብና የወተት ከብት ልማት ተግባር እየተከናወነ እንደሚገኝ ኃላፊው አክለው ገልፀዋል፡፡

በወረዳው የደጃዝማች ወንድይራድ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ የደጃዝማች ወንድራይድ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ‘ሰላም ሮሲዲ ህፃናት ማሳደጊያ ኮሌጅ’ በተቀናጀ የከተማ ግብርና በእንስሳት እና በእጽዋት ዘርፍ እንደ ሞዴል የሚወሰዱ ተቋማት መሆናቸውን ሻንበል ዳባ ይገልጻሉ። የከተማ ግብርና በስጋ፣ በወተት፣ በእንቁላል እና በጓሮ አትክልት ልማት ዘርፍ መንግስት የምግብ ሉዓላዊነት ለማረጋገጥ ከሚሰራቸው ስራዎች አንጻር ትልቅ አጋዥ መሆኑን ኃላፊው ይናገራሉ።

የተቋማትን የከተማ ግብርና ተሳትፎ በወረዳው ለማሳደግ የግብዓት፣ የዘር፣ የሙያ ድጋፍ እና ክትትል ስራዎች እየተሰራ መሆኑን አስታውቋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን የእጽዋት ዘርፍ ተወካይ ዳይሬክተር አቶ ሲሳይ እንሴኔ በከተማዋ በከተማ ግብርና ዘርፍ የተለያዩ የመንግስት እና የግል ተቋማት ተሳትፎ እያደረጉ መሆኑን ጠቁመው፣ መንግስት የሰጠውን ትኩረት መሰረት በማድረግ የከተማዋ አመራር እና ባለሙያዎች ጉዳዩን በባለቤትነት ይዘው በመስራታቸው አመርቂ ውጤት ተገኝቷል ብለዋል፡፡

እንደ አቶ ሲሳይ ገለጻ፣ በከተማዋ 261 የኃይማኖት ተቋማት፣ 395 የመንግስት ትምህርት ቤቶች እና 353 የግል ትምህርት ቤቶች በከተማ ግብርና ስራ ላይ ተሰማርተዋል፤ ተሳትፎ በመደረግ ላይ ይገኛሉ፡፡

በተጨማሪም 105 የመንግስት ጤና ጣቢያዎች እና 36 የግል የህክምና ተቋማት የከተማ ግብርናን ተግባራዊ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡

በከተማዋ በሚገኙ 602 የመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ 28 የቴክኒክ እና ሙያ ተቋማት፣ 128 የፌደራል ተቋማት፣ 25 ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣ 364 የግል ድርጅቶች በከተማ ግብርና ስራ ላይ ተሳታፊ መሆናቸውን አቶ ሲሳይ ይጠቁማሉ፡፡

በአጠቃላይ በከተማዋ 2 ሺህ 599 የኃይማኖት፣ የመንግስትና በግል ተቋማት በከተማ ግብርና ተግባር ላይ መሰማራታቸውን የጠቆሙት አቶ ሲሳይ፣ ዘርፉን ውጤታማ ለማድረግም የሙያ፣ የግብዓት፣ የቴክኖሎጂ እና የዘር አቅርቦት ድጋፍ እየተደረገ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

እንደ አርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን መረጃ በከተማዋ ከመኸር እርሻ 18 ሺህ 608 ነጥብ 68 ቶን ሰብል፣ ከግቢና ከጓሮ አትክልት 41 ሺህ 374 ነጥብ 88 ቶን፣ ከማሳ አትክልት ልማት 92 ሺህ 328 ነጥብ 22 ቶን፣ ከእንጉዳይ ምርት ደግሞ 6 ነጥብ 16 ቶን፣ ከፍራፍሬ 140 ቶን እንዲሁም ከበጋ ስንዴ 175 ነጥብ 50 ቶን ምርት እንደሚገኝ ተገምቷል። በጥቅሉ በዓመቱ ውስጥ በሰብል እና በዕፅዋት ልማት 152 ሺህ 633 ነጥብ 44 ቶን ምርት እንደሚገኝ ተመላክቷል፡፡

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# ባዮ ጋዝ፡- የከተማዋ ሌላኛው አማራጭ የኃይል ምንጭ

• የኢነርጂ አጠቃቀምን የሚመለከት የፖሊሲ ማዕቀፍ እየተዘጋጀ መሆኑ ተገልጿል

በሰይላ መሀመድ

ወይዘሮ ሀይማኖት ንጉሴ በወተት ላም እርባታ የተሰማሩ ሲሆኑ በተጓዳኝ ከብቶቹ የሚያስወግዱትን ቆሻሻ የባዮ ጋዝ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ሀይል እያመረቱ ይገኛሉ፡፡ ወይዘሮዋ የባዮ ጋዝ ቴክኖሎጂ መተግበር መቻላቸው አንድ የሀይል አማራጭ ሆኗቸዋል። የባዮ ጋዝ ቴክኖሎጂን ተጠቅመው ያመረቱትን 10 ሜትር ኪዩብ ሀይል በቤት ውስጥ ለምግብ ማብሰያነት፣ ለወተትና የወተት ተዋጽኦዎች ማቀዝቀዣነት እንደሚጠቀሙ ነው የሚናገሩት፡፡

በወተት ላም እርባታ እንደመሰማራታቸው የሚያመርቱት ወተትና የወተት ተዋጽኦዎች አልፎ አልፎ የሚያጋጥመው የመብራት ሀይል መቆራረጥ እንዳያበላሽባቸው ትልቅ እገዛ እያደረገላቸው ስለመሆኑም ወይዘሮዋ ጠቅሰዋል፡፡ በቀጣይም ከቴክኖሎጂው የሚገኘውን ሀይል በማስፋት በዋናነት መብራትን ጨምሮ ለተለያዩ ብዙ ሀይል ለሚጠይቁ እንደ ምጣድ ለመሳሰሉ ነገሮች እንዲውል ለማድረግ ማቀዳቸውንም አክለዋል፡፡

አቶ ዳዊት ሲሳይ “ትክክል” በሚል ስያሜ የሚጠራውን የተሻሻለ ማገዶ ቆጣቢ ምድጃ አምራች ናቸው፡፡ አቶ ዳዊት ስለሚያመርቱት ምድጃ ሲገልጹ፤ ጭስ እንዳይፈጥር፣ ሀይል እንዳይባክን አጠቃላይ ምድጃው ላይ የሚፈጠረው ሙቀት ሙሉ በሙሉ ወደ ሀይል መቀየር የሚያስችል ነው፡፡ ከ65 በመቶ በላይ ሀይል የሚቆጥብ ነው፡፡ ይህም ሲባል ለምሳሌ 100 ብር ይፈጅ የነበረን ሀይል በ35 ብር መጠቀም እንደማለት ነው። “ትክክል” ማገዶ ቆጣቢ ምድጃ ሲጠና ይህንን መስፈርት የሚያሟላ ነው። ወደፊትም አካባቢን የማይበክሉ ምድጃዎች ተመርተው ለማህበረሰቡ ተደራሽ እንዲሆኑ መንግስት በተለይም የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ተገቢውን ድጋፍ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ለአምራቹ አሁን እየተደረገለት ካለው ድጋፍ በተጨማሪ የማምረቻና የማሳያ ቦታ ሊመቻችለት ይገባል፡፡

ባዮ ኢነርጂ ምን ማለት ነው? የባዮ ኢነርጂ ቴክኖሎጂን ማስፋት ጥቅሙ ምን እንደሆነ በአዲስ አበባ ከተማ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የባዮ ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ማሻሻልና ማስፋፋት ቡድን መሪ አቶ እንዳለ ፍቃዱ ለዝግጅት ክፍላችን ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡ ቡድን መሪው በሰጡት ማብራሪያ፤ ባዮ ኢነርጂ ማለት ከኢነርጂ ክፍሎች አንዱ ነው፡፡ ከተለያዩ ነገሮች የሚፈጠር ሀይል ነው፡፡ ለምሳሌ ከስኳር ፋብሪካ የሚገኘው ኢታኖል አንዱ ነው፡፡ ባዮ ኢነርጂ ከተለያዩ ፍራፍሬዎች፣ እጽዋት እና ደረቅ ቆሻሻ የሚዘጋጅ ከሰል ተጠቃሽ ናቸው፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን አንዱ ተግባርና ኃላፊነት ማህበረሰቡን ከብክለት ለመከላከል የተፈጥሮ ኃብቶችን የመጠበቅ ስራ ነው፡፡ በመሆኑ እነዚህ የኢነርጂ አይነቶች ብክለትን የሚከላከሉ ናቸው። እነዚህን አማራጭ የኢነርጂ አይነቶች ማህበረሰቡ እየተጠቀመ ሲሄድ የደን መጨፍጨፍን ያስቀራል፡፡ ምክንያቱም የደን መጨፍጨፍ የሚከሰተው ህብረተሰቡ መብራት በማይኖርበት ወቅት የእለት ተእለት ኑሮውን ለመግፋት ሲል የተለያዩ የሀይል አማራጮችን መጠቀም ስላለበት እና እንጨትና ከሰልን ባልተሻሻሉ ምድጃዎች ለምሳሌ በባህላዊው ሶስት ጉልቻ ለማብሰያነት ስለሚጠቀም ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ቡና ለማፍላት ከሰል ይጠቀማል፡፡ ሰዎች ድግስ ሲኖራቸውና ከተሞች አካባቢ ላይ ሆቴሎች ለምግብ ማብሰያነት እንጨት ሲጠቀሙ ይስተዋላል፡፡ ማህበረሰቡ ዘልማዳዊ በሆኑት ሶስት ጉልቻና ከሰል ማንደጃ ምድጃዎች በሚጠቀምበት ወቅት ያልተሻሻሉና ማገዶ ቆጣቢ ባለመሆናቸው ብዙ ከሰልና እንጨት ይፈጃሉ፡፡

እንደ ቡድን መሪው ገለጻ፤ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ይህንን ችግር ለመፍታት የተሻሻሉ ማገዶ ቆጣቢ ምድጃዎችን ለማህበረሰቡ ማስተዋወቅ ላይ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ነው፡፡ ሌላው አብዛኛውን ጊዜ ማህበረሰቡ የሚጠቀመው ከሰል ደንን በመጨፍጨፍ በመሆኑ ይህንንም ችግር ለማስቀረት የተለያዩ የፍራፍሬ ተረፈ ምርቶችን እና በየቤቱ የሚመነጭ ደረቅ ቆሻሻን ለምሳሌ የሙዝ ልጣጭ፣ የአቦካዶ ፍሬ ወዘተ በማክሰል ጥቅም ላይ እንዲውሉ የማድረግ ስራ እየተሰራ ነው፡፡ ይህም ደን በመጨፍጨፍ የሚገኘውን ሀይል ቆሻሻን በመሰብሰብና በማክሰል ለማግኘት ያስችላል፡፡ ይህ የደን መጨፍጨፍን ከማስቀረቱም በተጨማሪ ሌሎች መሰል ችግሮችን ይቀርፋል፡፡

በሌላ በኩል በየቦታው የሚጣሉት የፍራፍሬ ተረፈ ምርቶችና ደረቅ ቆሻሻዎች አካባቢን በማቆሸሽና በመበከል በማህበረሰብ ጤና ላይ ችግር እንዳያመጡ ያደርጋሉ፡፡ በተለይም ቆሻሻዎቹ በየቦታው በሚጣሉበት ወቅት ሚቴን ጋዝ በማመንጨት የሚያስከትሉትን የአካባቢ ብክለት ተጽዕኖ ይቀንሳሉ፡፡ ቆሻሻዎቹ ተሰብስበው ወደ ከሰልነት በሚቀየሩበት ወቅት ወደ ከባቢ አየር የሚለቀቀውን ሚቴን ጋዝ ወደ ካርቦንዳይአክሳይድ ይቀይረዋል፡፡ በተለምዶ ከሰል የሚከሰለው ደን አካባቢ በመሆኑ የሚፈጠረውን ካርቦንዳይአክሳይድ ዛፎች ይጠቀሙታል፡፡ ይህ ቆሻሻን ወደ ከሰል የመቀየር ቴክኖሎጂ በአሁኑ ወቅትም በተለያየ መጠንና ቅርጽ ተዘጋጅተው በትላልቅ ሱፐርማርኬቶች ውስጥ እንደሚገኙና ለአገልግሎት እየዋለ መሆኑንም ነው ቡድን መሪው አቶ እንዳለ የገለጹት፡፡

ደረቅ ቆሻሻን ወደ ሀይል መቀየር የአየር ንብረት ለውጥን በመከላከል ረገድ ሚናው ከፍተኛ በመሆኑ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በማህበረሰቡ ዘንድ ግንዛቤ የመፍጠር ስራ እየሰራ ነው፡፡ ከውጭ ሀገር ይህንን ከቆሻሻ ከሰል የማምረት ልምድ ይዘው



ፎቶ ከፋይል

በባዮ ጋዝ ቴክኖሎጂ አማካኝነት የተገኘ ኃይል ለምግብ ማብሰያ አገልግሎት ሲያገለግል

በመምጣትና በመተግበር ዘርፉን እያስተዋወቁ የሚገኙ ግለሰቦችም አሉ፡፡ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ከውሀና ኢነርጂ ሚኒስቴር ጋር በመሆን የተመረተውን ከሰል ይፈትሻል፡፡ በትክክል ከቆሻሻ ተመርቷል ወይ? ከጥራት አንጻርም በውስጡ ምን ያህል እርጥበት አለው? ምን ያህል ጭስ ሊወጣው ይችላል? እርጥብ ከሆነ ጭስ የማውጣት አቅሙ ከፍተኛ ነው? ምን ያህል መጠን (density) አለው? የሚለውንና ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት አጠቃላይ የሀይል መጠኑ ምን ያህል እንደሆነ በቤተ ሙከራ ይታያል፡፡ ይህም በተሻለ የጥራት ደረጃ የሚመረተው ከሰል የሚጠበቀውን ያህል ሀይል እንዲሰጥ በተሻሻሉ ማገዶ ቆጣቢ ምድጃዎች መጠቀም ወሳኝነት አለው፡፡

አሁን ላይ በከተማዋ መስፈርታቸውን ያሟሉ ማገዶ ቆጣቢ ወይም የተሻሻሉ ምድጃዎች ገበያ ላይ አሉ፡፡ ማገዶ ቆጣቢ ምድጃዎች የሚባሉት የውሀና ኢነርጂ ሚኒስቴር ብቁ መሆናቸውን ያረጋገጣቸውን ናቸው፡፡ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ማህበረሰቡ እነዚህን እንዲጠቀም የማስተዋወቅና ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ይሰራል፡፡ በተጨማሪም መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት ትክክለኛውን ቴክኖሎጂ ለማህበረሰቡ በመስጠት ጥቅሙን እንዲያውቅና ቴክኖሎጂው እንዲስፋፋ የማድረግ ስራ ይሰራል፡፡

ቴክኖሎጂውን ከውጭ ቀስመው የመጡ ግለሰቦች አምርተው ለገበያ የሚያቀርቧቸውን ማገዶ ቆጣቢ ምድጃዎችንም መስፈርታቸውን ያሟሉና እውቅና ያገኙ መሆን አለመሆናቸውን ባለስልጣኑ እንዲያስፈትሹ ያደርጋል፡፡ መስፈርታቸውን ያሟሉ ሲባል ምድጃዎቹ የሚሰጡት የሀይል መጠን ነው፡፡ በትንሽ ከሰል ብዙ ነገር መስራት መቻላቸው ነው፡፡ ምድጃው ከሰሉ ሳያልቅ ረጅም ጊዜ እንዲቆይ ያደርገዋል፡፡ ይህም ምድጃው የሚሰራው ከሸክላ በመሆኑ እንዴ ከጋለ ቶሎ አይበርድም፡፡ ሌላው አመድ የሚወጣባቸው ቀዳዳዎችም ተመጥነው የተሰሩ ናቸው፡፡ አሁን ላይ በተለምዶ የምንጠቀምበት ምድጃ ብዙ ከሰል አድርገን የሚሰጠን ጥቅም ግን ትንሽ ነው፡፡ ስለሆነም ማገዶ ቆጣቢዎቹን በማስተዋወቅ ያልሆኑትን የሚያመርቱት ወደዚህኛው እንዲመጡ ድጋፍና ክትትል ይደረጋል፡፡

ሌላው የባዮ ኢነርጂ ምንጭ የባዮ ጋዝ ቴክኖሎጂ ነው፡፡ የተለያዩ ሊበሰብሱ የሚችሉ ቆሻሻዎችን በተለይም እንስሳት የሚያስወግዱትን ለምሳሌ የከብት አዛባን ሰብስቦ ጉድጓድ ውስጥ አስገብቶ ያለኦክስጂን በማብላላት ሚቴን ጋዝ እንዲፈጠር የሚያደርግና ሀይሉን ለተለያዩ አገልግሎቶች እንዲውል የሚያስችል ዘዴ ነው፡፡ ለመብራት፣ ለምግብ ማብሰያነት አጠቃላይ ከኤሌክትሪክ የሚገኘውን ማንኛውንም አገልግሎት ማግኘት የሚያስችል ነው፡፡ ከባዮ ጋዝ ማምረት የሚገኘው ተረፈ ምርት ለተፈጥሮ ማዳበሪያነት ያገለግላል፡፡ ይህም ከውጭ ለማዳበሪያ ግዢ የሚውለውን የውጭ ምንዛሬ በማስቀረት ረገድ የራሱን አወንታዊ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

የተፈጥሮ ማዳበሪያን መጠቀም ሲቻል የአፈር ለምነትን ይጨምራል። ቴክኖሎጂው ረጅም ጊዜ ያስቆጠረ ቢሆንም በሚፈለገው ደረጃ ጥቅም ላይ እየዋለ አይደለም፡፡ ማህበረሰቡ ከዚህ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያለው ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ እንዲሆን ባለስልጣኑ ግንዛቤ የመፍጠር ስራ እየሰራ ነው፡፡ በተለይም በከብት ማርባት ለተሰማሩት ትኩረት ሰጥቶ ስልጠናዎችን ይሰጣል፡፡ በከተማዋ በከብት ማርባት የተሰማሩ በርካታ ግለሰቦችና ባለሀብቶች እንዲሁም ተቋማት ከባዮ ጋዝ የሚገኘውን ጥቅም በመገንዘብ ተግባራዊ ቢያደርጉት ራሳቸውንና አካባቢያቸውን አልፎ ተርፎም ሀገራቸውን ተጠቃሚ ማድረግ ይችላሉ ሲሉም ቡድን መሪው መክረዋል።

እስካሁን በተፈጠረው ግንዛቤ ከ100 የማያንሱ የባዮ ጋዝ ተጠቃሚዎች ይገኛሉ፡፡ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ግንዛቤ ከመፍጠር ባለፈ ለማሳያነት በሚሆን መልኩ ሞዴል የባዮ ጋዝ ቴክኖሎጂን በተለያዩ ቦታዎች በመገንባት የማስተዋወቅ ስራ እየሰራ ነው፡፡

ማህበረሰቡ የተለያዩ አማራጭ የኢነርጂ ምንጮችን መጠቀም ይኖርበታል፡፡ ለዚህ ደግሞ ማገዶ ቆጣቢ ምድጃ የሚያመርቱትንና ከቆሻሻ ከሰል የሚያመርቱ አካላትን ድጋፍ በማድረግ ወደተሻለው መንገድ እንዲመጡ የማድረግ ስራ እየተሰራ ነው። ማህበረሰቡ እነዚህን ቴክኖሎጂዎች እንዲጠቀም ማስቻል የአየር ንብረት ለውጥን ከመከላከል ባለፈ የሚኖረው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የከተማው የኢነርጂ አጠቃቀም ምን ይመስላል በሚል ፖሊሲ ለማዘጋጀት እየተጠና ነው፡፡ በሀይል አጠቃቀም ላይ ጥናት ማጥናት ብቻ ሳይሆን ችግሩን እንዴት ማስወገድ ይቻላል የሚለው ምላሽ ማግኘት ስላለበት ነው ፖሊሲ ማዘጋጀት ያስፈለገው ሲሉ ቡድን መሪው ገልጸዋል፡፡

ጥናቱ መካሄድ የጀመረው በአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በጀት በ2017 ዓ.ም ሲሆን፤ ከፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ጋር በመሆን ነው፡፡ የጥናቱ ግኝት እንደሚያሳየው፣ በሳምንት 4 ጊዜ ለ9 ሰዓታት ያህል የኤሌክትሪክ ሀይል ይቋረጣል፡፡ በየዓመቱ 757 ሰዎች በከሰል ጭስ ይሞታሉ፡፡ 114 ሺህ 88 ቶን ከሰል ወደ ከተማዋ ይገባል፡፡ ይህም የሚያሳየው ብዙ ዛፍ እንደሚጨፈጨፍ ነው፡፡ ይህ አማራጭ ኢነርጂን መጠቀም ግድ መሆኑን ያመላክታል፡፡ ብዙ ማገዶ የማይፈጁ የተሻሻሉ ማገዶ ቆጣቢ ምድጃዎችን ማሰራጨትና ከደረቅ ቆሻሻ ከሰል የማምረት ቴክኖሎጂን ማስፋትና ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡ ይህንን ችግርና መፍትሄ ያሳየው ጥናት ወደ ፖሊሲ ማእቀፍነት እየተለወጠ ነው፡፡

## አገልግሎትን... ከገጽ 6 የዞረ

### የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ምን ይላል?

በአዲስ አበባ ከተማ በመንግስት ተቋማት ፈጣን፣ ቀልጣፋና ፍትሀዊ አገልግሎት ለመስጠት በቴክኖሎጂ በመታገዝ እየተሰራ ይገኛል፡፡ በተለይ ባለፉት አምስት ዓመታት በተከናወነ ስራ 347 አገልግሎቶችን በኦንላይን መስጠት ተችሏል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ 107 የሚሆኑት በአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል አገልግሎት በኩል እየተሰጡ እንደሚገኙ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ሃላፊ አቶ አዋሌ መሀመድ ለዝግጅት ክፍላችን ተናግረዋል፡፡

ቢሮው የተቋማትን አገልግሎት አሰጣጥ የሚያዘምኑ ሲስተሞችን በውስጥ አቅምና በውጭ በማልማት ወደ ስራ እንዲገቡ እያደረገ ይገኛል፡፡ ህዝብ እሮሮ ያቀርብባቸው የነበሩ እንደ የሲቪል ምዝገባና ነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ፣ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ፣ የንግድ ቢሮ፣ የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን፣ የከነማ ፋርማሲ ያሉ ወደ ሰባት የሚደርሱ ተቋማት የሚሰጡ አገልግሎቶችን ቀልጣፋ ለማድረግ ቴክኖሎጂዎችን በማልማት ወደ ስራ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ በአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል አገልግሎቶችን በአንድ ማዕከል በቴክኖሎጂ በመታገዝ አገልግሎት የሚሰጥበት ስርዓት ተፈጥሯል፡፡ በዚህም ተገልጋዮች አገልግሎት ለማግኘት ያባክኑት የነበረውን ጊዜና ወጪ በመቆጠብ ትልቅ ለውጥ ማምጣት ተችሏል፡፡ ለምሳሌ፡- ቀናትን ይፈጅ የነበረው የመታወቂያ አገልግሎት በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ መስጠት ተችሏል፡፡ ከዚህ ባሻገር ተገልጋዮች ወደ ቢሮ ሳይመጡ ቤት ድረስ አገልግሎቱን የሚያገኙበት ስርዓት ለመፍጠር ወደ ስራ መገባቱን የቢሮ ኃላፊ ተናግረዋል፡፡

በአዲስ አበባ የመሬትና አስተዳደር ቢሮ በቅርቡ ወደ ስራ የገባው ሲስተም ምልልስን በመቀነስ፣ አገልግሎትን በአጭር ጊዜና ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ መስጠት ያስቻለ መሆኑን አቶ አዋሌ ይናገራሉ፡፡ በፊት በነበረው ሲስተም ካርታ ለማተም ረጅም ጊዜ የሚወስድና የሰው ንክኪውም ብዙ ነበር፡፡ አዲሱ ሲስተም ተገልጋዮች ቅድመ ሁኔታዎችን ካሟሉ በአጭር ጊዜ አገልግሎት ማግኘት የሚችሉበትን ሁኔታ በመፍጠር ለተገልጋዮች እፎይታን ፈጥሯል፡፡ ለምሳሌ፡- መፍትሔ ሳያገኙ ለብዙ ጊዜ የቆዩ አርሶ አደሮች የይዞታ ማረጋገጫ ማግኘት ችለዋል፡፡ የእዳ እገዳ አገልግሎት በደቂቃዎች መስጠት የሚቻልበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

አዲሱ የመሬት ሲስተም የተገልጋዮች ፋይል፣ ይዞታቸው የሚገኝበት ቦታና ዝርዝር መረጃ እንዲሁም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መረጃዎችን አካትቶ የያዘ ነው፡፡ ከዚህ ቀደም የአንዱ ይዞታ ሌላው ላይ ተደርጎ ይታይ ነበር፡፡ አሁን ላይ ያለው ሲስተም ይህንን መቀበል የማይችል መሆኑን አቶ አዋሌ አብራርተዋል፡፡

ከሲስተም መዘግየትና መቆራረጥ ጋር በተያያዘ ይታይ የነበረውን ችግር መቅረፍ እንደተቻለም አቶ አዋሌ ተናግረዋል። ለምሳሌ፡- ከዚህ ቀደም አንድ ካርታ ለማተም ብዙ ጊዜ ይወስድ ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት ግን የሲቲኔት ኔትዎርክ መሰረተ ልማት ወደ ስራ በመግባቱ እና የባንድዊድዝ መጠንን በማሳደግ የመቆራረጥና መዘግየት ችግሩን ማቃለል መቻሉን የቢሮ ኃላፊው ተናግረዋል፡፡

የአገልግሎት አሰጣጥን የሚያቃልሉ ሲስተሞችን እያለሙ ወደ ስራ ከማስገባት አኳያ በ2018 በጀት ዓመት በኢንዱስትሪ ቢሮ፣ በኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣ በቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ፣ በሲቪል ምዝገባና የነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ፣ በአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን፣ በጤና ቢሮ፣ በትምህርትና ስልጠና ጥራትና ቁጥጥር ባለስልጣን፣ በመሬት ልማትና አስተዳደር እንዲሁም ሌሎች ተቋማት የሚሰጡ አገልግሎቶችን በቀላሉና ባጠረ ጊዜ ማግኘት የሚያስችሉ 18 ሲስተሞች በአምስት ወራት ለምተው ወደ ስራ ገብተዋል፡፡ እነዚህ አገልግሎትን በማዘመንና እንግልትን በመቀነስ ረገድ ትልቅ አቅም መሆናቸውን አቶ አዋሌ አብራርተዋል፡፡

## ለጋራ ... ከገጽ 8 የዞረ

ቦታ ብዙ ታሪኮችን መረዳት እንዲችሉ በማድረግ እርስ በርስ እንዲተዋወቁ፣ እንዲከባበሩና አንድነታቸውን እንዲያጠናክሩ በር ይከፍታል። በኢትዮጵያዊነት ውስጥ የመካተት ምልክታዊ ስሜትም ይፈጥራል፡፡ ከከፋፋይ ትርክት ወደ የጋራ ትርክት ለሚደረገው ጉዞ መሰረት በመሆን እንደሚያገለግል የታሪክ ምሁሩ ያስረዳሉ።

የኢትዮጵያውያን የጋራ የድልና ከፍታ ምልክት ከሆኑ ታሪኮች መካከል የዓድዋ ድል ዋነኛው እንደሆነ የሚያነሱት የታሪክ መምህሩ፤ ይህንን ሁሉም ኢትዮጵያዊ የሚኮራበት፣ ከጫፍ እስከ ጫፍ ሆ ብሎ ዘምቶ የተሳተፈበት የጋራ ድል ማጉላት ለብሔራዊ ትርክት ግንባታ ከፍተኛ ጥቅም ይኖረዋል፡፡

አቶ አገኘሁ አዳነ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የአለ ሥነ-ጥበብ እና ዲዛይን ትምህርት ቤት ዲን ናቸው፡፡ ቅርፃ ቅርፅ፣ ስዕል፣ ስነ ጽሑፍ፣ ሙዚቃና ሌሎች ሥነ-ጥበባዊ ስራዎች ብሔራዊ መስተጋብር፣ የወል እሴት በመገንባት፣ የጋራ እምቅ የሆኑ ሀብቶችን የመዘከርና ለትውልድ የማስተላለፍ ተፈጥሯዊ ጠባይና ጉልበት አላቸው፡፡ የአደጉ ሀገራትም ሥነ- ጥበብ ላይ በመስራታቸው ከተሞቻቸው የተዋቡ ናቸው፡፡ በሥነ- ጥበብ አማካኝነት በሚተላለፉ እሴቶች ማህበረሰቦቻቸው የሰለጠኑና የለሙ ናቸው ይላሉ፡፡

በአዲስ አበባም ሆነ በሌሎች አካባቢዎች በኮሪደርና የወንዝ ዳርቻ ልማት፣ መልሶ በመገንባት ለነዋሪዎችና ጎብኚዎች ምቹ እንዲሆኑ የሚያስችሉ መሰረተ ልማቶችን መገንባት ከሚያስገኘው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ባሻገር ማህበረሰባዊ ሁለንተናዊ ልማት በማምጣት፣ የሰለጠነ ሥነ-ጥበብን ማጣጣም የሚችል ባህል ያለው ማህበረሰብን ለመገንባት ከፍተኛ ጥቅም ይኖረዋል፡፡ በዚህ ረገድ በመዲናዋ በተገነቡና እየተገነቡ ባሉ ልማቶች ጥበባዊ በሆነ መንገድ የጋራ ትርክትን መገንባት የሚያስችሉ ታሪኮችንና ሀብቶችን ማስቀመጥ ይበል የሚያሰኝ ነው ብለው የበለጠ አጠናክሮ መስራት እንደሚገባም አቶ አገኘሁ ይናገራሉ፡፡

በኢትዮጵያ የሥነ- ጥበብ ታሪክ ብዙዎቹ የአደባባይ ሐውልቶችና መሰል የሥነ- ጥበብ ስራዎች በውጭ ሀገር ሰዎች የተሰሩ እንደሆኑ ያነሱት አቶ አገኘሁ፤ በጊዜ ሂደት ብቁ ሙያተኞችን በማፍራት ሀገሪቱ በራሷ ሙያተኞች መስራት መቻል ትልቅ እምርታ ነው፡፡ ብዙዎቹ በከተማዋ በተሰሩ ልማቶች ላይ የተቀመጡ ሥነ-ጥበባዊ ስራዎች በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አለ የሥነ-ጥበብና ዲዛይን ትምህርት ቤት ተመርቀው የወጡ ባለሙያዎች አሻራ ናቸው፡፡

ከእንጦጦ እስከ ፒኮክ ባለው የወንዝ ዳርቻ ልማት የሚካተቱ የሥነ- ጥበብ ስራዎችን በተመለከተ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአለ የሥነ-ጥበብ እና ዲዛይን ትምህርት ቤት በማማከር እየተሳተፈ ይገኛል፡፡ ስራዎቹን በመስራት የሚሳተፉትም ከትምህርት ቤቱ የተመረቁ እንደሆነ አቶ አገኘሁ ጠቁመዋል፡፡

“ሥነ- ጥበባዊ ስራዎች የሚያስተምሩ ሳይመስሉ ነው የሚያስተምሩት፡፡ የአስገዳጅነት ጠባይ የላቸውም፡፡ የዘርፉ ምሁራን እንደሚሉት የጥበብ ስራዎች ትህትና እና ኮስታራነት ተባብረው የሰው ልጅ እንደሚማር ሳያውቅ የሚያስተምሩ ዘርፎች ናቸው፡፡” የሚሉት አቶ አገኘሁ፣ ሥነ-ጥበባዊ ስራዎች ከተዝናኖት ባሻገር ማህበረሰባዊ የወል ትርክት ለመፍጠር ያገለግላሉ፡፡ የሰለጠነ ባህል ያለውና ሥነ-ጥበብ ማጣጣም የሚችል ማህበረሰብ መፍጠር ያስችላል፡፡ ልጆች የጥበብ ስራዎችን እያዩ ሲያድጉ ነገ አካባቢያቸውን መረዳት፣ መጠበቅና መተርጎም የሚችሉ ሆነው እንዲያድጉ ማድረግ ያስችላሉ ሲሉ ፋይዳቸውን አብራርተዋል፡፡

የታሪክ መምህሩ ኑሩ ይማም እንደሚናገሩት፣ ኢትዮጵያን የማዘመን ጥረት የኢትዮጵያን ማንነትና ምልክቶችን ባካተተ መንገድ መሆን አለበት፡፡ ከውጭ ቀድቶ ሙሉ በሙሉ የሌሎች ሀሳብና ምልክቶችን አምጥቶ ማስቀመጥ ከአሁን በፊት የነበረው የዘመናዊነት አረዳድ ነው፡፡ አሁን ላይ ግን በኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች የሚሰሩ፣ ኢትዮጵያዊነትን የሚያጎሉና ለጋራ ትርክት ግንባታ የሚሆኑ ሥነ- ጥበባዊ ስራዎችን አጠናክሮ ማስቀጠል ያስፈልጋል፡፡

ሀገራዊ ትርክትን ለመገንባት የሚሰሩ ስራዎችን አካታች በማድረግ የመገለል ስሜትን በማስወገድና የጋራ መንግስታዊ ባለቤትነትን በማጠናከር መስራት ይገባል፡፡ ኢትዮጵያ ብዝሃነት ያለባት ሀገር ናት፤ ብዝሃነቷ በአንድነት ውስጥ የሚታይ መሆኑን የሚያሳዩ ልማቶችን አጠናክሮ መቀጠል እንደሚገባም አክለው አስገንዝበዋል፡፡

## እየጎለበተ ... ከገጽ 9 የዞረ

የመሥሪያ ቦታን ጨምሮ የተለያዩ ድጋፎችን አግኝተናል፡፡ ለሠራተኞቻችን የሙያና ክህሎት ስልጠናዎችን (የካይዘን፣ የቴክኖሎጂ፣ የአልባሳት ዲዛይን...) ጋር የተያያዘ ከተግባረ ዕድ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ተከታታይነት ባለው ሁኔታ ተጠቃሚ ሆነናል፡፡ ከሥራና ክህሎት ቢሮ ጋር በመተባበር የሥራ ላይ ስልጠና የሚወስዱ ወጣቶችን በሥራ ላይ እንዲሰማሩ የሚደረግበት አሠራርም ወጣቶቹንም፣ ድርጅታችንንም ተጠቃሚ እያደረገ ነው፡፡ ከሥራችን ስፋት አንፃር ከመንግስት የተሰጠን መሥሪያ ቦታ ባለመብቃቱ ሌሎች ሁለት ቦታዎችን ተከራይተን እየሠራን እንገኛለን” ብለዋል።

ድርጅቱ በቂ የሆነ የሀገር ውስጥ ተጠቃሚዎች ስላሉ የገበያ ችግር እንደሌለበት አቶ ክብሮም አንስተው፤ በከተማዋ ውስጥ ባላቸው ሁለት ሱቆች (መርካቶ እና ኮልፌ) ምርቶቻቸውን እንደሚሸጡ ተናግረዋል፡፡ የጨርቃ ጨርቅ እና አልባሳት ዘርፍ አስተማማኝ የገበያ አማራጭ ስላለው፤ ድርጅቱ በሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት ውስጥ ከፍተኛ የማስፋፊያ ሥራ ለማከናወን አቅዷል፡፡ በዚህም የሠራተኞቹን ቁጥር ወደ 3 ሺህ ለማሳደግ ግብ አስቀምጧል፡፡ ለዚህ ውጤት ለመብቃት የመሥሪያ ቦታ ጥያቄ ከመንግስት ምላሽ እንደሚያገኝ ተስፋ በማድረግ እየተጠባበቁ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

የካቫና የቆዳና ቆዳ ውጤቶች አምራች ኢንዱስትሪን እንዲሁም የአልማኪር ጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ማምረቻ ኢንዱስትሪን ጨምሮ በአሁኑ ወቅት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ 2 ሺህ 265 ተኪ ምርት የሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎች በማምረት ሥራ ላይ እንደሚገኙ ያነሱት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ በቢሮ ኃላፊ ደረጃ የአምራች ኢንዱስትሪ ድጋፍ ዘርፍ ኃላፊ አቶ ጳውሎስ ኩሳ፤ ተኪ ምርትን በማምረት እንደ ሀገር ከፍተኛ ጠቀሜታ እየተገኘ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የራሱን አስተዋፅኦ ማድረጉን አጠናክሮ ቀጥሏል። ለማሳያ ያክል ብናነሳ፡- በ2017 በጀት ዓመት በከተማዋ በማምረት ሥራ ላይ ከነበሩ ኢንዱስትሪዎች 7 ሚሊዮን 461 ሺህ 764 ቶን የሚመዝን ምርት አምርተዋል፡፡ እነዚህን ምርቶች ለሀገር ውስጥ ገበያ በማቅረብ 1 ቢሊዮን 854 ሚሊዮን 859 ሺህ 224 የአሜሪካ ዶላር ወጪን አስቀርተዋል፡፡

በተመሳሳይ በያዝነው የ2018 በጀት ዓመት፣ የመጀመሪያ አራት ወራት ውስጥ ኢንዱስትሪዎቹ 5 ሚሊዮን 53 ሺህ 487 ቶን ተኪ ምርቶችን አምርተው ለሀገር ውስጥ ገበያ አቅርበዋል፡፡ በዚህም እንደ ሀገር ይወጣ የነበረውን 613 ሚሊዮን 426 ሺህ 791 የአሜሪካ ዶላር አስቀርተዋል፡፡ የአራት ወራቱ አፈጻጸም እንደሚያሳየው እንደከተማ የዘንድሮው አፈፃፀም ከአምናው የተሻለ እንደሚሆን የሚያመላክት ነው፡፡

አቶ ጳውሎስ በማብራሪያቸው፤ በአሁኑ ጊዜ እንደ ከተማ የአምራች ኢንዱስትሪዎች የማምረት አቅም 66 ነጥብ 6 ከመቶ ደርሷል፡፡ ይህንን በ2022 በጀት ዓመት ወደ 85 ከመቶ ለማድረስ ታቅዶ እየተሠራ ነው፡፡ የማምረት አቅም ማለት፡- ኢንዱስትሪዎቹ ያላቸውን የሠው ኃይል፣ የመሥሪያ ቦታ፣ ማሽን፣ ካፒታል፣ ግብዓት በአግባቡ በመጠቀም ማምረት ከሚጠበቅባቸው ከፍተኛ መጠን ውስጥ በተጨባጭ ያሳኩት ምን ያክል እንደሆነ የሚያመላክት ነው፡፡

ኢንዱስትሪዎች ከሚያመርቷቸው ተኪ ምርቶች መካከል፡- የተማሪ የትምህርት ቁሳቁሶች (ደብተር፣ እስክርቢቶና እርሳስ)፣ የተማሪ የደንብ ልብስና ቦርሳዎች፣ የተለያዩ ተቋማት ሠራተኞች የሥራ (የደንብ) ልብሶች፣ የፀጥታ አካላት አልባሳት እና ጫማዎች፣ የንፅህና እና የፅዳት መጠበቂያ ግብዓቶች፣ በኮሪደር ልማቱ ጥቅም ላይ የዋሉ የመንገድ ዳር መብራት ፖሎች (የመጀመሪያ ዙር ላይ ከቻይና ከመጣው በስተቀር)፣ የእብነበረድ (ግራናይት)፣ የቢሮ መገልገያ ፈርኒቸሮች እና መሰል ምርቶችን በሀገር ውስጥ መተካት የተቻለበትን ሁኔታ ማንሳት ይቻላል፡፡

ኢንዱስትሪዎች የሚያመርቷቸው ተኪ ምርቶች በገበያ ላይ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ቢሮው ከተለያዩ ተቋማት ጋር በመተባበር ጠንካራ ድጋፍና ክትትል እንደሚደረግላቸው ያነሱት የአምራች ኢንዱስትሪ ድጋፍ ዘርፍ ኃላፊ፤ በተለይ ምርታቸው ዓለም አቀፍ የጥራት ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን በኢትዮጵያ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት የተዘጋጀውን የጥራት መመዘኛ መስፈርት እንዲያሟሉ መደረጉን ጠቅሰዋል፡፡

# የቅጥር ማስታወቂያ

**የምዝገባ ቀን ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ 10 ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ ሲሆን የትምህርት መስረጃችሁን ዋናውን እና የማይመለስ ፎቶ ኮፒ ጋር የምታስይዙ መሆኑን እንገልጻለን።**

| ተ.ቁ | መደቡ የሚገኝበት የስራ ክፍል | የስራ መደቡ መጠሪያ | የስራ መደብ ደረጃ | ደመወዝ | የመ/መ/ቁጥር | ፆታ | ብዛት | የቅጥር ሁኔታ | ተፈላጊ ችሎታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሜዲካል ዳይሬክተር | ኤክስኪዩቲቭ ሴክረታሪ I | IX | 12566 | ክ/31-10-ጤ10-002 | ሴ | 1 | በቋሚነት | በጽህፈት ቢሮ አስተዳደር /በሴክሬተሪያል ሳይንስና ኦፊስ ማኔጅመንት/ ዲፕሎማ ወይም የቴክኒክና ሙያ በደረጃ 3 /10+3/ እና 4 የብቃት የማረጋገጫ (COC) ያላት 4 ዓመት የስራ ልምድ |
| 2 | የድንገተኛ ህክምና እና አስተኝቶ ማከም ዲፓርትመንት ኃላፊ | አንቡላንስ ሹፌር | VII | 8478 | ክ/31-10-ጤ10-60 | ወ/ሴ | 1 | በቋሚነት | አዲሱ 10ኛ ክፍል በቀድሞ 12ኛ ክፍል ያጠናቀቀና 3ኛ ህዝብ 1 መንጃ ፍቃድ ያለው እና 4 ዓመት የስራ ልምድ ያለው/ያላት |
| 3 | የመ/ህ/መ/አቅ/ክ/ስ/ጥገናና ቁጥጥር ዲፓርትመንት ኃላፊ | ጉልበት ሰራተኛ | III | 6750 | ክ/31-10-ጤ10-229 | ወ | 1 | በቋሚነት | 10ኛ ክፍል ያጠናቀቀና 2 ዓመት የስራ ልምድ ያለው/ያላት ወይም 9ኛ ክፍል ያጠናቀቀና 3 ዓመት የስራ ልምድ ያለው/ያላት ወይም 8ኛ ክፍል ያጠናቀቀና 4 ዓመት የስራ ልምድ ያለው/ያላት |
| 4 | የንብረት አስተዳደር ቡድን መሪ | የህፃናት ማቆያ ጽዳትና መልዕክት አገልግሎት ሰራተኛ | II | 6365 | ክ/31-10-ጤ10-276 | ሴ | 1 | ኮንትራት | 10ኛ ክፍል ያጠናቀቀና 2 ዓመት የስራ ልምድ ያለው/ያላት ወይም 9ኛ ክፍል ያጠናቀቀና 3 ዓመት የስራ ልምድ ያለው/ያላት ወይም 8ኛ ክፍል ያጠናቀቀና 4 ዓመት የስራ ልምድ ያለው/ያላት |
| 5 | የንብረት አስተዳደር ቡድን መሪ | የህፃናት እንክብካቤ ባለሙያ | VII | 8478 | ክ/31-10-ጤ10-274 | ሴ | 2 | በቋሚነት | በህፃናት አያያዝ፣ እንክብካቤ እና ተዛማች ሙያ መስከ ዲፕሎማ እና በሌቭል IV እና ከዚያ በላይ ያለው/ያላት በሙያው 2ዓመት ያገለገለ |

**ማሳሰቢያ ፦** ማንኛውም ተመዝጋቢ ለመመዝገብ ሲመጣ የት/ት ማስረጃ እና የስራ ልምድ ዋናውን ከማይመለስ ኮፒ ጋር ይዞ መቅረብ ይጠበቅበታል:::

- በሌቭል ወይም በደረጃ ለሚቀርቡ ማስረጃዎች የብቃት ማረጋገጫ (COC) ማቅረብ ይጠበቅባችኋል ::
- የመመዝገቢያ ቀን ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10 ተከታታይ የስራ ቀናት በስራ ሰዓት ይሆናል::
- የመመዝገቢያ ቦታ በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ወረዳ 10 ገላን ጉራ ጤና ጣቢያ የሰ/ኃ/አስ/ቡድን ቢሮ ቁጥር 406 ይሆናል::

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ወረዳ 10 ገላን ጉራ ጤና ጣቢያ**

አንሻ አደም አህመድ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 09 ሴሪ ቁጥር 0637540 እና የካ/205992/10 የሆነ በስማቸው ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ ያላቸው ሲሆን ግለሰቡ በጽ/ቤታችን ቀርበው ለዲጂታል ካርታ እንዲሰራላቸው ማህደራቸው ታጥፎ እንዲላከላቸው አገልግሎት ጠይቀውናል ይሁን እንጂ እጃቸው ላይ የነበረው ካርታ የያዙት ማህደሮች ባልታወቀ ምክንያት የጠፋባቸው መሆኑን ስለገለፁና ማኛውም ካርታውን ይገኛዋለሁ የሚል ግለሰብ በ20 (ሃያ) ቀን ውስጥ በየካ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት የስራ ሂደት ቀርቦ ማህደሮችንና ካርታ እንዲያስረክበን እየጠየቅን ካልሆነ ግን በምትኩ አዲስ ካርታ ሰርተን የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን::

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የየካ ክ/ከተማ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

**ትውልድን...** ከገጽ 12 የዞረ

ከትምህርት ቤት ውጪ የሚከበረው የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ምርቃት እንደሆነ የሚናገሩት ርዕሰ መምህሩ፣ በዓሉ የ12ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ፈተና ከተፈተኑ በኋላ አንድ ተማሪ ከአንድ ወላጅ ጋር በመገኘት በሸራተን አዲስ ትምህርት ቤቱ በሚያዘጋጀው ፕሮግራም በመገኘት የምርቃት ሥነ ሥርዓት ይካሄድበታል። የሚካሄደው መርሀ ግብር ከትምህርት ቤቱ እና ከወላጅ እውቅና ውጪ አይደለም ሲሉም አክለዋል::

"አንድ ተማሪ ከትምህርቱ በተጨማሪ ብቁ ዜጋ የሚሆነው ከቤተሰብ ጀምሮ በጋራ መስራት ሲቻል ነው" ያሉት ርዕሰ መምህሩ፤ በዋናነት ወላጅ ልጁን ወደ ትምህርት ቤት መላክ ብቻ ሳይሆን ውሎውንም ሆነ ተያያዥ ጉዳዮችን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንዳለበት ተናግረዋል::

በትምህርት ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ዲናኦል ጫላ የውጭ ባህላዊ ድርጊቶችን በተመለከተ ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት አስተያየት፣ በትምህርት ቤቶች ቀናት ተፈጥረውላቸው የሚከበሩት ስርዓተ ትምህርቱን የሚጎዱ መሆናቸውን ገልጸዋል::

ተግባሩ ሲከወን የነበረው የመማር ማስተማር በሚካሄድበት ሰዓት መሆኑ እና ጊዜያቸውን እያባከነ ያለ ሂደት እንደነበር የተናገሩት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ የውጭ ባህላዊ ድርጊቶች የተማሪዎችን ሥነ ምግባር ከማነጽ ሂደት ጋር የማይገናኙ መሆናቸውን አብራርተዋል::

የውጭ ባህላዊ ድርጊቶች በተማሪዎች ሥነ ምግባር እና በትምህርት ውጤታቸው ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳርፍባቸዋል:: በተለይም በትምህርት ቤቶች ውስጥ አንዳንድ ቦታዎች ላይ የትምህርት ቤት ንብረት የወደመበት እና ከፍተኛ ጉዳትን ያስከተለ መሆኑ አስቸጋሪ አድርጎት ነበር::

ይህ ነገር እንዳይከሰት መጀመሪያ መደረግ ያለበት ባህርይ ግንባታ ነው። ተማሪዎች ለእነሱ ጠቃሚ እና ጎጂ የሆኑ ነገሮችን የማሳየት እና የማስገንዘብ ስራ ነው መጀመሪያ መሰራት ያለበት። ይህንን ምን ያህል ጎጂ እንደሆነ፤ በተለይ ደግሞ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ እንደሚጎዳቸው የማሳየት ስራ ለተማሪዎች በየትምህርት ቤቶቻቸው ሚኒ ሚዲያን ጨምሮ በተለያዩ ክበቦች አማካኝነት የማሳወቅ፤ በተለይም የውጭ ባህላዊ ድርጊቶች የሚያስከትሉት ጉዳት ምን እንደሆነ የማሳየት፣ እነሱም ይህንን ተረድተው በሂደቱ እንዳይሳተፉ የማድረግ እና የማስገንዘብ ስራ በሁሉም ትምህርት ቤቶች ላይ እየተሰራ መሆኑን ተናግረዋል::

በየትምህርት ቤቶቹ የሥነ ምግባር፣ ሰላምና ፀጥታ ክበብ አለን:: ትምህርት ቤቶች ላይ በዚህ ክበብ አማካኝነት ተማሪዎች እንዲማሩት እና እንዲያውቁት የማድረግ ስራ እየተሰራ ነው:: በቀጣይም ትምህርት ቤቶች መጤ ባህሎችን ተግባራዊ እንዳያደርጉት በህግ የመከልከል ስራ ነው የምንሰራው ብለዋል::

አሁን ላይ ሁሉም ትምህርት ቤቶች ተግባራዊ አድርገዋል:: አንዳንዴ በመንግስት ደረጃ የወረዱ ቀናትን ተገን በማድረግ የሚፈልጉትን ነገር ግን ሊተገበሩ የማይገባቸውን የማክበር ሁኔታዎች ይፈጠራሉ:: ያንን የመከልከል ስራ እየተሰራ ነው:: እንደዚያም ሆኖ ያን ያህል ያጋጠመ ችግር አለመኖሩን ኃላፊው ተናግረዋል::

ትምህርት ቢሮ የሚያስተዳድረው በከተማዋ የሚገኙ ትምህርት ቤቶችን እንደሆነ የተናገሩት ምክትል ርዕሰ መምህሩ፤ በዚህ ሂደት ውስጥ ወጣ ብሎ ስናገኘው የማስተካከል ስራ እንሰራለን። የሥነ ዜጋ እና ሥነ ምግባር ትምህርት ላይም ትኩረት በመስጠት ተማሪዎች እንዲማማሩ የማድረግ ስራ እንሰራለን። የውጭ ባህላዊ ድርጊቶችንም ሆነ ለመማር ማስተማሩ እንቅፋት የሆነውን ድርጊት ተማሪው እንዲፀየፈው እና 'የእኔ አይደለም' እንዲል ደግሞ ግንዛቤውን የማሳደግ ስራ እየተሰራ ይገኛል::

እንደ ሀገርም ሆነ እንደ ከተማ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ቀንን ጨምሮ የተለያዩ ቀናት ሲከበሩ ትምህርት ቢሮ አቅዶ ባወረደው መሰረት ትምህርት ቤቶች እንዲያከብሩት ይደረጋል:: የውጭ ባህላዊ ድርጊቶችን በተመለከተ የተዘጋጀው ደንብም ምንም እንኳን እንደ ትምህርት ቢሮ ቀደም ብሎ ወደ ትምህርት ቤቶች በማውረድ የተለያዩ ስራዎች እየተሰሩ ቢሆንም የጋራ አፈፃፀም እንዲኖረው በማድረግ ረገድ ትልቅ ፋይዳ አለው:: መማር ማስተማሩ ላይ ሁሉም ባለድርሻ አካል እንደመሆኑ የደንቡ አፈፃጸም ላይ ሁሉም ትኩረት ሊያደርግ ይገባል ብለዋል::

በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ወረዳ 01 የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ቁጥር ኮ/ቀ/የማ/ን/መ/106/16383/00 ሴሪ ቁጥር 040119 በአቶ ቀለመወርቅ ቢክስ አካሉ ስም የተመዘገበ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) የጠፋባቸው መሆኑን በቀን 09/04/2018 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይገዌዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ 30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ሙና አሊ ከማል በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 01 የሚገኘው የይዞታ መለያ ቁጥር AA000080115475 በሴሪ ቁጥሩ 0152243 በስማቸው በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ይገዌዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

እነ ወ/ሮ አስቴር ገብረስላሴ(6 ሰዎች) በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በጉ/ክ/ከተማ ወረዳ 07 ነዋሪ የሆኑት የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000100703690 የሴሪ ቁጥር R 030315 በቀን 10/05/2010 ዓ/ም ወጪ የተደረገ ካርታ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት/ካርታ/ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለው /ይገዌዋለው/ የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ጉለሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 04 አስተዳደር ውስጥ ኤርታሌ የማምረቻ ማሽነሪና ግባት አምራች በካርታ ቁጥር 021565/2 በሴሪ ቁጥር 105302 የተመዘገበ ይዞታ ማህደራቸው ከማህደር ክፍላችን መገኘት የነበረበት የጠፋባቸው ስለሆነ ማህደሩን የያዘ ግለሰብ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ድረስ መጥተው ካላሳወቁ ማህደር በማዘጋጀት አገልግሎት የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ዩ.ዩ.ኤ የጋ/ህ/ሥ/ማህበር በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 13 ክልል ውስጥ የሚገኝ ይዞታ ካርታ ተመዝግቦ የተሰጣቸው የመጀመሪያ ካርታ ቁጥር አቃ/ቃ/ክ/ከ/ሊዝ 0650 ሴሪ ቁጥር 191132 እና በካርታ ኮፒ አገልግሎት የተሰጣቸው ካርታ ቁጥር አቃ/ቃ/ክ/ከ/ሊዝ 06501 ሴሪ ቁጥር 029802 የይዞታ ስፋት 1135.68 ካ.ሜ የሆነ ካርታ የጠፋባቸው መሆኑን ከፖሊስ ማስመዝገባቸው በቁጥር ወ/መ/10/12223/18 በቀን 07/04/18 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ በተገለፀልን መሰረት ወጪውን ግለሰቡ በመቻል በጋዜጣ እንዲታወጅላቸው እየገለፅን በማንኛውም ምክንያት የጠፋው ካርታ ይገዌዋለሁ የሚል አካል ካለ እስከ 30 ተከታታይ የስራ ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ካላቀረቡ በምትኩ ሌላ ካርታ የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በ ወ/ሮ ማህሌት ዘውዴ ተሰማ እና በአቶ ግርማ ነጋሽ ጎሹ ስም የተመዘገበ ይዞታ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000090604936 ሴሪ ቁጥር L098537 የጠፋባቸው መሆኑን በ 09/04/2018 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይገዌዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ 90 (ዘጠና) ቀናት ውስጥ ጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአቶ አሊ አራጋው መሀመድ ስም የተመዘገበ ይዞታ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 09 ካርታ ቁጥር K08/01/5/35/352/5234/03 ሴሪ ቁጥር 039735 የጠፋባቸው መሆኑን በ22/02/2018 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይገዌዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ 90 (ዘጠና) ቀናት ውስጥ ጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአቶ ረሺድ ዲዶ ቢፎ ስም የተመዘገበ ይዞታ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08 የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000090806962 ሴሪ ቁጥር L 017250 የጠፋባቸው መሆኑን በ 14/04/2018 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይገዌዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ 90 (ዘጠና) ቀናት ውስጥ ጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በ እነ መርሻ ለማ ሻይ (4ሰዎች) ስም የተመዘገበ ይዞታ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 የካርታ ቁጥር ወ2/ውዝ01/369/10334/01 ሴሪ ቁጥር 041235 የጠፋባቸው መሆኑን በ13/04/2018 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይገዌዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ 30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ ወ/ሮ ወ/ት አበራ በለጠ የተባሉት በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 11 ቀበሌ ወይም በቀድሞው ወረዳ ---- የቤት ቁጥር የካርታ ቁጥር የካ/246/183777/07 ሴሪ ቁጥር 051824 ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት ይገዌዋለው የሚል ካለ እስከ 20 ቀን ድረስ አዲስ አበባ ከተማ የካ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እንዲቀርቡ ባይቀርቡ ግን በምትኩ ሌላ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የየካ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ኢንዱራንስ ሪል እስቴት ኃ/የተ/የግ/ማህበር በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 ካርታ ቁጥር ቦሌ 12/82/1/17/264686/264830/272951/03 የሆነ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኝ ይዞታ /የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት /ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይገዌዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአቶ መኮንን አማረ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ወረዳ 01 ክልል ውስጥ የሚገኝ ይዞታ ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ ቁጥር 00537/2 ሴሪ ቁጥር 0708290 የቦታው ስፋት 205 ካሬ ሜትር የሆነ ካርታ የጠፋባቸው በመሆኑ በጋዜጣ እንዲታወጅ እየገለጽን በማንኛውም ምክንያት የጠፋውን ካርታ ይገዌዋለሁ የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከታወጀበት ዕለት ጀምሮ እስከ 20 ተከታታይ የስራ ቀናት ባለው ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ካላቀረቡ በምትኩ ሌላ ካርታ የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

## የጠፋ ካርታ በጋዜጣ እንዲወጣ ስለማሳወቅ።

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው የመሬት ይዞታ ምዝገባና ወረጃ ኤጀንሲ የካ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በወረዳ 12 በ ብርሃን ፃአሩ ወልደስላሴ ስም የተመዘገበ የይዞታው መለያ ቁጥሩ AA00005120733849901010 የተሰጠበት ቀን 03/02/15 ዓ/ም እና ሴሪ ቁጥር C216843 የሆነ የመብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እንደጠፋባቸው በቁጥር የካፖ/መ/ቁ/15/7299 በቀን 8/4/2018/ ዓ.ም የሚገልፅ መረጃ በማቅረብ አመልክተዋል፡፡ ይህም በጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ ካርታውን አይቻለው ወይም መብት አለኝ ባይ በ90 ቀን ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ ቀርቦ እንዲያሳውቅ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች በምትክ ሰርተፍኬት የሚሰጥ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ/ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ/ወ/ሮ/ወ/ሪት አወት አማኑኤል አብርሃም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 7 የይዞታ ልዩ መለያ ኮድ AA000100705826 በሴሪ ቁጥር L 0105499 የሆነው ይዞታ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኝ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ/ሰርተፍኬት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለው /ይገዌዋለው/ የሚል ሰው ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረበ በምትኩ ሌላ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ/ሰርተፍኬት/ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ጉለሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ በቀድሞ ወረዳ 8 ቀበሌ 24 በአዲሱ አደረጃጀት ወረዳ 06 የሚገኘው ቤት በካርታ ቁጥር አካ-21/26/1/3028/አ. ካርታ በሴሪ ቁጥር 022449 በትሬዛ ጉርሙ እና ማርቆስ ዳመነ ስም የይዞታ/የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ ተሰጥቶ የነበረ ቢሆንም ካርታው በመጥፋቱ ምክንያት የካርታ ኮፒ አገልግሎት የተጠየቀ ሲሆን አገልግሎቱን ለመስጠት በይዞታ አስተዳደር አገልግሎት አሰጣጥ ደንብ ቁጥር 163/2016 መሰረት የባለይዞታው የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ መጥፋቱ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ማስታወቂያ ወጥቶ በ20(ሃያ ቀን) ቀን ውስጥ ተቃዋሚ ካልቀረበ አገልግሎቱን መስጠት እንደሚቻል ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ስለሆነም ካርታውን ይገዌዋለው የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ20 (ሃያ ቀን) ውስጥ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ አገልግሎት ፕሮጀክት ጽ/ቤት ይዞ እንዲቀርብ እያሳሰብን ይህ ካልሆነ ግን በመመሪያው መሰረት የጠፋውን ካርታ አምክነን በምትክ ሌላ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተደደር ቢሮ የአዲስ ከተማ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ምንተስኖት ጥላሁን ጉልላት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 ካርታ ቁጥር ቦሌ የሆነ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኝ ይዞታ/የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት/ካርታ ቦሌ/12/71/6/14/118034/00 ሴሪ 1511247 ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይገዌዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

# የአዲስ አበባ አዲሱ የስፖርት ወጋገን

**በሳህሉ ብርሃኑ**



ፎቶ- ከገፀ ድር
በከተማዋ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ልማት በስፋት እየተከናወነ ነው

ምቹ ባልሆኑና ደረጃቸውን ባልጠበቁ ሜዳዎች ስፖርታዊ እንቅስቀሴዎችን ማድረግ የአዲስ አበቤዎች ታሪክ አካል ሆኖ ዘመናት ተቆጥረዋል:: የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን የቀድሞ ተጫዋቾች የነበሩት እንደ ሳላዲን ሰይድ፣ አዳነ ግርማ፣ ሽመልስ በቀለና ጌታነህ ከበደን መሆን ህልማቸው የሆነ በርካታ አዳጊዎች አቧራ የለበሰ ፊታቸውን እየጠራረጉ የሸራ ኳስ የሚያንከባልሉባት እንደነበረች አይዘነጋም::

በመዲናዋ ስመጥር የሆኑት እንደ አልማዝዬ ሜዳ፣ መላጣ ሜዳ፣ ብሪሞ እና '15 ሜዳ'ን የመሳሰሉ የስፖርት ማዘውተሪያ ሜዳዎች ደግሞ እነዚህ ህልሞች ይጸፉባቸው የነበሩ ገጾች ናቸው። በእርግጥ እነዚህ የስፖርት ስፍራዎች የአዳጊዎቹን ህልም መሬት ለማውረድ ምቹ ስፍራዎች አልነበሩም:: ለዓመታት አስታዋሽ አልነበራቸውምና አብዛኞቹ ደረጃቸውን ያልጠበቁ የንጽህና ጉድለት ያለባቸው፣ ለአደጋ አጋላጭና አልፎ አልፎም ለአካባቢው ወጣቶች የሱስ ማስተናጋጃ ስፍራ ሆነውም አገልግለዋል።

አሁን ግን ሁኔታው እየተቀየረ ነው፤ ከፈረንሳይ ለጋሲዮን እስከ አልማዝዬ ሜዳ፣ ከሲኤምሲ እስከ ቤቴል ድረስ፣ ከብሪሞ እስከ ባንቢስ ስፖርታዊ ስፍራዎች አስታዋሽ አግኝተዋል:: የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ መረጃ እንደሚያመላክተው በከተማዋ ከ1 ሺህ 500 በላይ ስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች እንደ አዲስ ተገንብተው ወደ አገልግሎት ገብተዋል:: ከእነዚህ ውስጥ ከ100 ያላነሱት በኮሪደር ልማቱ አማካኝነት የተገነቡ ናቸው::

በአዲስ አበባ ከተማ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ የማህበራትና ውድድር ዳይሬክተር አያሌው ታደለ እንደሚገልጹት የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ለከተማዋ ድምቀት ከመሆን ባለፈ የህብረተሰቡን የስፖርት ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ ናቸው። በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተገነቡ ያሉ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል እና የስፖርት ዓይነቶች ያካተቱ መሆናቸው ቀደም ሲል ከነበሩት የተለዩ ያደርጋቸዋል ብለዋል።

በተለይም የኮሪደር ልማቶች ላይ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ተካትተው መሰራታቸው የቴኳንዶ ስፖርትን ጨምሮ ሌሎች ስፖርቶችን ለማስፋፋት እንደሚረዳም ታይቷል:: የአዲስ አበባ የወርልድ ቴኳንዶ ፌደሬሽን ፅህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ጥላሁን ዋሲሁን የሚገለፁትም እየተሰሩ ያሉ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ከተለመዱት እንደ እግር ኳስ፣ አትሌቲክስና መሰል ስፖርቶች ውጪ ላሉ የስፖርት አይነቶችም ዕድል የፈጠሩ ናቸው:: በእርግጥም የስኬት ቦርድ ስፖርት ውድድር፣ የቴኳንዶ ፌስቲቫልና ትርዒትን የመሳሰሉ ስፖርታዊ ክንውኖች እየተለመዱ የመጡት ከአዳዲስ ስፖርታዊ ማዘውተሪያ ስፍራዎች መስፋት ጋር ተያይዞ ነው::

የአዲስ ልሳን ዝግጅት ክፍል በተለያዩ የከተማዋ አካባቢዎች ተዘዋውሮ እንደተመለከተው በርካታ መጫወቻ ሜዳዎች ተገንብተዋል:: ቀደም ባሉት ጊዜያት ተጎሳቁለው የነበሩ ሜዳዎችም ዛሬ ላይ ዘመናዊ የሜዳ ንጣፍ ተሰርቶላቸው ለመርገጥ የሚያሳሱ ምቹ የመጫወቻ ስፍራ ሆነዋል:: አብዛኞቹ እንደ አዲስ የተሰሩት የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች በምሽት ጨዋታ እንዲደረግ የሚያስችል መብራት ጭምር የተገጠመላቸው ናቸው። በበጋው ወቅት አቧራማ ክረምት ሲገባ ደግሞ ከመቅፀፊት የሚጨቀዩት ሜዳዎች ዛሬ ላይ መልካቸው ተቀይሯል። መጫወቻ ሜዳዎቹ ዛሬ ላይ ዘመናዊ የሜዳ ንጣፍ፣ ደረጃቸውን የጠበቁ መቀመጫዎችና አጥር ተሰርቶላቸው ምቹ ሆነዋል::

ወጣት በረከት ሙሉነህ የሚለውም ይህንኑ ነው:: ወጣቱ በረከት በሰጠን አስተያየት፣ "አሁን ላይ የቅርጫት ኳስና እግር ኳስ የምንጫወትባቸው ሜዳዎች ምቹ ናቸው:: ከዚህ ቀደም ግን በአብዛኛው የምንጫወተው የመኪና መንገድ በመዝጋት በመሆኑ ብዙ ችግሮችን አሳልፈናል:: ለከፍተኛ ጉዳትም እንዳረግ ነበር:: ከተሽከርካሪ ጋር እየተጋፈጥን ጭምር ነበር የምንጫወተው" ብሏል::

በአካባቢያቸው የነበረው ሜዳም ቢሆን ደረጃውን የጠበቅ ባለመሆኑ ራሳቸውን ለአደጋ አጋልጠው ይጫወቱ እንደነበር የሚገልፀው ወጣት በረከት፣ አንዳንድ ጊዜም መጫወቻ ሜዳ ፍለጋ ከአካባቢያቸው ርቀው ለመሄድ ይገደዱ እንደነበርም ያስረዳል::

ዮሴፍ አለባቸው አስተያየታቸውን ከሰጡን ወጣቶች መካከል አንዱ ሲሆን፣ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ በወረዳ ሁለት ወጣት ማዕከል ውስጥ በተሰራው የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ውስጥ በሚገኝ ሜዳ ስፖርታዊ እንቅስቃሴ እያደረገ ነው ያገኘነው:: በግቢው ውስጥ እንደ አዲስ የተሰራው የእግር ኳስ መጫወቻ ሜዳ እጅግ ዘመናዊና ለማንኛውም ስፖርታዊ እንቅስቃሴ የተመቸ ስለመሆኑ ነግሮናል:: ከዚህ በፊት ግን ሜዳው ደረጃውን የጠበቅ ባለመሆኑ ራሳቸውን ለአደጋ አጋልጠው ይጫወቱ እንደነበር የሚገልፀው ወጣት ዮሴፍ፣ አንዳንድ ጊዜም መጫወቻ ሜዳ ፍለጋ ከአካባቢያቸው ርቀው ለመሄድ ይገደዱ እንደነበርም ያስረዳል::

> **"በከተማዋ ከ1 ሺህ 500 በላይ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ተገንብተዋል፤ እነዚህ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎች ታሳቢ ያደረጉና በርካታ የስፖርት አይነቶችንም ያካተቱ ናቸው"**

በተጨማሪም በከተማዋ ልዩ ቀለም ያለው ለሩጫ ብቻ ተብሎ በተዘጋጀው በርካታ ኪሎ ሜትሮችን በሚሸፍነው መንገድ ላይ የውጭ ሀገር ዜጎችን ጨምሮ በርካታ የመዲናዋ ነዋሪዎች በየቀኑ ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች ሲያደርጉ መመልከት የተለመደ ነው:: ለዚህም ማለዳ ተነስቶ ከዓድዋ ድል መታሰቢያ ዙሪያ፣ ከአራት ኪሎ ቀበና መገናኛ፣ ከአራት ኪሎ ቦሌ አየር ማረፊያ፣ ከቦሌ ድልድይ መገናኛ፣ ከአዲስ ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን ማዕከል እስከ ሲኤምሲ፣ በሌላ በኩልም ከሜክሲኮ አፍሪካ ህብረት፣ ሳርቤት፣ ወሎ ሰፈር አካባቢዎችን መመልከት በቂ ነው::

ከፒያሳ፣ አራት ኪሎ፣ መገናኛና ቦሌን ይዞ ከተማዋን የሚያካልለው የኮሪደር ልማት ስራ ለስፖርቱ ዘርፍ የሰጠው ትኩረት በስፖርት ወዳዱ የመዲናዋ ነዋሪ ዘንድ ምስጋና የተቸረውም ለዚሁ ነው:: በአዲስ አበባ ገርጂ አካባቢ ነዋሪ የሆነው ዋለልኝ ተስፋዬ አስተያየትም ይህንኑ የሚያጠናክር ነው:: ዘወትር እሁድ ስፖርታዊ እንቅስቃሴ የማድረግ ልምድ እንዳለው የሚገልጸው ወጣት ዋለልኝ ከዚህ ቀደም ንጹህና አረንጓዴ ከባቢዎችን በመዲናዋ ማግኘት አስቸጋሪ እንደነበርና ለስፖርታዊ እንቅስቃሴም ምቹ እንዳልነበር ያስረዳል:: እንደዚሁም የመዲናዋን ህዝብ የሚመጥን ሰፋፊ አረንጓዴ ስፍራዎችን ማግኘት አስቸጋሪ ነበር:: ስፖርት ልንሰራ ወጥተን በሽታ ሸምተን እንመለስ ነበር በማለት ያስታውሳል::

የመዲናዋ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች በአብዛኛው ተለውጠዋል በሚለው አሰተያየት የአዲስ ተስፋችን እግር ኳስ ፕሮጀክት መስራችና አሰልጣኝ መሐመድ ናስር ይስማማል:: የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች፣ የአዳጊና ወጣት ፕሮጀክቶች ስፖርቱን ለማስፋፋትና ለማሳደግ ዋንኛ መሰረቶች ናቸው የሚለው አሰልጣኝ መሐመድ አሁን ላይ በመዲናዋ በሲኤምሲ አካባቢ ከ7 እስከ 17 ዓመት ያሉ አዳጊዎችን በፕሮጀክት አቅፎ በማሰልጠን ላይ ይገኛል::

አሰልጣኙ እንዳለውም በመዲናዋ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች መስፋፋት ስፖርታዊ እንቅስቃሴ እየተነቃቃና ተተኪ ተጫዋቾች እንዲፈጠሩ መሰረት እየጣለ ይገኛል:: በተለይም ወጣቱ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ በማጣቱ ምክንያት አልባሌ ቦታዎች ለመዋል ይገደድ እንደነበር አስታውሶ፣ አሁን ላይ ግን ንጽህና ያላቸውና ደረጃቸውን በጠበቁ መጫወቻ ሜዳዎች የመዲናዋ ወጣቶች በሚኖሩበት፣ በሚማሩበትና በሚሰሩበት አካባቢ በስፖርት እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ ትልቅ ዕድል ፈጥሯል::

አሰልጣኝ መሐመድ አያይዞም እነዚህ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች መሰራታቸው ይዞ የመጣው ብዙ ለውጥ እንዳለ ያስረዳል:: አዳጊዎችን በፕሮጀክት ይዘው ለሚያሰለጥኑ አሰልጣኞች ደረጃውን በጠበቀ ስፍራ ማሰልጠን ስለጀመሩ፣ የስፖንሰር ድጋፍና ለስራቸው ተመጣጣኝ ክፍያ እንዲያገኙ አስችሏል። ለአዳጊዎች የሚሰጡ ስልጠናዎችም ሳይንሳዊና ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑና የጉዳት መጠን እንዲቀንስ እንዳገዛቸው አብራርቷል::

እንደ አሰልጥኝ መሐመድ ማብራሪያ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎቹ ህዝባዊ መሰረት እንዲኖራቸው በማድረግ ከመንግስት ድጎማ ተላቅቀው ራሳቸውን እንዲችሉ ማድረግ ይገባል። ተቋማቱ በባለሙያ እንዲተዳደሩ ቢደረግ፣ በአንዳንዶቹ ላይ ከመጫወቻ ሜዳ ውጪ እንደ መጻዳጃ ቤትና ፍሳሽ ማስወገጃ፣ ልብስ መቀያየሪያና መሰል ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው እንደሚገባ ያነሳሉ:: አያይዞም የስፖርት ማዘውተሪ ስፍራዎቹ ተገቢው ባለሙያ ተመድቦላቸው እንክብካቤ ሊደረግላቸው እንደሚገባና ለምሳሌ መጫወቻ ሜዳዎቹ ውሃ የሚያጠጣ፣ ሜዳዎቹ እረፍት የሚያገኙበትን ጊዜ የሚቆጣጠርና ጥገና የሚደረግበት አሰራር ሊዘረጋ እንደሚገባ አሳስቧል::

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ በበኩሉ፣ በከተማዋ የተገነቡ እና እየተገነቡ የሚገኙ የስፖርት ማዘወተሪያ ስፍራዎች በህግ እንዲተዳደሩ መመሪያ ተዘጋጅቷል:: በአዲስ መልክ የሚሰሩና ነባር የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ተገቢው ጥበቃ እንዲደረግላቸው ከማዕከል እስከ ወረዳ በቅንጅት መስራት እንደሚገባና የሁሉንም ማዘውተሪያዎች መረጃ በአንድ ቋት ማደራጀት የተጠያቂነት ስርዓት ለመዘርጋትና ይህም የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎቹን በዘላቂነት ለመጠቀምና እየተነሱ ያሉ ችግሮችን በአሰራር ለመመለስ ያስችላል ተብሏል::